

# ዳግማዊ
# አጤ ሚኒልክ

አፈወርቅ ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስ

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# ዳግማዊ፡አጤ፡ሚኒልክ

## ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ።

## ኣፈወርቅ ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስ

## ዘብሔረ ፡ ዘጌ።

በሺህ ፡ ተ፱፻፩ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት፡

ሮማ ፡ ከተማ ፡ ታተመ።

# A

# YOHANNES

## TENERO FIGILIUOLO DELL’AUTORE L’EDITORE

II prof. Afework, che io avevo pregato di detare una succinta biografla dell`imperatore Menilek II, mi ha dato lo scritto che qui pubblico. Esso non e. come I`A stesso, esponendone le ragioni, dichiara nella introduzione, una completa storia della vita dell’attuale imperatore, ma piutosto una narrazione dei piu salient episodi diessa, dalla prigionia presso teodero sino alla campagna del 1896.

Degli avvenimenti che narra I’A. e stato sovente testimone. E talora partecipe, di che viene al lavoro singalore interesse; ma maggiore, e a questo, almeno. Che io ho inteso pubblicandolo.

II lavoro e redatto in quello stile ricco vivo colorito che all’A. e abituale. E la narrazione degli episodi e inframmezzata e collegata da pagine descrittive, polemiche, apologeticha; apologetiche sono, anzi, la struttura e l`intonazione generale del lavoro: quail, dunque, dovevano

ispirarle ad uno scrittore abissino l`opera e la fortuna del suo sovrano.

Naturalmente, in uno scritto come questo, ovesi tratta difusamente del coneflitto avvenuto fra l'Abissinia e i`Italia, non potevano mancare peroledi riprovazione per taluni funzionarii deplmatici e military italiani: tuttavia, nel biasimare, l'A. si tiene ben lontano da quelle violenze di giudizi e di linguaggio, di cui e, cui e, inverce, tutto untipico esemplare l`epinicio raccolto dalla missione duchensne-Fournet.

Mentre la stampa volgera al termine, L'A. ha aggiunto al suo lavoro il messaggio imperial del 10 genbot 1901 (18 maggio 1009); tale do-cumento era gia stato pubblicato nel fascicolo di guigno del semeur d`ethiopie, sebbene in una redazione alquanto piu concise di quella qui riportata.

In un indice sono raccolti I nomi di persona e di luogo contenuti nel testo. II nome Menilik, ricorrendo quasi ad ogni pagina, non-e registrato in tale indice: vi e bensi nome di Guerra dell'imperatore. A quasi tutti I nomi personali abissini segue I`indicazione del titolo o della carica da sono accompagnati nel testo; consimile indicazione mi e parsa superflua pei nomi italiani, qualche nome locale tigrino, come ad es, e dall'A. dato in forma un po'differente da quell

ache, se non erro, e usata sul luogo, ma la forma adoperata nel testo e conservataanco nell`indice

Una traduzione di questo testo sara, a I’io piacendo, pubblicata in seguito.

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# ማውጫ

በአማን ወልዱ ለሰሎሞን ወልደ ዳዊት። .......... 7
ዳግማዊ ምኒልክ ባሥራ ሁለት ዓመትዎ። .......... 11
አጤ ተክለ ጊዮርጊስና አጤ ምኒልክ። .......... 17
አጤ ዮሐንስና አጤ ምኒልክ። .......... 18
የምባቦ ጦርነት .......... 23
አጤ ዮሐንስ ወደሸዋ። .......... 26
አጤ ምኒልክና ጣይቱ ብጡል። .......... 28
አረርጌ። .......... 29
ኢትዮጵያና የዳግማዊ ምኒልክ ንግር። .......... 32
በስደት ሲኖር ሲኖር ኑሮ የሰሎሞን ዘውድ በ፲፰፻፹፩ ዓመተ ምሕረት ከስፍራው ገባ። .......... 37
አጤ ምኒልክና የኢጣልያ መንግሥት። .......... 44
ያዱ ጦርነት። .......... 55
ለኢትዮጵያ ሣህል ወምሕረት። .......... 68
የጃንሆይ የዳግማዊ ምኒልክ ቃል። .......... 69

# ዳግማዊ ምኒልክ

## በአማን ወልዱ ለሰሎሞን ወልደ ዳዊት።

ወይ ግሩም! ግሩም ነው ግሩም የግሩም ግሩም ምኒልክ ትበል እንዲህ እናት ስምን መላክ ነው የሚአወጣው። ምኒልክ ማለት የሰሎሞን ልዥ የዳዊት የልዥ ልዥ በመሆኑ አያስደንቅም። ምኒልክ ማለት ምን ይልክ ይሆን እግዚአብሔር ማለት ነው።

እግዚአብሔር እሄው ምኒልክን ላከ። ላከ ማለት አነገሠ ማለት አይደለም። መንግሥማ እነቴዎድሮስ፣ እነዮሐንስ፣ እነተክለ ጊዮርጊስ እስንቱ ሌላው ሁሉስ ነግሦ አልነበረምን፤ ምኒልክ ግን እንደሌሎች አልነገሠም። ዳግማዊ ምኒልክንስ እግዚአብሔር መርጦ፤ ሂድ ኢትዮጵያ ተጎድታለች፣ የኢትዮጵያ ሰው አልቅሷል በህዝቡ ድንቁርና በዝቶበታልና፤ ሂድ ኢትዮጵያን አይዞሽ በላት የደሀውን እንባ አድርቅለት፤ ድንቁርና ጨለማ እውቀት ግን ብርሃን ነውና በኢትዮጵያ ጨለማው እንዲሻር ብርሃን እንዲወጣ ለህዝቡ የረቀቀው በልብ የጐላው በዓይን እንዲከሰትለት አስተምረው፣ አርመው፣ ጠብቀው፤ ላንተ አይደለም ለኢትዮጵያ ነው ያነገሥሁህ ብሎ ላከው።

ዳግማዊ ምኒልክም በተላከው እሄው ወዲአው ከመንገሡ ደሀውን ከባርነቱ አርነት አወጣ። እስከ ትላንት ድረስ በነቴዎድሮስና በናፄ ዮሐንስ ጊዜ የኢትዮጵያ ድሀ ለወታደር መጫወቻ ባርያ ነበረ። ባርያ በገዛ እራሱ ማዘዝ እንደማይሆንለት፤ የኢትዮጵያ ደሀም በገዛ ቤቱ ማዘዝ አይሆንለትም ነበረ። የሚአዝዝበት ቆርፋፋ ጋሻ ያነገበና አንድ ባለጌ ጦር የያዘ አንድ የመሸበት ደበናንሳ የጀራረገውና ተሰገባው በስፍራ ተጣልቶ ፀሐይ የሚሞቀው ጎራዴ መሳይ በወገቡ ያገነበጠ ቅማላም ወታደር ነበረ። ይሄው ወታደር ግን እሱን ደስ ላይለው፣ የሌላውን ደስታ ሲከለክል፤ ለገዛራሱ ላያልፍለት፣ የደሀውን ንብረት ሲአፈርስ ይኖር ነበረ። ይሄው ወታደር እንኳንስ ተሰሪነት ገብቶ ለቅሎጥ ሂዶም ባደረበት አገር ሳይቀር ደሀውን የፊጥኝ አስሮ ነጭ ኑግ፣ ጥቁር

ወተት፣ ውለድ ሲልና ባለቤቶቹ ምሽቲቱ እንደገረድ ባልዮው እንደሎሌ፤ እግር አጥበው፣ አልጋ አንጥፈው፣ ትራፊውን በልተው፤ እነሱ ተምድር፣ እሱ ታልጋ ተኝተው ያድሩ ነበረ። ከተም አንዳንድ ጊዜስ መልከ ቅን ምሽት የነበረችው ባላገር በመከራ ላይ መከራ፣ በግፍ ላይ ግፍ፣ በውርደት ላይ ውርደት ታክሎበት ያድር ነበረ። ከነዚሁ መከረኞች አንዱ መልከ ቅን ምሽት ነበረችው። አንድ ቀን በቴዎድሮስ ጊዜ አንድ ቅጫማም ነፍጠኛ ተቤቱ ተመርቶ ገባና ባለቤቲቱ መልከ ቅን ሁና ባያት ጊዜ ነፍጡን ተጉልበቱ ላይ አድርጎ አንተ እሂች እትህ እስንት ዓመቷ ነው፡- ቁርጥ አንተን ትመስላለች አለው። ያ ባላገር ግን ምሽቴ ናት ማለቱን ፈራ። ያም እርጉም ነፍጠኛ በጥፊ እያጣፈረ ያችን ምሽቱን ይዞበት አደረ። ከዚህ በኋላ ያ መከረኛ ደሀ አዘንና ንዴት ያዘውና ታገር እኖር ብየ ከብት እነዳ ብየ ልዥ አሳድግ ብየ ለባሻ ዳርሁለት ምሽቴን እቴ ብየ ብሎ አንጎራጎረ።

የውነት ነው እንዲህ ያለውን ስራ እነዚያ ንጉሦች አድርጉ ብለው አልነበረም፤ ነገር ግን በእነዚኣ ንጉሦች ጊዜ ማን ደፍሮ ከወታደር ጋራ ይናገር ነበረ። ለነዚያ ንጉሦች የበህር ልዣቸው ወታደር ብቻ ነበረ። ባላገሩንማ እንደ እንጨት ጠርበው እንደጭቃ አንቦልቡለው የሰሩት ያስመሰሉት ነበር እንጂ እንደነሱ በአራያ ሥላሴ የተፈጠረ አይመስላቸውም ነበረ። ነገር ግን ደንቆሮነታቸው ነው እንጂ፣ ሁሉም እንደነሱ ትክክል የተፈጠረ ነበረ። አለደሀ ዘውድ አለገበሬ ማድ ጀግና ማስከተል እንዳይቻልና ደኅን ካስለቀሱ ተሥላሴ ይወቀሱ መንግሥተ ሰማያትን አይወርሱ፣ መሆኑን አውቀውት ቢሆን ደግ ነበር። በሆነ ባልሆነው እግዚአብሔር አሳምሮ የሰራውን አካል ዓይን በሳት ሲአስፈርጡ ምላስ በምላጭ ሲአሳጥሩ ይኖሩ ነበረ። አሁን በደጉ በዳግማዊ ምኒልክ ጊዜ ግን ያ ሁሉ መከራ፣ ያ ሁሉ ግፍ ቀረ በኢትዮጵያ ፀሐይ ወጣ፤ ጨለማ ተሻረ ወታደርና ባላገር ትክክል ያድር ጀመረ፤ ደኅና ባለጠጋ ትክክል ተናግሮ ሁሉም እንደልቡ ተዛንቶ ይኖር ጀመረ፤ አለፈለት፣ ደስ አለው፣ በዓለም እንቅልፉን ይተኛ ጀመረ።

በናጤ ቴዎድሮስና በናጤ ዮሐንስ ጊዜ ከጅብ አምልጦ የቀረ ቆርብት የመሰለ ጨርማዳ ጋሻ በብብቱ ያጣበቀና ባለቋድ ወይም ሲሶ እንጨት ብረት ወሳይ በጫንቃው አጋድሞ ብቅ ያለ እንደሆነ፤ አንድ እከካም ነፍጠኛ ብቻውን ሁኖ አንድ መንደር ሲአሥር፣ ሲፈታ፣ ሲአስጨንቅ ያድር ነበረ። በዳግማዊ ምኒልክ ጊዜ ግን እንኳን ነፍጥ ተሸክሞ መድፍም በጐኑ አሟቅሎ ቢሄድ ለወታደር የሚፈራ ባላገር የለም። በምኒልክ ጊዜ ወታደርም ባላገርም ሁሉም በየውለታው ትክክል ያድራል፤ ሁሉም ትክክል ነው።

ትላንት ባጤ ዮሐንስ ጊዜ ንጉሡ አልፈው ሲሄዱ ትክ ብሎ አክብሮ እንደ ብርቅ ንጉሡን ያየ ሰው እንደ ከፉ አድራጊ በጀርባው የዱላ ማት ይፈላበት ነበረ። ደጉ ምኒልክ ግን ማንም የተገፋ ደሀ፣ ማንም ሰራተኛ፣ ማንላቸውም ባላገር ቀርቦ ጉዳቱን ጥቃቱን ቢነግረዎ እንዳባት ስቀው እንደ ንጉሥ አውቀው፤ ለምን ደፈረኝ ሳይሉ በምሕረት ዓይነዎ አይተው፣ ፊተዎን አብርተው ሰምተው ደስ ያሰኙታል። ምኒልክ ለደኅው አባት ነው እንጂ፣ ንጉስ አይደለም። ለምኒልክ ምን ኵራት፣ ምን ንፍገት፣ ምን ሰሀ፣ ምን አመል አለው? የምኒልክ አመሉ ሰው ሁኖ መፈጠሩ። ሰው ተሆነ ዘንድ እንደሰው አደገ፣ እንደጀግና ተዋጋ፣ እንደ ንጉሥ ዘውድ ጫነ ሉል ጨበጠ፤ ነገር ግን እንደ ንጉሥ አልገዛም፤ ብቻ ለህዝቡ እንዳባት አሰበ፣ ለደኅው እንደናት አዘነ። የሱ አመሉ ሥጋ ለብሷልና እንደሰው ታደገ፣ እንደ ሰው አረጀ፣ ሞት አይቀርምና እንደ ሰው ይሞታል፤ ሞት አይቀርለትም። የዳግማዊ ምኒልክ ይሄ ነው አመሉ ይሄ ነው፤ የኢትዮጵያ ጉዳት ይሄ ነው፣ ያበሻ መከራ። ምነው እንደ ሰው የማታረጅ፣ እንደ መላክ የማትሞት፣ የማትታመም፣ የማትደክም ሁነህ ተፈጥረህ ቢሆን አንተ እናት ንጉሥ! ።

የዳግማዊ ምኒልክ ታሪክ ከተወለዱ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያደረጉት ነገር እንደ ገድል በብር ተጭሮ፣ በቀለም ተጽፎ ባላለቀም ነበረ። የርስዎን ታሪክ የርስዎን ታምራት፤ በዚህ ቀን ተወለዱ፣ በዚህ ወር በዚህ ዓመት እንዲህ አደረጉ፣ በዚህ ወር በዚህ ዓመተ ምሕረት ከዚህ ተዋጉ፣ እገሌን ድል መቱ፣ በዚህ ወር እንዲህ ያለ ሥራ ተሰራ እንዲህ ያለ ሕግ ተደነገገ እያለ ተጠንቅቆ

አሳክቶ የዳግማዊ ምኒልክን ታሪክ ለሚጥፍ ሰው ትልቅ ክብር ብዙ ሞገሥ በተገባው ነበረ። ዳሩ ግን ማነው በመልካም አማርኛ ኣጣፍጦ አሳምሮ ላንባቢው እንዲቀና፣ ለሰሚው እንዲገባ፣ ትንሽ ትልቁ፣ እሴት ወንዱ እንዲአነበው እንዲአደንቀው አድርጎ የሚጥፈው? የተማሩት ሊቃውንቱም ቅዳሴ ምስጢረ ሥላሴ፣ ድጓ፣ ቅኔ፣ መዋሲት ዝማሬ ይመስል፤ በጥንት ባሮጌው ቋንቋ በግዕዝ ብቻ ነው መጣፍ የሚወዱ። ይሄን አሮጌ ቋንቋ ለቤተክርስቲያን ትተው የቀረውን የዓለሙን ነገር የዓለሙን ሥራ ግን ሁሉ በሚአውቀው ሁሉ በሚናገረው ቋንቋ ባማርኛ ቢጽፉ ደግ ነበረ። ደግሞም ለንግድ ለጥበብ ለመንግሥት የሚጠቅመውን አማረኛውን ማረም፣ ማሳመር፣ ማስተማር፣ ማልማት ይሻላል፤ ይገባልም። ዛሬ አለቃ ታየ የሚሉት ደቀመዝሙር ያጤ ምኒልክን ታሪክ ነገሥት ሊጥፍ ታዝዟል ይባላል። እስቲ ተሆነ እናያለን፣ እግዚአብሔር ይገዘው። ነገር ግን ሁሉ እንዲአነበውና እንዲገባው በግዕዝ ትቶ ባማርኛ ባደረገው ደግ ነበረ። አማረኛው ግን ገጥ ያለ፣ ቅልጥፍ ያለ፣ ላንደበት የተስማማ ለጆሮ ያልገለማ፣ ላንባቢው የሚመች ለሰሚ ማይሰለች እንደሆን አድርጎ መጣፍ ነው። ግዕዝ ብቻ ማሳመር አማረኛ ንቆ ግዕዝ ብቻ ማክበር፤ አባቱን ገሎ ላማቹ ይነጭ፣ አማቱን ጋርዶ እናቱን ያስፈጭ የሚሉት ነገር ነው። አማረኛ ማልከስከስ አሮጌ ቋንቋ ማደስ የተገባም አይደል፤ አማረኛን ማረም፣ ማሳመር፣ ማስተማር ነው። አማረኛን የሚአሳምር ጠፋ እንጂ ለመዶግዶግማ ፊደል ሳይቈጥር በመጋፊያ እየጣፈ በገል እየጫረ ጽሕፈት የተማረ ሁሉስ ይዶገዱግ የለምን? ያም ሆነ ያም ሆነ አለቃ ታየን የመሰለ ብልህ የተማረ ሰው አማረኛውን አስተውሎ ይጥፍ ዘንድ ተስፋ አለን። ያጤ ምኒልክን ታሪክ በግዕዝ የጻፈ እንደሆነ ግን ታልተጻፈ ቁጥር ነው። በፈረንጅ አገርም የጥንቱን ቋንቋ ሮማይስጡን ለቤተክርስቲያናቸውና ለሌላ ነገር ትተው ሁሉም አዲስ ቋንቋቸውን እያረሙ አሳመሩ ለልጆቻቸውም ያስተምራሉ። ኢትዮጵያም እንዲሁ ማረግ ይገባታል።

እኔ አቅሜ ባይሆን ነው እንጂ የግማዊ ምኒልክን ታሪክ ነገሥት ብጥፍ ደስ ባለኝ ክብርም በሆነኝ ነበረ። ነገር ግን በምን አቅሜ በሄትኛውስ እውቀቴ

እጽፈዋለሁ? ተነገሩ ሁሉ በፊት ተፈረንጅ አገር ኑሮዬ ተበዛ ዘንድ ነገሩን ሁሉ ረስቸዋለሁ። ይሄ ብቻም አይደል ጥንቱንም ታገሬ ሳለሁ ያጤ ምኒልክን ታሪክ ከተወለዱ ጀምረው እስከ ዛሬ ያደረጉትን ሁሉ ታሪክ አንዱ ላንዱ ሲአጫውት፤ የስሚ ስሚ የቅጂ ቅጂ የሰማሁት ነበር እንጂ የታሪክዎን ሁሉ ነገር ዘመኑን ለይቶ ቀኑን ደንብቶ በዚህ ቀን በዚህ ወር በዚህ ዓመት እንዲህ አደረጉ፤ በዚህ ዘመን በዚህ ዓመት እንዲህ ፈጠሩ ብሎ አጥርቶ ለይቶ የሚናገር መጽሐፍ ምንም አላየሁም አላነበብሁም። ያም ያየሁትና የሰማሁትም ታሪክዎ ይበልጠው ወገን ተረሳኝ ረሳሁት ረስቸዋለሁ። ነገር ግን ዋናው ታሪከዎ የተጣፈውም እስቲታደስ ያልተጣፈውም እስቲጣፍ ድረስ ያን የማውቀውን ነገር ባጭሩ አድርጌ እጥፈዋለሁ። ነገር ግን ያገሬ ሰዎች ለምን ታሪኩን ሁሉ ቈርጦ ተወው ወይም ቀኑን ወርሁን ዘመኑን አሳሳተ ብላችሁ አትፍረዱብኝ ብረሳው ነው። በቀረውም ይሄ የምጽፈው ነገር ጥቂት ወሬ ነው እንጂ ሙሉ ታሪከ ነገሥት እንዳልሆነ ታውቃላችሁ። ደግሞም ሰው የያዘውን ተወረወረ ፈሪ አይባልም ነውና፣ ያን የማውቀውን የምገነዘበውን እጥፋለሁ እንጂ የማታውቀውን ታልጣፍህ ብሎ የሚፈርድብኝ ሰው የለም።

## ዳግማዊ ምኒልክ ባሥራ ሁለት ዓመትዎ።

በሰኔ በ፳፩ ቀን ፲፰፻፵፫ ዓመተ ምሕረት አጤ ቴዎድሮስ አይሻል ላይ እራስ አሊን ድል መቱ። ራስ አሊ ከድሉ በኋላ አምልጠው ደራ ተዋቄ ደቦ አድነኝ አሉና ተጠጉ። ዋቄ ደቦ ግን መቸም የቴዎድሮስ ስም ድፍን ኢትዮጵያን ማንቀጥቀጥ ጀምሮ ነበረና ፈርቶ፤ ራስ አሊ ከኔ ቢመጡ እንዳያመልጡ ይዣቸዋለሁና የወደዱትን ያድርጉ ብሎ ወደ አጤ ቴዎድሮስ ላከ።

ዋቄ ደቦ ያደረገው ነገር ከራስ አሊ ጆሮ ደረሰ። ከዚህ ወዲአ እራስ አሊ ተጨነቁና ቶሎ ውስጥ ለውስጥ ለሸዋ ንጉሥ ለኃይለ መለኮት አደራ ያውጡኝ፤ አምኘው ብመጣ ዋቄ ደቦ አስሮ ለቴዎድሮስ ሊሰጠኝ ሆነ ብለው ላኩ። የሸዋው ንጉሥ ኃይለ መለኮት ገሥግሰው ወደ ዋቄ ደቦ ደረሱና ደራን

ከበው አምባውን ሰብረው ራስ አሊን አዳኑ። አጤ ቴዎድሮስ ይሄን ወሬ በሰሙ ጊዜ ተናደዱና፤ ታጠቀ መጣሁብህ! ብለው በኃይለ መለኮት ላኩ። ነገር ግን ክረምት ከለከላቸውና ቴዎድሮስም ወሎ ሁነው ኃይለ መለኮትም ሸዋ ሁነው ሲፈካከሩ ከረሙ። ቴዎድሮስ የድፍን አማራንና የወሎን ጦር አስከትተው በጥቅምት ሸዋ ገቡ። የግሸው ገዥ ሀብተ ማርያም ገባላቸው። ፍርኩታ ሲደርሱ የይፍራታው ገዥ አቶ በድሉም ገቡላቸው። አጤ ቴዎድሮስ ጉር ሥላሴ ሲደርሱ ሸዌ ብዙ ሰው ፈጀባቸው። ኃይለ መለኮትም ፈረስ አጠጥረው የሸዋን ጦር አስከትተው ለመዋጋት ተዘጋጁ። ነገር ግን ግፋን መሄዱን ትተው ታንኮበር በላይ ቶራ መስክ ሰፍረው ይጠብቁ ጀመር። ንጉሥ ኃይለ መለኮት ጤና ታጡ ብዙ ቀናቸው ነበረ። አጤ ቴዎድሮስ ተሰልፈው ተጠንቅቀው ሲጓዙ ሲጓዙ ደብረ ብርሃን ደረሱ። የሸዋው አቶ በዛብህ ባንድ ወገን ጋልቦ ብዙ ሰው ፈጀባቸው። የሁለቱም ንጉሦች ጦር ቅርብ ለቅርብ ተሳፈረ። ነገር ግን ተዛሬና ተነገ ይዋጋሉ ሲባል ንጉሥ ኃይለ መለኮት የልብዎን ሳያደርሱ ታመውበት የነበረ በሽታ በረታና አጣድፎ ዕለቱን ገደለዎ የኅዳር አመ ፴ ሌሊቱን አረፉ። አጤ ቴዎድሮስ ግን ደብረ ብርሃን ላይ ሠራዊታቸውን ሙሉ ሰልፍ አሰልፈው ለጦርነት ሲጠብቁ ሳለ የንጉሥ ኃይለ መለኮት መሞት ወሬ ደረሰላቸው። ነገር ግን ነገሩ እውነት አልመስላቸው አለና እንደተሰለፉ ወደፊት ተጉዘው ቶራመስክ ደረሱ። ከዚህ ወዲያ ኃይለ መለኮት የሚቀበሩበትን ስፍራ በጠቋሚ ሰምተው ሰውን ከደጋው ትተው ከጥቂት ሰው ጋራ ደብረ በግዕ ወረዱ። እውነትም የደረሱ ጊዜ ኃይለ መለኮት መቃብር ሲወርዱ አዩና አጤ ቴዎድሮስ አለቀሱ።

የሸዋ መኳንንት ግን እንዲአው ሳይታሰብ በድንገት ጌታቸው በሞቱ ጊዜ ተደናግጠው ለመዋጋት ምንም አላሰቡ ብቻ በሽሽጎት ቶሎ የኃይለ መለኮትን እሬሳ ለመቃብር ደብረ በግዕ ሰደዱና የጌታቸውን ልጅ ሕፃኑን ምኒልክን ከጠላት እጅ እንዳይወድቅባቸው ይዘው ሸሹ። አጤ ቴዎድሮስ ይሄን በሰሙ ጊዜ ከደብረ በግዕ ወጡና ጠራ ላይ ሲደርሱ ከደጋው ላይ የነበረውን ሠራዊት ሂድ አያምልጥህ ብለው አዘዙ፤ እርሳቸውም ይከተሉ ጀመር። የጠራን ሜዳ

ተሻግረው መገዘዝ ሲደርሱ በራስ እንግዳ እግር አሳዝዘው ብዙ ጦር ወደበረኸት ሰደዱ። አጤ ቴዎድሮስ ግን ወደ ምንጃር ተቈለቈሉ። በዚህ ጊዜ የሸዋ መኳንንት ሕፃኑን ምኒልክን ይዘው ካረርቱ ተነሥተው ቆላ ቆላውን ሂደው ከሰምን ተሸግረው ወደ በረኸት ብቅ ሲሉ ከነራስ እንግዳ ጋር ተጋጠሙና እናቶ ሀብቱ ሕፃኑን ምኒልክን ይዘው ሲሸሹ የቀሩት የሸዋ መኳንንት ተዋጉ። ከጦርነቱ ብዙ ሰው አለቀ፤ የሸዋው አቶ በዛብህም ተያዙ።

ይኼ ሁሉ ተሆነ በኋላ ነገሩ ሁሉ እንዳልተሳካ አይተው፣ ከሕፃኑ ምኒልክ ጋራ የነበሩት መኳንንት በከንቱ ይሄን ጮርቃ ልጅ ለምን አገር ላገር እያዞርነ እናደክመዋለን? ብለው መከሩና መጣነ ብለው ላጤ ቴዎድሮስ ላኩ፤ ወዲያውም ሕፃኑን ይዘው ገቡ። አጤ ቴዎድሮስም በምኒልክ መግባት እጅግ ደስ አላቸው። የዚያን ጊዜ ሕፃኑ ምኒልክ ፲፪ ዓመቱ ነበረ።

ከዚህ ወዲያ አጤ ቴዎድሮስ ሸዋን ለተገባው ለንጉሡ ልዥ ለምኒልክ መስጠት ትተው ለንጉሡ ወንድም ላቶ ኃይሌ መርድ አዝማች አሰኝተው ሹመው ሰጡ። ነገሩ ለምኒልክ መስጠቱ ሸዋ ባላባቱን ታገኘ አይገዛኝም ብለው በመፍራት የተነሳ ነው። የዚያን ጊዜ የምኒልክ አጎት አቶ ዳርጌ፣ ገና ወጣት ጐበዝ ነበሩና ከሕፃኑ ምኒልክ ጋር አብረው በቴዎድሮስ እጅ ወደቁ። አጤ ቴዎድሮስ የሸዋን ነገር አሰማርተው ሲአቆሙ አግር መንገደዎን ሲአልፉ የጃርሶን አሮሞ አሳምነው በደስታ ወደወሎ ተመለሱ። ሕፃኑን ምኒልክን እራስ ውቤን ጠባቂ አድርገው መቅደላ ታምባው ላይ አስቀመጡ።

ይኼ በሆነ በሶስት ዓመት አቶ ሥራህ ብዙ የሚባል የሸዋ ሰው መርድ አዝማች ኃይሌን ነውረኛ ነህ ከጃንሆይ ጠላት ከርቄው ባላባት ጋር ተላልከህል፣ መልክተኞችንም ተግር እስከ ራስ አንቈጥቍጠህ ሸልመህ ሰደህል ብሎ ከሶ ከሹመታቸው አስሽሮ አሳሠራቸው። አጤ ቴዎድሮስ ከዚህ ወዲያ ለሸዋ ሰው ማነን ብሾምለት ይወዳል? ብለው ላቶ ሥራህ ብዙ ቢአማከሩት፣ አቶ ዳርጌን ቢሾሙለት ደስ ይለዋል አለ። አጤ ቴዎድሮስ በዚህ ምክር ለሸዋ አቶ ዳርጌን ለመሾም ነገሩን ጨረሱ። በዚህ መካከል አቶ ጃራ የሚሉት የሸዋ ሰው አቶ ሥራህ ብዙን ካቶ ዳርጌ ተመሳጥረሀል፣ ነገር አለህ ብሎ ከሰሰው፤

ነገሩም እውነት ሁኖ ተገኘ። በዚህ አቶ ዳርጌም ታሠሩ፤ እንዲህ አቶ ሥራህ ብዙም ተዋረደና ቀረ። ከዚህ ወዲያ አጤ ቴዎድሮስ ነገሩ ደነቃቸውና ሽዎች እንዲአውም ባያያችሁ የተንኮል መዝገቦች ናችሁ ብለው የመንሥት ትውልድ የሌለውን አቶ በዛብህን ለሸዋ ምስለኔ አድርገው ሹመው ሰደዱ። ነገር ግን የዚያን ጊዜ የንጉሥ ኃይለ መለኮት አንደኛው ወንድም አቶ ሰይፉ ሸፍተው የሸዋን እኩሌታ ይልቁንም ያንኮበርን ቈላ ቈላውን ሁሉ ጨርሰው ይዘው አንኮበር ተቀመጡ። ላቶ በዛብህ የማይቻሉ በሆነ ጊዜ አጤ ቴዎድሮስ እንደ ገና ሸዋ ዘመቱ። አቶ ሰይፉን ድል አድርገው ሸዋን ሁሉ እንደ ገና አሳምነው አቶ በዛብህን ሸዋ ትተው አጤ ቴዎድሮስ ወደ በጌምድር ተመለሱ።

ሕፃኑ ምኒልክም ይሄ ሁሉ ሲሆን የቁም ዕሥር ሁኖ ተቀመጠ። እንደ እውነት ግን አጤ ቴዎድሮስ ተገዛ ልዣቸው ተመሸሻ ምኒልክን አብልጠው ይወዱ ነበረ። መሸሻና ምኒልክ አብረው አደጉ። ምንም የቁም እሥር ቢሆን ምኒልክ በቴዎድሮስ ቤት ተከብሮ ተቈላምጦ ተከብክቦ አደገ። ነገር ግን ያ ሁሉ መከብከብ ያ ሁሉ መቈላመጥ ምን ሊሆን? ተልብ ሊደርስን ነው? በወርቅ ቀፎ ተዘግቶ ተሚኖር ቆቅ ቅጠል ለቅጠል የሚዛለል ወፍ ይበልጠዋል። ምኒልክ ድሮ ነፍስ እያወቀ አእምሮ እየዋጠ ሄደ፤ ልዥነቱ ቀረ። ድሮ ምኒልክ ያገሩ ነፋስ ያገሩ ወንዝ ይናፍቀው ገባ። ድሮ ምኒልክ ይሮጥበት የነበር መስክ፣ ይድህበት የነበር እልፍኝ ውል ይለው፤ ይናፍቀው ጀመረ። ድሮ ሕፃኑ ምኒልክ ኃይለ መለኮትን ያህል አባት በጠዋት ተቀጭቶ ሂዶበት ያያት የቅማቱ አልጋ በኃይለኛ እጅ እንደ ፈረሰ ያባቱ ዘውድ አላግባብ እንደወደቀ አየው። እሱም ገና ነፍስ ያላወቀ ልዥ ሁኖ ተከላክሎ ያባቱን አገር ባለማዳኑ ያዝን፣ ይተክዝ፣ ይቆረቆር ጀመረ። ቀጥሎም ጉብዝናው እየገፋ በሄደ ጊዜ ያለፈውስ አለፈ፣ ለንግዴሁ ምን ሲሆን እናያለን፤ ከዚህ ሁነን ምን እንጠብቃለን? አለና ምኒልክ አገሩን ለመግባት ልቡ ቈረጠ። ከዚህ ወዲአ የመሄዱን ነገር ሌት ተቀን ያስብ ጀመረ፤ ወዳገሩም ውስጥ ለውስጥ መላላክ ጀመረ። በዚህ መካከል አጤ ቴዎድሮስ የገዛ ልዣቸውን አግባ ብለው ለምኒልክ አጋቡ። ነገሩ ለብልሀት ነበረ። አጤ ቴዎድሮስ ያሰቡት መቸም

ብልህ ነበሩና፣ የኋላ ኋላ ምኒልክ ላገሩ ጌታ ሳይሆን አይቀርምና እሂን ጊዜ ልዝዥን ላጋባው፤ ለኔም ጥግ ይሆነኛል፤ የኔም ዘር በልዥ ምክንያት ባለዘውድ ባላልጋ ሁኖ ይቀራል ነበረ። ነገር ግን የሥላሴ አሳብ እንዲህ አልነበረም።

ምኒልክ ግን ለጊዜው እንቢ ማለት አልሆነለትም፤ በውድም በግድ አገባ። የምኒልክ አሳብ ተጥንቱም ጀምሮ ለማግባት ያሰበው ጣይቱ ብጡልን ነበረ። የዚን ጊዜ ጣይቱ ብጡል ገና ላካለ መጠን ያልደረሰች ጮራ ያላያት ጽጌረዳ ትመስል ነበረ። ጣይቱ ብጡል ገና ነብስ ጨርሳ ሳታውቅ ለዘውድ የታጨች በመልኳም አይደል፤ ባባት የሚተባበራት በኢትዮጵያ አልነበረም፤ በየጁ የራስ ጉግሳ የልዥ ልዥ በስሜን የደጃች ኃይለ ማርያምና የጎሩት ልዥ፣ የነማርየ፣ የነዶሪ፣ የናሉላ እት ናት። እነሂ ሁሉ ንጉሥ ባይሆኑ ዘውድ ባይጭኑ ንጉሥ አከል ሁነው ንጉሦችን አንደግዜ ደግፈው ታልጋ ሲአወጡ፤ አንደጊዜ ጐትተው ሲአወርዱ እንደፈቃዳቸው ሲአደርጉ ይኖሩ ነበር። ጣይቱ ብጡል ገና ጮርቃ ልዥ ሁና ለዘውድ የታጨች በዘሯ ብቻም አይደል፤ መልኳ ልብ የሚአዘነጋ ውበቷ ላይን የማይጠገብ ከጠጉሯ እስከ ጥፍሯ አንድ አመል አንድ ስህ የሌለባት ነበረች። ጣይቱን የመሰለ ማን ነበረ? ላያት የምታሳዝን ለሰማ የምታስደንቅ ነበረች። ያም ሆነ ያም ሆነ፣ የዚያን ጊዜ የጣይቱ ብጡል ነገር በግድ ቀረ ምኒልክ ገና ወጣት ልዥ፣ በግዱ ያጤ ቴዎድሮስን ልዥ አገባ። ነገር ግን የሸዋ መሄድ ነገሩ ተቆረጠና ምኒልክ በሰኔ በ፷፬ ባ፲፰፻፶፰ ዓመተ ምሕረት በሌሊት ከጥቂት ሰዎች ጋር ገሥግሶ በወይዘሮ ወርቂቱ በኩል አድርጎ ሸዋ ገባ። የሸዋው ገዢ አቶ በዛብህ ምኒልክ ከቴዎድሮስ አምልጦ ከሸዋ መሬት ገባ ባሉት ጊዜ የድፍን ሸዋን ጦር አስከትቶ ግፋን ወደቀወት ተጓዘ። አቶ በዛብህ በተከተለው ፈረሰኛ ብዛት ኮርቶ እንኳን ድል መሆኑን ጥንቱንም ምኒልክ ከዚያ ከጥቂት ጦሩ ጋራ ደፍሮ ይዋጋኛል ብሎ አልጠረጠረም ነበረ። እውነትም የምኒልክ ተከታይ ከሸዋ መሬት መንገድ ለመንገድ ያጠራቀመው ጦር ቢበዛ ቢበዛ አራት መቶ ያህል ነበር ይላሉ። ነገር ግን ያ ወጣት ልዥ ምኒልክ ገና በ፳፪ ዓመቱ ምንም ያን ሁሉ ስፍር ቁጥር ያልነበረው ጦር ቢአይ፣ ምንም ያን እሳት የሆነ ጀግና አቶ በዛብህን ቢአውቀው እንደ ልዥ ዓይኑ

ሳይፈራበት፣ ልቡ ሳይባባበት፣ ተመህል ገባበት። የዚያን ጊዜ ወይዘሮ እጅግ አየሁ የምኒልክ እናት ከግድም ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ገብተው እያለቀሱ የግብር ስንዴ ይፈጩ ጀመር ይላሉ።

የሸዋ ጦር በስደት ይኖር የነበረውን ጌታውን፣ የጌታውን ልዥ የውነተኛውን ባላልጋ ምኒልክን ባየ ጊዜ ሁሉም እንኳንስ ለበዛብህ አግዞ ሊወጋው እልልታውን እያቀለጠ የናፍቀት እንባውን በጁ እየጠረገ ተቀበለው። አቶ በዛብህም ጋልቦ አመለጠና ፍቅሬ ግምብ ገባ ። ከዚህ ቀን ጀምሮ አጤ ምኒልክ በሸዋ ነገሡ ከዚህ ወዲህ ከተገባዎ ታያት ተቅድመ አያተዎ አልጋ ያነቃነቀዎ አልተገኘም።

(*) እስከዚህ ድረስ የሕፃንነትዎን ታሪክ ለማሳመር ቃሉን ባንትታ ስጽፍ ነበር ተንግዴህ ግን ቃለ አጋኖ ካለበት ሥፍራ በቀር እንደሚገባው በእርስዎታ እናገረዋለሁ።

አጤ ቴዎሮስ ግን አጤ ምኒልክ ከከዱ በማግሥቱ ተናደዱና ታሥሮ ከተቀመጠበት እያስጎተቱ እያስወጡ ብዙ ሰው በገደል አስጣሉ። የወይዘሮ ወርቂቱን ልዥም እናቱ ለምኒልክ አግዛ ለምን ሸሽጋ ሰደደችው ብለው በንዴት ገደል አስጣሉት። እሄ በሆነ በሁለት ዓመት አጤ ቴዎድሮስ ሸዋንም ደግመው ሳይረግጡ ምኒልክንም ሁለተኛ ሳየዩ፣ ተንግሊዞች ጋር ተዋግተው ድል ቢሆኑ በገዛ ጠበንጃቸው ሞቱ።

አጤ ምኒልክ ወዲአው በሸዋ እንደነገሡ የምስራቾ ታሥር ዓመት በኋላ ከቴዎድሮስ እሥራት አምልጬ አገሬን ገባሁ ባባቴ አልጋ ተቀመጥሁ ብለው ባደኑ ገዥ በኩል ለንግሊዝ መንግሥት ላኩ። የንግሊዝ መንግሥትም በኤካቲት ባ፳፫ ቀን ባ፲፰፻፷፰ ዓመተ ምሕረት ቴዎድሮስን እንወጋለንና ለቴዎድሮስ አይርዱብን፣ ለኛ ግን ቢረዱ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደተገባዎ ለርስዎ ይሆናል ብለው ላኩ። አጤ ምኒልክ ግን ለንግሊዞች እሺ ታሉ ወዲያ ምንም ቢሆን አጤ ቴዎድሮስን እንዳባት አርገው ይወዱ ነበርና ለሁሉም

ሳይረዱ ቀሩ። ብቻ ብዙ ፍሪዳ አበሻ ለወጣው ለንግሊዞች ጦር ሰደዱ ነገር ግን ፍሪዳው ሳይደርስ በፊት እንግሊዞች ድል አድርገው ተመለሱ።

# አጤ ተክለ ጊዮርጊስና አጤ ምኒልክ።

ወዲአው አጤ ቴዎድሮስ እንደ ሞቱ ባ፲፰፻፷ ዓመተ ምሕረት አጤ ተክለ ጊርጊስ ነገሡ። አጤ ምኒልክ ግን በዚህን ጊዜ ወደበጌምድር ተሻግረው ካጤ ተክለ ጊዮጊስ ጋራ ለመከላከልና በኢትዮጵያ ለመንገሥ አልፈለጉም። ስለምን የሸዋ መንግሥትዎ ጭራሹን አልተሸራሸም ነበረ። ባንድ ወገንም አሮሞ እስተ ጠራና እስከ ደብረ ብርሃን እየጋለበ ባደጋ ሰው እየፈጀ ይሄድ ነበረ። ባንድ ወገንም እናቶ በዛብህን እነመርድ ኃይሌን ያህል ጠላት ነበረብዎ ደግሞም ሸዋ ተገቡ ገና ሁለት ዓመት ብቻ ነበረና ሁሉን ባንድ ጊዜ ማሰማራት አልተቻለዎም ነበረ።

አጤ ተክለ ጊዮርጊስ እኔን ሁሉ በወሬ ይሰሙ ነበረና ወዲአው እንደነገሡ አክብረው ፈርተው ሁላችንም በያለንበት ተሰማምተን እንኑር ብለው ለሸዋው ንጉሥ ላጤ ምኒልክ ላኩ። አጤ ምኒልክም እሺ ብለው ላኩ። ከዚህ በኋላ አጤ ምኒልክ ወሎን ማሳመን ጀመሩ። አጤ ተክለ ጊዮርጊስ ምኒልክ ወሎን ጨርሶ ተያዘ በኋላ ወደኔም ሳይጋፉ አይቀር ብለው ሠግተው ባ፲፰፻፷፪ ዓመተ ምሕረት ገሥግሰው ዘቢጥ ላይ በሩን ያዙና ገብር ንጉሠ ነገሥቱ እኔ ነኝ ብለው ላጤ ምኒልክ ላኩ። አጤ ምኒልክ ግን መቸም ከተፈጥሮዎ ማስተዋል እንጂ ለነገር መቸኮል አይወዱምና እሺም እንቢም ሳይሉ በራስ ጐበና እጅ የዚያን ጊዜ ገና አቶ ጐበና ይባሉ ነበር፣ ለግብር አልነበረም ለፍቅር ብለው ብዙ ፈረስና በቅሎ ለተክለ ጊዮርጊስ ሰደዱ። ብልሀቱ ወሎን ጨርሸ ሳላሳምን አስቀድሞ መጣላቱ ያሰብሁትን ሁሉ ነገር ያበላሽብኛል ለማለት ነበረ። በዚህ መካከል ያጤ ተክለ ጊዮርጊስ አማች የንደርታ ሽፍታ ደጃች ካሳ ትግሬን ሁሉ ለመያዝ አለሁ፣ አለሁ ይል ጀመረ። ተክለ ጊዮርጊስ አንድ ላዳን ጤፍ ሰደዱና የኔ ሠራዊት በዚህ ቁጥር ነውና አትችልም ግባ ብለው ላኩ።

ደጃች ካሳ ያን ጤፍ አሳረረ አስቆላና የኔ ነፍጥ እንዲህ ያሳርረዋል፤ የኵራህበትን ጦር ብሎ መለሰ። እንዲህ ማለቱ እንግሊዞች ቴዎድሮስን ለመውጋት ሲወጡ ስላገዛቸው ፲፪ መድፍና ብዙ ነፍጥ ሰጥተውት ነበርና በዚአ ነበር ኵራቱ። ተክለ ጊዮርጊስ ዘቢጥን ለቀቁና አማቹን ገሎ ምሽቱን አስለቃሽ እያሉ እየፈከሩ ወደትግሬ ገሠገሱ። ደጃች ካሳም አማቹን ገሎ እቱን አስለቃሽ እያለ እየፈከረ አዷ ላይ ቆየ። ወዲአው ሁለቱ በሐምሌ ባ፲፰፻፷፫ ዓመተ ምሕረት አዷ ላይ ተጋጠሙ ተክለ ጊዮርጊስ ድል ሆኑ ደጃች ካሳም ዮሐንስ ተብለው በኢትዮጵያ በጥር በ፲፰፻፷፬ ዓመተ ምሕረት ነገሡ። አጤ ምኒልክ ግን ወሎን ቀጥቅጠው በዚህ ጊዜ አስገቡ የወሎ ባላልጋዎች ሁሉ አመኑ።

## አጤ ዮሐንስና አጤ ምኒልክ።

አጤ ዮሐንስ ነገሡና ምንም አጤ ተክለ ጊዮርጊስን ድል ቢመቱ ጭራሹን ደስታቸውን ደስታ አላደረጉትም፤ የሸዋ ፈረስ የምኒልክ ብርታት አሳቡ በልባቸው ተበርዞ እንቅልፍ አሳጥቷቸው ነበር። በዚሁ አሳብ አጤ ዮሐንስ አክብረው ፈርተው ላጤ ምኒልክ በያለነበት እርሰዎም በሸዋ እኔም በትግሬና በመሀል አበሻ ተሰማምተን እንኑር ብለው ላኩ። አጤ ምኒልክም እሺ ብለው የፍቅር ደብዳቤ ላኩ። ነገር ግን መቸም የምኒልክ ልማድ ለመስጠት አይገመገምምና፣ ለፍቅር ብለው ብዙ ፈረስና በቅሎ ላጤ ዮሐንስ ላኩ። አጤ ዮሐንስ ግን ያጤ ምኒልክን ለጋስነት ማድነቅ ትተው የፍርሀት መሰላቸውና ተደፋፈሩ፣ በላይ እኔ ነኝ አሉ።

አጤ ምኒልክ በዚህ ተናደዱና ዋና ዋና መኳንንተዎን ሰብስበው ነገሩን አማከሩ። የሸዋ መኳንንት ሁሉም ተሁሉ ሁሉ ራስ ዳርጌ ራስ ጐበና እነደጃች ገርማሜ እንዋጋ ይዋጣልን፣ እናስገብራለን እንጂ ለትግሬ አንገብርም አሉ። ነገሩ በዚህ ተቈረጠ። አጤ ምኒልክ ከዚህ ወዲያ ከምስር ንጉሥ ጋር ተላላኩ። የምስር ንጉሥ ወዳጤ ዮሐንስ ብዙ ጦር ለመዋጋት ላከ። ባንድ ወገንም ባውሳ

በኩል ብዙም አይባል በመጠኑ ጦር ላጤ ምኒልክ ኢጋዥ ብሎ ካለቃ ብሩ ጋር ወደ ሸዋ ሰደደ። አጤ ዮሐንስ በቱርኩ መምጣት ደንግጠው የድፍን ኢትዮጵያን ጦር ባዋጅ ክተት አሉ ወዳጤ ምኒልክም ነገሩን ሳያውቁ፣ እባክዎ ይገዙኝ ብለው ላኩ። የምስር ጦርም ጎዳጉዲ ደረሰና ምሽጉን አበጀ። ነገር ግን አጤ ዮሐንስ ከሸዋ በቀር የድፍን አበሻን ጦር አስከትተው ተዋጉና ለወሬ አንድም ሳይቀር ቱርኩን እንደካንቻ መቱት። ካለቃ ብሩ ጋር ባውሳ የወጣውም የምስር ጦር ያውሳው ንጉሥ መሀመድ አንፉሪ ወዳጅ መስሎ ፍሪዳውን ወተቱን ሰጥቶ እንግድነት ተቀብሎ አሳድሮ ሲአቆም ሌሊት ምንም የለብነ ብሎ ከተኛበት ለዘር ሳይቀር አርዶ አርዶ ጣለው። የምስር መንግሥት በዚህ ተናዶ እንደገና ደሙን ለመወጣት ብዙ መድፍ ጨምሮ ሁለት እልፍ ጦር ጉራ ድረስ ሰደደ። ነገር ግን አጤ ዮሐንስ አምናውን በማረኩት በገዛ መድፉና በገዛ ሰናድሩ እንደገና ብጥልጥሉን አወጡት። የዚህን ጊዜ ካጤ ምኒልክም ሁለት ሽህ ያህል ጦር ኢጋዥ መጥቶላቸው ነበረ።

አጤ ምኒልክ ከምስር መንግሥት ጋር በመላላካቸው ሰው ባላወቀው ነገር አማ እንጂ ላገራቸው ሰው ላጤ ዮሐንስ ትተው ለባዕድ እስላም ለምስር ጦር ለማገዝ አልነበረም። ብቻ የገዛ መንግሥተዎን አላገባብ የቀማቸውን ጠላት አጤ ዮሐንስን ተወጋ በኋላ ያ የምስር ጦር ከኢትዮጵያ ግዛት ወጥቶ ምንም ሳያደርግ በመጣበት እግሩ ተመልሶ አገሩን ሊገባ ነበረ ውላቸው። በቀረውም ባጤ ምኒልክ ተመፍረድ ይልቅ ባጤ ዮሐንስ ይልቅ ሰዉ አይፈርድም ኑሯልን? ባጤ ቴዎድሮስ ጊዜ ለንግሊዝ መንግሥት እረድቶ መንገድ ጠርጎ ስንቅ ሰንቆ መሪና ሰላይ ሰጥቶ መቅደላ ድረስ እንግሊዝን መርቶ ያደረሰ ማ ኑሯል? አጤ ዮሐንስ ነበሩ። የኢትዮጵያ ቅስም የተሰበረ የቴዎድሮስ ግምባር የታጠፈ ባጤ ዮሐንስ የተነሣ ነበረ። አጤ ዮሐንስ ይሄን ማድረጋቸው ለመንግሥት ሳስተው ነበረ ያውም ባልተገባቸው፣ ካባታቸው ባልቆያቸው መንግሥት። የትግሬ ሰው አጤ ዮሐንስን ከጥንት ተመሰረት ተባለ መንግስት የተወለዱ ናቸው ይላል። ከማን ንጉሥ ተወልደው ኑሯል? የስዑል ሚካኤል የልዥ ልጅ ነበሩ ይላል የስሑል ሚካኤልስ ልጅ ቢሆኑስ

እኒኸው አጤ ኢዮአስ ደግዳጋ ንጉሥ እንደሆኑ አይተው ገነኑና ዘመን ቢአነሣቸው ጉልበት ቢሰማቸው ሸፍተው ትግሬን ገዙ እንጂ ንጉሥን ኑረዋል? ይሄን ሁሉ ጨርሶ ማወቅ ነው። የዚህን ነገር እንተወውና አሁንስ የጀመርነውን እንናገር።

አጤ ዮሐንስ ቱርክን ሁለት ጊዜ ደጋግመው ጎዳጉዲና ጉራ ላይ ተተመተሙት ወዲአ ከዚሁ ቱርክ በማረኩት መድፍና ሰናድር እንብዛ ኩራት አለልክ ተጫናቸው። እውነትም ያጤ ዮሐንስ ግርማ ከቱርክ ድል ወዲአ ነው የመጣ ይልቁንም ይልቁንም አጤ ዮሐንስ ተመፈራት የደረሱበት ከቱርክ ጦርነት በፊት ባበሻ የነበረው ነፍጥ ሁሉ ባለባሩድ ብቻ ነበረና ከቱርኩ የማረኩት ሁሉ ብረት ባፉ ትቶ በቂጡ የሚለጎም ሰናድር ስለሆነ ነው። ባበሻ ባለጥይት ጠበንጃ ተጎዳጉዲ ጦርነት በኋላ ነው የመጣ።

አጤ ዮሐንስ በዚህ ሁሉ አለቅጥ ኮሩና አጤ ምኒልክን ጨርሰው ገብር አሉ። አጤ ምኒልክ የዚያን ጊዜ የሸዋንም መርጋት የወሎንም መገዛት የሠራዊተዎንም ብዛት የትግሮችንም እምብዛ መኰራራት አዩና ወግድ ይዋጣልነ ብለው ሠራዊተዎን አስከትተው በ፲፰፻፸ዓመተ ምሕረት በመጋቢት በጌምድር ተሸገሩ። እስተ ጐንደር ድረስ ሾሙበትና በከንፈሮ አባይን ተሻግረው ጎጃም ገቡ። ፋሲካን ከባሕርዳር አጠገብ ስሉልታ ላይ ዋሉና ደብረ መይ የኋላ ምሽታቸውን ጣይቱ ብጡልን አይተው ተነጋግረው መሀል ጎጃም ሰለል ብለው ገቡ። ተጎጃም መሬት አንድም ሰው ለመዋጋት ያሰባቸው አልተገኘም። በቀረውም አጤ ምኒልክ ያደሩበት አገር ለምልሞ ያድር ነበረ እንጂ፣ ደሀ ምንም አይጎዳም ነበረ። ትግሬ ባለፈበት ግን እንዳንበጣ ልሶት ነበረ የሚአድር፤ ስለዚህ የድፍን ጎጃም ሰው ባለፉበት ሁሉ አጤ ምኒልክን እልል እያለ ተቀበለ።

በዚህ መካከል አጤ ምኒልክ ገና በጎጃም ሲዘዋወሩ ተሸዋ ክፉ ወሬ ደረሰ። ወሬውም የወይዘሮ ባፈና መክዳት የመርድ አዝማች ኃይሌም መሸፈት የመሸሻ ሰይፉም ወይዘሮ ባፈና በሱ ስም የሸዋ ሰው እንዲከዳላቸው ብለው ተታሰረበት አስፈትተውት ኑሮ መክዳት። ነገር ግን መሸሻ ሰይፉ ወይዘሮ

ባፈናን አሰረና እሱ ለራሱ ከዳ ካጤ ዮሐንስም ተላላከ። የዚህ ሁሉ ነገር ባልጐዳም ነበረ፤ ይልቁን የከበደው ነገር የወሎው ባላል ጋ መሀመድ አሊ የዛሬው ራስ ሚካኤል ከዱና ወረይሉን ዘርፈው፣ ከተማውን አቃጥለው፤ ለትግሮች ገቡ የሚሉ ወሬ ላጤ ምኒልክ ጎጃም ድረስ ደረሰ። አጤ ምኒልክ በደጀን አድርገው፣ አባይን ተሻግረው፣ ወደ ሸዋ ገሠገሱ። ነገር ግን መርድ አዝማች ኃይሌም ፊት አዛዥ ወልደ ጻድቅን ድል ታደረጉ በኋላ፣ ደጃች ገርማሜና አቶ በዳኔ ድል አድርገው ያዟቸው። መሸሻ ሰይፉንም ራስ ዳርጌ አምባውን ከበው ይዘው፤ ፊት በምክር፣ ኋላም በጉልበት አስጨንቀው ታሞን ሰብረው ይዘው ላጤ ምኒልክ አቆዩ። አጤ ምኒልክ እንደ ደረሱ ወይዘሮ ባፈናም ይማሩኝ ብለው ታረቁ። መርድ አዝማችና መሸሻ ሰይፉ ታሰሩ።

በዚህ ሁሉ ነገር አጤ ምኒልክ አዝነው፣ ተናደው ተቀምጠው ሳለ አጤ ዮሐንስ በመሀመድ አሊም ለሳቸው በመግባቱ ከሸዋ ውስጥም እንዲአ ያለ ድብልቅልቅ ነገር በመደረጉ ተደፋፈሩና፤ ይሄ ሁሉ በሆነ ዓመት ሳይሞላ በጥር ባ፲፰፻፸፩ ዓመተ ምሕረት ሸዋ መሬት ገቡ። ወደመንዝ ሲደርሱ እነበሻህ አቦየ፣ እነወልዴ አባ ሰዩም፣ እነደጃች ገርማሜ መንገድ ለመንገድ እየተዋጉ የትግሬን ጦር አሰጡት፤ የትግሬም ጦር መንቀጥቀጥ ጀመረ። የሸዋ መኳንንት ከትልቁ እስከ ትንሹ ድረስ ይዋጣልነ፣ እንዋጋ አለ። አጤ ምኒልክ ግን ልበልን፣ ልተው ሲሉ ቈዩና በመጨረሻው ከሸዋ ገና ጠላት እንደነበረብዎ አዩት ባንድ ወገንም የወሎን ባላል ጋ መክዳቱ አጐደላቸውና አለ ጊዜው መዋጋት ሆነብዎ። ይሄን ሁሉ አውጥተው አውርደው አይተው ያሰቡትን ሁሉ ተዉና ከልቸ ተነሥተው ብዙ ግብር ይዘው አጤ ዮሐንስ ከሰፈሩበት ድረስ ሄዱ። አጤ ዮሐንስም ያላቸውን ሁሉ ጦር አሰልፈው ያለውን ሁሉ መድፍና ነፍጥ ግባት አስተኵሰው አጤ ምኒልክን ተቀበሉ። አጤ ምኒልክ ገና ተፊታቸው ብቅ ሲሉ ምኒልክን ያህላል የተቻለው ጌታ የውነተኛው የኢትዮጵያ ባላል ጋ ያነን ሁሉ አሳቡን ትቶ ሲገባላቸው ባዩ ጊዜ አጤ ዮሐንስ በእንባ እየታነቁ ተቀበሉዎ። የዚያን ለት የታረቁበትም ውሉ አጤ ምኒልክ አጤ መባልዎን ሊተዉ፣ ሃይማኖተዎም ተዋህዶ ሊሆን አጤ ዮሐንስም ተበሽሎ ወዲህ፣ ያጤ ምኒልክ

ግዛት መሆኑን ሊአውቁና ታመት ግብር በቀር ከሸዋ ግዛት በምንም በምን ላይገቡ ባውሳ በኩልም የባሕር መንገድ እንዳያለሙ ነበረ። ከዚህ እርቅ በኋላ ወደጐንደር የመጋፋቱ አሳብ ሞተ፣ ቀረና አጤ ምኒልክ ዝም ብለው ግዛተዎን ወደኦሮሞ ያሰፉ ጀመረ። ድሮ ያባ ዳኘው ግዛት ወሎን እንደ እግር ሸዋን እንደ እምብርት አደረገና ግራ ክንፉን ወደ ጨርጨር ቀኝ ክንፉን ወደ ወለጋ ዘርግቶ እራሱን ወደጅማና ወደከፋ አቅንቶ ይሰፋ፣ ይንሰራፋ ጀመረ። ያባዳኘው ፈረስ ከዚህማ ወዲያ ፀሐይ አይጠመርረው በረሀ አያልበው ቁልቍለት አይደክመው፣ አቀበት አይገታው፤ እንዲአው ይረብ፣ እንዲአው ይነጕድ፤ መሬት አይብቃኝ ሜዳው ጠበበኝ ይል ያልፍ ይሄድ ጀመረ። ድሮ ያጤ ዮሐንስ ግዛት ባባዳኘው ግዛት አይነት አንድ ጕልት መሰለና ቀረ። ይሄ ሁሉ ሲሆን ያባ ዳኘው አሳብ ሌላ ነበረ። ነገሩ ገና እንደ ተጀመረ እንጂ በዚህ እንዳይቀር ያውቅ ነበረ። አባ ዳኘው የዚያን ጊዜ ጀምሮ ዛሬ የሚገዛውን ሁሉ በጁ ጭብጥ፣ በግሩ እርግጥ አድርጎ ይዞት ነበረ። ዳግማዊ ምኒልክ የዚያን ጊዜ ጀምሮ ፈረሱ ከህንድ ባሕር ጀምሮ እስከ ሱዳን ድረስ እየጋጠ ጥማቱን ተነጩ አባይና ከቢቶሪአ ባሕር እንዲአበርድ ከኤርትራ ባሕር እንዲዋኝ ያውቀው ነበረ።

ዳግማዊ ምኒልክ የዚህ ሁሉ አሳብ፣ የዚህ ሁሉ ጎንፃ በልበዎ ሳለ ከንግግረዎ ኩራት ካፊዎ ስሕተት አይገባበትም ነበረ። እንዲአው በትዕግስት እንዲአው በደግነት ላጤ ዮሐንስ የሚሰጡት ግብር የብርና የወርቁ፣ የፈረሱና የበቅሎው፣ የድልቡ፣ የሽህሩ፣ የመጣምሩና የጣፋው ነገር ቁጥር ስፍሩ አይታወቅም ነበረ። ነገር ግን በዚህ ልገሳዎ ቁጥር ቀናተኛና ምቀኛ ጠላት ነበረበዎ። በያመቱ በየወሩ በየጊዜው የሸዋው ንጉሥ ሸፈተ ዘንድሮ እርግጥ ይዋጋናል እያለ አጤ ዮሐንስን ሲአባባና ሲአባንን ይኖር ነበረ። ዳግማዊ ምኒልክ ግን ይሄን ሁሉ ቁም ነገር ሳይሉ ይሄን ወሬ ለሚአወራብዎ ለነበረው ምቀኛዎ ሁሉ እንደ መልካም አድራጊ ዓይነዎ ሳይገመግም እጀዎ ሳይቈጥር ወርቁን፣ ብሩን፣ ፈረሱን፣ በቅሎውን ይሰጡት ያጠግቡት ነበረ። የትግሬ ሰፈር አለ ምኒልክ ጐኑ አይቀናም ነበረ። በመጀመሪአ የትግሬ ሰው ቆዳ ሸዌ እያለ

ሲሳደብ ይኖር ነበረ ኋላ ግን አለ ምኒልክ የተጣጋው ጐኑ እንዳይጠረቃ ባየው ጊዜ ለምለሙ ሸዌ መጣ ይል ጀመረ።

ተዚህ ቀጥሎ የትግሬ ሰው የበጌምድርን ሲሳይ ምጥጥ አርጎ አራግፈና፣ እንኳን በጥርሱ የሚነክሰው ሥጋ ባፉ የሚጐርሰው እንጀራ በምላሱ የሚልሰው ሙቅ እንኳ አጥቶ ሌትና ቀን ተኩምቱ ጋራ ሲጫወት ሲአድር፤ የሸዋ ድልብ፣ የሸዋ ሽህር፣ የሸዋ ሲሳይ በደረሰለት ጊዜ፣ የትግሬ ሰፈር በዘፈን ደምቆ ያድር ነበረ። ቀጥሎም የሸዋ ሲሳይ እንዲህ የወር መንገድ ገሥግሶ መጥቶ ሲአጠግበነ ከዚአ ከስፍራውስ ብንሄድ እንዴት ያልፍልነ፡- እያለ የትግሬ ሰው ሌት በጨለማ ቀን በደመና እየከዳ ሸዋ መግባት ጀመረ። ድሮ ያጤ ዮሐንስ ሰፈር ሳል እንደያዘው ድመት እየመነመነ ሲሄድ፣ ያባ ዳኘው ከተማ እየሰፋ ስፍራ እየጠበበው ተግርማ ግርማ እየጨመረ ያድር ጀመረ። አጤ ዮሐንስ በዚህ ተደናገጡና ሰው እየከዳቸው እንዳይሄ በየበሩ ያስጠብቁ ጀመረ። ነገር ግን ምን ሊሆን? ማን አግቶ ሊአስቀረው? ችጋር ያባረረው ትግሬ፣ ባሩድ የሸተተው አውሬ አንድ ናቸው፤ እንደ ቡኸር በሄትም እየዘለለ ሸዋ ለመግባት አልቦዝን አለ።

## የምባቦ ጦርነት

ይሄ ሁሉ ሲሆን የምኒልክ አሽከር፣ የምኒልክ ቀኝ ክንድ ጉበና አባ ዳቂ መቸም ፈረሱ አንቅፋት አይመታው፣ ልጓም አይገታው፤ ባክንፍ እንጂ ባራት እግር የሚሄድ አይመስል ነበር፣ እንዲአው አሮሞ ደም እየጠማው ግቤን ተሻግሮ ሌቃን መዛብሮ በወለጋ ሜዳ አፍንጫውን ነፍቶ፣ እንደተቆጣ አንበሳ ዓይኑን እያጉረጠረጠ፣ በግሩ እየደነፋ ወዲህና ወዲህ ሲፏልል የጎጃም ጦር ብቅ አለና፣ እንቅፋት ሆነው። ጎጃሜ በጠቦ ደረሶ እግር ታዝዞ ነበረ። ከዚህ ወዲአ ራስ ጉበናም የኔ ነው፤ ራስ ደረሶም የኔ ነው ሲሉ ባገር ተጣሉ። ነገር ግን መዋጋቱን ትተው ሁሉም እየጌቶቻቸው ላኩ።

ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ባለማወቃቸው የሸዋ ጦር በፈረስና በብዛት ነው እንጂ ለተኩስ አልተፈጠረም ሲሉ ሰምተው እውነት መስሏቸው አንዋጋ ብለው ላጤ ምኒልክ ላኩ። ያላላኩቸውም ነገር እጅግ የሚገርም የሚደም፣ ለሰሚው እውነት የማይመስል ነበረ። ያንኑ ቃል በደብዳቤ ትተው በቃል ላኩት። ቃሉም እንዲህ ነበረ፣ በደብዳቤ ብልከው ለብቻህ አይተህ ቀዳደህ ትጥለዋለህ፤ በቃል የሆነ እንደሆነ ሁሉ ይሰማዋልና በግድ ትዋጋኛለህ ብየ ነው፤ አሁንም ተጠራ ሜዳ እንገናኝ፣ ይዋጣልነ ይል ነበረ። አጤ ምኒልክ ቃሉን ተመኳንንቶቻቸው ጋር ሰምተው ነገሩ እውነት አልመስለዎ አለና እንዲህ ያለ ቃል ደፍሮ ተክለ ሃይማኖት ሊልክብነ? አብዶ እንደሆነ እንጂ እንዲህ ያለ ቃል ደፍሮ አላቅሙ አይልክም አሉና ተመልክተኞቹ እውነቱ እስቲታወቅ ድረስ አንዱን አስረው አንዱን ለቀው ሂድ ተቻልኸኝ እሺ መጣሁ በለው ብለው ላኩት። ወዲአውም በበነጊአው ወደጦርነቱ ተጓዙ።

በግንቦት ባ፲፰፻፸፬ ዓመተ ምሕረት ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ቀድመው እምባቦ ላይ ስፍራ መርጠው ተሰልፈው ቆዩ። ሰልፋቸውም ሸዋን በፈረስ አንችለውምና፣ አንድ ሰው በፈረስ አይውጣ ብለው አዝዘው ነበረ። ብልሀቱ የጎጃም ሰው በግር አምልጠን ላናመልጥ ጠንክረን እንዋጋ ብሎ ጨክኖ እንዲዋጋ ነበረ። አጤ ምኒልክ ደግሞ አንድ ጎጃሜ እንዳያመልጥህ ከበህ ጠብቅ ታላዘዝሁህ በቀር ምንም አትዋጋ ዙሪአውን ከበህ ተመልከት ብለው ለራስ ጉበና አዘዙ። ከዚህ ወዲያ አጤ ምኒልክ ወደጎጃሜው ሰልፍ ይጓዙ ጀመረ። ከሁለቱ ንጉሦች መካከል ከዘባጣው ላይ ዱር ነበረ። የሸዋ ጦር አገር ምድሩን እያላበሰ ብቅ ባለ ጊዜ ጎጃሜ መድፉን ይለቀው ጀመረ። አጤ ምኒልክ ግን ዝም ብለህ ተጓዝ፣ ተኵስ ሳልልህ ምንም አትተኩስ አሉና ተመሀል ሁነው ዱሩ አላሻግር ቢል በጐራዴ እያስመነጠሩ ነጋሪቱ ድምጡ እስቲሰል እየተጐሰመ፣ ቀንዳ መለኸቱ ጉረሮው እስቲሰነጠቅ እያከላላ ፊት ለፊት ተጓዙ። ጎጃሜ እየተኰሰ ሰው መፍጀት ተጀመረ ብዙ ጊዜው ነበረ። በጣም እንደተቃረቡ ባዩት ጊዜ አጤ ምኒልክ እንግዴህ በለው አሉና አዘዙ። ከዚህ ወዲያ ተኵሱ ሰማይና ምድር ያናውጥ ጀመረ። ነገር ግን ጎጃሜ ተመሀል ቁጥር

ብሎ ተቋጥሮ ሲዋጋ ነፍሱን የተበደራት እንጂ የገዛ እራሱም አትመስለው ነበረ። እንዲአው ዓይኑን እየጨፈነ እየገባ የሩቁን በነፍጥ፣ የቅርቡን ባፋ እያመሸከ በሾተሉ እየጠበዘዘ እየጣለ ፊታውራሪውን ሸሮ ወዳባት ነፍጠኛው ተጋባ ቀጥሎም መሀል ለመሀል እየተሸበለበለ አጤ ምኒልክ ወደነበሩበት ወደገዳሙ ተቃረበ። በዚህ ጊዜ ጦሩ እንደጠመረረ አዩና አጤ ምኒልክ ካጠገብዎ የነበረውን ዘበኛን ሰናድር ያዢን ባሩድ ቤትን ባለሚልን ተመሬት ተለሸለሸ ብለው አዘዙ። እርሰዎ ግን ጠጣውን አምጣ ብለው ጠጣው በሚባል ፈረሰዎ ወጡ። ነገር ግን የወጡበት ፈረስ ታንገቱ ላይ አንዲት አረር ነደፈችና ጣለችው፤ ሞተ። አባ ዳኘው በሌላ ፈረስ ወጣ እንደገና ያም ፈረስ ባረር ቈሰለ። ጃን ጥላ ያዡ አጤ ምኒልክን በጥላው ምልክት ተኵሶ ጎጃሜ እንዳይገልዎ ብሎ ጃን ጥላውን እጥፍ አደረገ። አጤ ምኒልክ ግን ተቈጡና፣ የኔ ጥላ አይታጠፍምና ቶሎ ዘርጋ ብለው ጃን ጥላው እንደገና ተገተረ። ያን ጃን ጥላ አየና ጎጃሜ በንጉሥ ተክለ ሃይማኖት እግር ታዝዞ መሀል ለመሀል ተሸበልብሎ እየፈከረ ያ ተምድር የተለሸለሸው ባሩድ ቤትና ሰናድር ያዥ ዘበኛ ባለሚል ጋሻ ጃግሬ ገበታ አቃፊ አስታጣቢ ሁሉ የሞተ መስሎት እያወከ አጤ ምኒልክን ለመያዝ ተቃረበ። አጤ ምኒልክ በዚህ ጊዜ እንዳለህ ሳትነሳ በሰናድር እግር እግሩን በለው አሉና አዘዙ። ከዚህ ወዲአ ዘበኛ እንደ ኤሊ አንገቱን ወደምድር ቀብሮ የነበረው አንገቱን ብቻ ቀና እያደረገ ተኵሱን ለቀቀው። ከዚህማ ወዲያ ምን ይሆናላ ጎጃሜ ያ ሁሉ ተማች፣ ያ ሁሉ ወዘላ ጐበዝ፣ ያ ሁሉ ወጣት ሽልሚ እግር እግሩን ተሰንክሎ፣ ተሰንክሎ በረዶና ወጀቦ ተጋግዞ ያበላሸው ገብስ ዝርዝር መሰለ። እንዲአ ባላገደዳቸው ነገር ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት አላቅማቸው ጉልበት ተሰምቷቸው ተጠናቅለው የጎጃምን እናት፣ የጎጃምን አባት፣ የጎጃምን ሙሽራ ፊቱን አስነጩት፣ ጠጉሩን አስቆረጡት፣ ማቅ አስለበሱት። በምባቦ ጦር እስንት ሙሽራ በሏን አጣች፣ እስንት እናት አባት ደገፋቸውን ጧሪአቸውን አጡት፣ የስንቱ ጋሻ ተሰበረ፣ እስንት ጐጃሜ ምሾ አወጣች፣ እስንቱ ተፋጀ፣ እስንቱ አለቀሰ። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም ከዚያም ላይ ከብዙ ስፍራ ቆስለው ተያዙ። ወዲያው ተይዘው ካጤ ምኒልክ

ፊት እንደ ደረሱ፣ ያነን የመሰለ ጀግና የጎጃም ጌታ አድርጎት የማያውቅን እየተንቀጠቀጠ ይማሩኝ ብሎ ተግር ወደቀ።

አጤ ምኒልክ ግን እንኳን ቂም ይይዙባቸው፤ አይዞህ ምንም አላደርግህ፣ ተነሥና ሳመኝ ብለው ዝቅ ብለው ደግፈው አንሥተው ሁለቱ ተሳሳሙ። አጤ ምኒልክ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ከብዙ ላይ ቈስለው ባዩ ጊዜ አዝነው በንጉሥ እጀዎ እንደ ወጌሳ አረሩን ፈልፍለው አውጥተው፣ ቍስሉን በዶሮ ላባ እያጠቡ መድኃኒት እያደረጉ አዳኑ።

የምባቦ ለት ተጎጃሞች አባ ወልደ ጊዮርጊስ፣ የዛሬው አፄጌ ወልደ ጊዮርጊስ፤ ፊታውራሪ ስዩም፣ የዛሬው ደጃች ስዩም እራስ ደረሶ ግሩም አድርገው ተዋጉ። ከሸዋ ሰራዊት ደግሞ ወሌ ብጡልና ወሎየ በወይዘሮ መስተሀት እግር አሳምረው ተዋጉ። የእምባቦ ጦርነት ነገር ባጭሩ አደረግሁት እንጂ ብዙ ነበረ። ከድሉ በኋላ አጤ ምኒልክና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ሲጨዋወቱ አጤ ምኒልክ፣ ኧረ በል ተክለ ሃይማኖት አንተ ድል አድርገኸኝ ቢሆን ምን ታደርገኝ ኑረሀል፡- ብለው ቢጠይቁ፣ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት እውነቱን ልናገረው፣ እኔ ድል አድርጌ ቢሆን ቶሎ አስገድለዎ ነበር አሉ። ነገሩም በሳቅ ተከተተ።

## አጤ ዮሐንስ ወደሸዋ።

አጤ ዮሐንስ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ድል ሁኖ መያዝና ያጤ ምኒልክን ድል ማረግ በሰሙ ጊዜ እጅግ ተደናገጡ፤ የትግሬም ጦር ተሸበረ። የዚህ ወሬ ላጤ ዮሐንስ የደረሰላቸው ትግሬ ባጅተው በጌምድር ለመክረም ሰኔ እንደባተ ደብረታቦር የገቡ ዕለት አርብ ቀን ወደማታው ነበረ። ገና ተልፍኛቸው ሊገቡ ተበቅሎ ሲወርዱ ወሬው ደረሰና ጓዙ ሁሉ ከሰፈሩ ሳይደርስ፣ ወደሸዋ መንገድ ይጓዝ ብለው አስለፈፉ። ጉዞው ሁሉ የሸዋን ዘመቻ በሰማ ጊዜ በሽብር ተደባለቀ። አጤ ዮሐንስም ቅዳሜ ማለዳ ተጓዙ፣ ደረሱና አደሩ። ከዚህ በኋላ የትግሬ ሰው ተጨንቆ አፍ መውጫውም

አሞራው ሸዌ ፊት ጎጃሜን ድል ተመታ፣ እኛንም በተሳለ ጉልበቱ ይደግመናል ማለት ብቻ ሆነ። አጤ ዮሐንስ ገሥግሰው ከሸዋ ግዛት እንደደረሱ መሸሻ ሰይፉን ከታሰረበት ፈቱና ምኒልክ የሸፈተ እንደሆነ በሸዋ መሸሻን ሹሜ እሰዳለሁ ብለው ላጤ ምኒልክ ማንገራገሪአ አደረጉ። ነገር ግን አጤ ምኒልክ የምዋጋበት ጊዜ ዛሬም አይደለ በጣም ልሰናዳ ብለው ሳይሸፍቱ የጎጃምን ሁሉ ምርኮ እስከ ንጉሡ ይዘው ካጤ ዮሐንስ ደረሱ። አጤ ዮሐንስም የምኒልክ ነገር አሳቡ እንደ መርግ ተጭኖ ይዟቸው የነበረ ደስ አላቸውና፣ ስለምን ተዋጋችሁ? ብለው ጠየቁ። አጤ ምኒልክና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም የተዋጉበትን ነገር ቀኝና ግራ ተቋቁመው ተናገሩ። አፄ ዮሐንስ ግን ምንም በምኒልክ በደል ባይገኝ ምክንያት አድርገው ሲመኙት የነበረን አገር ወሎን ካጤ ምኒልክ ቀምተው ለራስ ሚካኤልና ለራስ አራያ ሥላሴ ለልዣቸው ተሁለት አካፍለው ሰጡ። ተንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም አገው ምድርን ቀምተው ለራስ አሉላ ሰጡ። ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ግን እምባቦ የተማረከው ሁሉ ነፍጥ ተመለሰላቸውና ወደጎጃም ተመለሱ።

ይሄ ከሆነ ከጥቂት ቀን በኋላ አጤ ዮሐንስ ያጤ ምኒልክን ልብ ለመያዝ ልዥህን ለልዤ ስጥልኝ ብለው ለምነው፣ ወይዘሮ ዘውዲቱን ለራስ አራያ ሥላሴ ባ፲፰፻፸፭ ዓመተ ምሕረት አጋቡ። የዚያን ጊዜ ወይዘሮ ዘውዲቱ ፲ ዓመት አልሞላቸውም ነበረ፤ ራስ አራያ ሥላሴም ገና ፲፪ ዓመት አልሆናቸውም ነበረ።

# አጤ ምኒልክና ጣይቱ ብጡል።

አጤ ምኒልክ እስከዚህ ቀን ድረስ ከተመኙት ሁሉ ሁለት ነገር ብቻ ነው ይቀራቸው የነበረ። አንዱ ገና ያጤ ቴዎድሮስ እስር ሁነው ሳሉ ከልዥነት ጀምረው ይመኟት የነበረን ጣይቱ ብጡልን ለማግባት፤ አንዱ ደግሞ በውነተኛው ባያት በቅድመ አያትዎ በንጉሠ ነገሥቱ አልጋ ለመቀመጥና የተገባዎን የሰሎሞንን ዘውድ በራሰዎ ለመጫን ነበረ። ከነዚህ ከሁለቱ ምኞቶቻቸውም አንዱ ይሄው ደረሰ። ከልዠነት ጀምረው ሲመኟት እንደ ህልም ሲአልሟት ትኖር የነበረችው ጣይቱ ብጡል ባ፲፰፻፸፭ ዓመተ ምሕረት ደብረ ብርሃን ገባች፣ ንግስተ ሸዋ ሆነች፤ ወዲያው የፋሲካ ለት አንኮበር መድኃኔ ዓለም ቈርበው ሁለቱ ተጋቡ። የሸዋ ቤተመንግሥት ዓለሙ የዚህን ቀን ተጀመረ። የሸዋ ቆሌ፣ የሸዋ ደስታ፣ የዚህን ቀን ተጀመረ። የሸዋ ቤተ መንግሥት ከጣይቱ ወዲያ ወቃቢ ገባው ግርማና ውበት ተጫነው፣ ጥላው ከበደ፣ የውነተኛው አዶኛ የውነተኛው ደስታ ከጣይቱ ብጡል ጋራ ገባ። የውነተኛውን ነገር ልናገረው፣ በወይዘሮ ባፈና ጊዜ የነበረው ክፉ ስም ከቤተ መንግሥቱ ጠፋ። ፀሐይቱ ለማለት ጣይቱ ተባለች፣ ነገር ግን ከጣይቱ፣ እጣይቱ ለመባል ይገባታል። እንደ እውነትም ጣይቱ ብጡል ተገባች ያባ ዳኘው መንግሥት ወድያው እያደረ ሰፋ ተሳፋ፣ ገነነ ተጋነነ፣ ተሞገሥ ሞገሥ ተግርማ ግርማ ጨመረ። ወይዘሮ ባፈና ያጤ ምኒልክን መንግሥት ለማፍረስ ሲጥሩ ሲሸፍቱ ስም ሲሰብሩ ይኖሩ ነበረ። ጣይቱ ብጡል ግና የምኒልክን አልጋ በምክር ስትደግፍ በጉልበት ስታጠና ኖረች፣ ትኖራለች። በጉልበት ማለቴ ወሴን ያህላል የታመነ ሃይማኖቱ ተጅማት ጉልበቱ ተብረት የጠና ከጥንት ጀምሮ ሳይለወጥ የምኒልክን አልጋ ሲደግፍ፣ የምኒልክን እድሜ ሲጠብቅ ኖረ፣ ይኖራል። ጣይቱ ብጡል እንደ ሌሎች ሁሉ ንግሥቶች አይደለችም፤ የመከረችው አገር የሚአሳድር፣ የተናገረችው ከምድር ጠብ የማይል፣ ለባሏ መልካም ደገፋ፣ ለኢትዮጵያ ጋሻ ናት። በዚህ የተነሣ በኤውሮፓ ለምን ላገሯ ጣረች፣ ለምን ለገዛ መንግሥቷ አሰበች ብሎ እንደ

ማመስገን ሁሉ ጠላት ለፈፋት። ኢትዮጵያ ግን የጣይቱን ወረታ አታጠፋም፣ አታጥፋ፤ ብልህ ይመርቃት፣ የተረገመ ይጥላት።

## አረርጌ።

ያባ ዳኘው ፈረስ የጉበናን ፈረስ መንገድ መሪ አድርጎ ይሄድ ይጓዝ፣ መሬት ጠበበኝ ይል ጀመረ። ያባ ዳኛው ፈረስ ደንበርና ወሰን ተፊቴ አልይ አለ። ሁሉንም እየደመሰሰ ደንበሩን እያፈረሰ እስላሙን ታማራው ጉራጌውን ተስልጤው ኦሮሞውን ከሻንቅላው አጋባው፣ አዛመደው፤ እያዋሀደ ባንድ እንዲበላ ባንድ ስም እንዲገዛ አደረገው። ከጠራና ከደብረ ብርሃን ከጅሩ በመለስ አንድ ክርስቲያን ትርው ብሎ አይደርስበት የነበረ ድሮ ሁሉን ሰጥ አድርጎ ገዛና እሴት በንቅብ ወርቅ ተሸከማ፣ ተንጦጦ ወለጋ፣ ተወለጋ ከፋ ሌት ተቀን ብትጓዝ ብትንከራተት ምንም እንዳይነካት አደረገ። ቀጥሎ ፊቱን ወደጨርጨር መለሰ። ያባ ዳኘው ፈረስ አራት ዓይን ነበረው፤ ባራት ዓይኑ አራቱን ማዝን እያስተዋለ ጭራው ተወሎ እስከሸዋ ሳለ የኋላ እግሩ፣ እንጦጦ የፊት እግሩ፣ ቀኙ ከፋን፣ ግራው እግሩ ጨርጨርን ረገጠ። ያባ ዳኘው ፈረስ የሚደርስበትን እንጂ የደረሰበትን አያይም ሆነ። ከፋ ላይ ሲደርስ ወላሞ ፋሾዳ ቁልጭ ብሎ ይታየው ነበረ። ጨርጨር ሲደርስ ያረርጌ ከተማ፣ የወጋደን መንደር ፍንትው ብሎ ይታየው ነበረ። የምኒልክ ነገር እንዴት ብሎ ባፍ ተተርኮ በብር ተጽፎ ያልቃል፤ የዳግማዊ ምኒልክ ነገር እንዲአው ግሩም ነው፣ የግሩም ግሩም።

ደጃች ወልደ ገብርኤል በረኸትን ሲገዙ ሳለ አቈልቍለው ባዩ ጊዜ የከረዩ ጋላ እስከ አዋሽ ድረስ ይታያቸው ጀመረና ላጤ ምኒልክ ልሂድበት ብለው ለመኑ። አጤ ምኒልክ ግን ያዩት የነበረ አረርጌን ነበረና፣ ምን ከረዩ ብቻ፣ ሂድ ጨርጨር ግባ ብለው ደጃች ወልደ ገብርኤልን ብዙ ጐንደሬ ጨምረው መንገድ ጠራጊ ለማረግ ጨርጨር ሰደዱ። ይሄ የሆነ በ፲፰፻፸፫ ዓመተ ምሕረት ነበረ። ደጃች ወልደ ገብርኤል እስከ ቦሰና ድረስ ጋለቡና ብዙ ጋላ

ፈጁ። ያረርጌ ንጉሥ ከዚህ ወዲአ ገፉና ወደ ደጃች ወልደ ገብርኤል ጦር ሰደደ። የሁለቱም ወገን ተጐነጫጨፈ። የዚያን ጊዜ ደጃች ወልደ ገብርኤል ተተኵሶ የወደቀ ሁለት የመድፍ አረር ወደ አፄ ምኒልክ ሰደዱ። አጤ ምኒልክ እኔ እመጣለሁና ሰው በከንቱ እንዳታስፈጅ፣ ወደኋላህ እንጂ ወደፊት አትግፋ ብለው ላኩ። ወዲያው አጤ ምኒልክ ፈረሴን ጫን አሉ፣ ተጓዙ። ኢቴጌ ጣይቱ የዚያን ጊዜ ገና ወይዘሮ ጣይቱ ይባሉ ነበር፣ እንጦጦ ቀሩ። የዚያን ጊዜ አዲስ አበባ ገና ስሙ ያልታወቀ የቆማጣ መሰብሰቢአ ነበረ። አጤ ምኒልክ ሁለት ሶስት ጠማማ ሰቀላ መሳይ ብቻ አስቁመውበት ነበረ።

አጤ ምኒልክ ተጓዙና ወደ ሸለንቆት ወራቢሌ ላይ የልደት ገሀድ ደረሱ። ወዲያው የልደት ገሀድ ያረርጌ ጦር ከሸዋ ፊታውራሪ ጋራ ተጫጫረና አደረ። የልደት ለት ገና ሲነጋጋ ወይ ድፍረት ወይ አለማወቅ! ያረርጌ ንጉሥ ያን ግንድ ግንድ የሚአካክል አሮጌ መድፉን ግም ግም ያደርግ ጀመረ። አጤ ምኒልክ የሚመክትልኝ መስሏቸው ለመዋጋት ከድንኳነዎ ይሸላለሙ ጀመረ። ነገር ግን ገና የሸዋ ጦር ተሰልፎ ሳይጨርስ ወደ ፊት ቀድሞ ከሄደው ጦር ጋራ ተወጋጋና ድል ሁኖ መድፉን ሁሉ እንደ ግንድ አጋድሞ ጥሎ ያረርጌ ጌታ አብድላሂ ተጥቂት ፈረሰኛ ጋራ ጋልቦ ሸሸ። የቀረው ጦሩ ግን ከዚያው ላይ እርግፍ አለና ቀረ፣ የተማረከውም ተማረከ። አጤ ምኒልክም ወዲያው ተከትለው አረርጌ ገቡና፣ ያለውን ሁሉ ሲሳይ ልቅምቅም አድርገው፤ ውሻውና ርግቡም አልቀራቸው ሁሉንም ያዙ። የምስራቹን ወዲያው ለእቴጌ ጣይቱና ላጤ ዮሐንስ ሸዋ ለቀሩት ሁሉ መኳንንትም ለናዛዥ ወልደ ጻድቅ ላኩ። ባረርጌ ግን ከባላምባራስነት ደጃዝማች አሰኝተው ደጃች መኮንን ሾሙ። ካረርጌ ሳይነሱ በፊት አጤ ምኒልክ የጎንደሬን ሁሉ ጦር ከደጃች መኰንንን ሾሙ። ካረርጌ ሳይነሡ በፊት አጤ ምኒልክ የጐንደሬን ሁሉ ጦር ከደጃት መኰንን ጋራ እንዲቀር አደረጉ፤ ቀጥለውም ባዋጅ ከመኰንን ጋራ አረርጌ መቅረት የወደድህ ሁሉ ፈቅጀልሀለሁ ቅር አሉና አዋጅ ነገሩ። ድሮ የደጃች መኰንን ጦር ያንድ ንጉሥ ጦር አከለ። ይሄን ሁሉ ታሳማሩ በኋላ አጤ ምኒልክ ወደ

አሩሲ አቀኑ። አሩሲ ገና ጨርሶ አልገባም ነበረና እህሉን ዘርፈው ተምሽጉ አግብተው ለራስ ዳርጌ ጦር ቀለብ ትተው ወደ እንጦጦ ተጓዙ።

ያረርጌ መያዝ የምስራቹ እንጦጦ በደረሰ ጊዜ ድሉ መቸም የልደት ዕለት ነበረና እቴጌ ጣይቱ እንዲህ ብለው ገጠሙ፤ የሚጓዘው ሰንጋ የተነዳው ሽህር ለልደት ባይደርሥ፣ እስላም አርደው ዋሉ የሸዋው ንጉሥ። ባንድ ወገን ደግሞ ውሀ በል ገምቦኛ በጀርባዋ ጠጅ፣ በልቧ ደስታ እየፈላባት አጤ ምኒልክ ታረርጌ ብዙ ነጫጭ ርግብ በቀፎ አስደርገው ትልልቅ ዝንጕርጕር ውሻ አሲዘው ሲጓዙ አየችና፤ የምኒልክ ነገር ኧኸን ኧኸ ይመስለኛል ተረት፣ ኧኸን ኧኸ አሞራው በቀፎ ውሻው በሰንሰለት! እያለች እያሸበሸበች እንጦጦ ደረሰች። እንዲህ ታረርጌ ወዲያ ለሸዋ መንግሥት ታለም ላይ ዓለም ተጨመረ። እውነትም የምኒልክ ነገር ተረት ይመስላል እንጂ ባፍ ተናግሮ በጆሮ ሰምቶ በልብ አድንቆ የሚርጨሱት ነገር አይደለም። ከጣይቱ ብጡል በቀር አንድ በምክር የሚአግዝ ተመኳንንቱ ሳያገኝ ባንድ ንጉሥ ልብ ይሄ ሁሉ ታስቦ ለመደረግ የሚቻል አልነበረም። የምኒልክ ነገር እጹብ ድንቅ ነው። መኳንንቱ ከራሱ እስከ ቢትወደዱ፣ ከባላምባራሱ እስከ የሻለቃው፣ ተወታደሩ እስከ ጋሻ ጃግሬው ዘመቻ ሲሉት ጕራዴውን መሳል፣ ፈረሱን ማጠጠር፣ ጠበንጃውን መወልወል፤ ተነሥም ሲሉት ለውሻ የሥጋ ክምር የርጎ ባሕር አለ ቢሉት ወዴት ነው ሳይል እንደሮጠ ለመዝረፍ ከብት ለመንዳት ተልዠ እስከ አሮጌው ለመፍጀት፣ ተቆንጀው እስከ ባልቴቱ አጋፎ ለባርነት ለማምጣት ይቸኵል ነበር እንጂ ለጌታው አንድ በምክር የሚአግዝ አልነበረም። ምኒልክ ግን ልቡ ባሕር ነው፣ ልቡ ብርሃን ነው ከተመኘውና ታሰበው ሁሉ አንድ አልቀረም፤ ይሄ ባንድ በምኒልክ አሳብ ተደረገ። ዳግማዊ ምኒልክ ብቻ አስቦ ያደረገውን ነገር በኤውሮፓ እልፍ የተማረ ብልህ ተካፍሎ እየረድፉ የንግዱን በንግድ፣ የርሻውን በርሻው፣ የትምርቱን፣ የጥበቡን የፍርዱን፣ የመንገዱን፣ የሠራዊቱን የዚህን ሁሉ ነገር ተከፋፍሎ ለመስራት ያቃቅታል፤ ያስቸግራል። ዳግማዊ ምኒልክ ግን ለብቻዎ ሁነው ይበልጠውን ወገን ጨርሰው አደረጉት የቀረውንም የኢትዮጵያ ረድኤት ቢአሰነብተዎ ያደርጉታል።

አጤ ምኒልክ አረርጌ ዘምተው ሳለ ኢቴጌ ጣይቱ ለጥቂት ቀን አዲስ አበባ ወርደው ተቀምጠው ሳለ፣ ያረርጌ መያዝ የምስራች መጣላቸውና እንግዴህ ይሄን ስፍራ አዲስ አበባ እንበለው አሉ። እስከዚህ ቀን ድረስ አዲስ አበባ በኦሮሞ ስሙ ፍንፍኒ፤ ባማራ ስሙ ፍል ውሀ ይባል ነበረ። ለቡሆ የተጣደ ውሀ ይመስል ፍል ውሀ ሲባል ለነበረው አንድ ገጠር ኢቴጌ ጣይቱ አዲስ አበባ ብለው የማይሞት የማያረጅ የማይረሳ ስም አወጡለት። በምንቸት እንደተጣደ ሁሉ ፍል ውሀ ሲባል የነበር የቆማጣ መደበር አንድ ገጠር በጣይቱ ብጡል ቃል እንዲህ ተቀድሶ አዲስ አበባ ተብሎ ፀሐይ ባየው ዓለም ይታወቅ ዘንድ ማን አስቦት ነበር? ግሩም ነው፣ ግሩም የግሩም ግሩም።

ይሄ ሁሉ ሲሆን ባረርጌም መገዛት በጋላም እስተ ከፋ ድረስ ሰጥ ብሎ መገዛቱ ለዳግማዊ ምኒልክ ገና ከልበዎ አልደረሰም ነበረ። ያባ ዳኘው አሳብ ገና እሩቅ ነበረ። እስከዚህ ድረስ አባ ዳኘው በፈረስ ሶስቱን ማዝን ጋለበ ጋለበና፣ አራተኛው ማዝን ቀረው። ያባ ዳኘው ፈረስ ተሸዋ ተነሥቶ በጭራው ወሎን እየነካ ባንድ ወገን አዳልን አረርጌን ባንድ ወገን አሩሲን ከፋን ባንድ ወገን ወለጋን ሻንቅላን ረገጠ። ከዚህ በኋላ ያባ ዳኘው ፈረስ ፈረስነቱን ንቆ አንበሳ መሆኑን ጨርሶ ወደደ። ይሄ አንበሳ ወደፊቱ የሚአይ እየመሰለ ወደኋላው ይመለከት ጀመረ። ይሄ የሰሎሞን አንበሳ ድሮ ፊቱን ወደ ትግሬ፣ ወደ ጐንደር ቀና ማድረግ ጀመረ። ለዚህ የውነተኛ አንበሳ ያረርጌ ሰንጋ የኦሮሞ ድልብ የሸዋ ሽህር ሰለቸውና የትግሬን ያንበሳ ለምድ የለበሰ በሬ መስበር ወደደ።

## ኢትዮጵያና የዳግማዊ ምኒልክ ንግር።

ድፍን ኢትዮጵያ በትግሬ ጥፍር ገብታ መቸም ተጨንቃለች፣ ታለቅሳለች፤ መከራዋን ታያለች። ብልሀቱ አይታወቅም፤ ገና ከዚህ ሁሉ በፊት የሸዋው ምኒልክ በኢትዮጵያ ሰባት አመት ይነግሣል የሚሉት ንግር ነበረ። ሰባት ዓመት ይነግሣል ማለቱ 'ት' ተሳስታ አለስፍራዋ ገብታ ነው እንጂ፣ ንግሩ

ሰባ ዓመት ለማለት ይሆናል። ይሁን እንዲሆን ያድርገው እግዚአብሔር። ሰው ሁሉ የዚህን ንግር ያውቀው ነበረ፣ ያልሰማው በኢትዮጵያ አንድም ሰው አልነበረ። በዚህ የተነሣ ብዙ ሰው ካጤ ዮሐንስ እየከዳ ወደ ሸዋ ይሄድ ነበረ። በዚህ ንግር የተነሣ ምኒልክ መቸ በነገሠልነና ይሄ አንበጣ ትግሬ በጠፋልነ እያለ የማይመኝ ሰው በኢትዮጵያ አልነበረም። አጤ ምኒልክ ይሄን ሁሉ የደኅ ምኞት እንደሰሙ ሁሉ፣ አይዞህ መጣሁልህ፣ መጣሁልህ! የሚሉ መስለው ባውሳም በተጕሪም በሄትም በሄት መድፉን ሰናድሩን ጥይቱን ያስገዙ ይሰበስቡ ጀመረ። ቀጥለውም ከኢጣልያ መንግሥት ጋር ውስጥ ለውስጥ ተዋዋሉ። ውሉ አጤ ምኒልክ፣ አጤ ዮሐንስን ወግተው በተገባዎ መንግሥት ሊቆሙ ለኢጣሊያ መንግሥትም በመሳሪአ ስላገዘ ተምጥዋ በላይ ጥቂት ታብራጃው አገር አስመራን ሊሰጡ፣ ኢጣልያ ግን ከተቀበለው ሌላ ተሻግሮ መሬት ለመያዝ እንዳያምረው፣ ፍቅር እንዲሰፋ፣ ንግድ እንዲለማ ነበረ። የዚህን ጊዜ አጤ ዮሐንስ ሰሐጢ ላይ ከኢጣልያ ጦር ጋራ ተሰላልፈው ነበረ። ደርቡሽ አጤ ዮሐንስ በጦርነት መያዛቸውን አይቶ ወደ ጐንደር ገፋ። አጤ ዮሐንስ ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት፣ ውረድና ከደርቡሽ ተዋጋ ብለው ላኩ። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ግን የደርቡሽን ብርታት አይተው፣ ዛሬ የመጣው ደርቡሽ ለኔ የሚቻል አይደለም ብለው ላኩ። አጤ ዮሐንስ እንዲህ ማለትህ ፈርተህ ነው፤ ውረድና ተዋጋ ብለው ላኩባቸው። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ምንም ነገሩን ቢአውቁት፣ በኔ ምንም ፍርሀት የለብኝ እስትሞት እዋጋለሁ ብለው ተዋጉ፤ ድል ሆኑ ሰውም አለቀ፤ እርሳቸውም ሸሽተው አመለጡ።

አጤ ዮሐንስ ግን በዚህ ተናደው አንተ በፈከርኸው ወደህ ድል ሆንህ ሰውን አስፈጀህ ብለው ተቆጥተው ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ላኩ። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ግን እንኳን አንተ አልሞትህ እንጂ ግድ የለም አይዞህ ብለው እንደ መላክ ሁሉ፣ እንዲህ ያለ ክፉ ቃል ላኩብኝ ብለው አዘኑ። አጤ ዮሐንስ ላጤ ምኒልክ እባክህ ደርቡሽ መጥቶ ቤተክርስቲያን ሲአቃጥል፣ ታቦት ሲአረክስ ዝም አትበል፣ ለኔ አልልም ስለ ሃይማኖትህ፣ ስላገርህ ብለህ ተዋጋ አሉና ላኩ። አጤ ምኒልክ ከወሎ ገሥግሰው ወደ ጐንደር በሄዱ ጊዜ ደርቡሽ

ጐንደርን አቃጥሎ አገሩን ገባ። ደርቡሽና አጤ ምኒልክ ግን ነገር ለነገር ተዋውቀው ነበረ አስቀድመው። ለሁሉም ነገር አጤ ምኒልክ አዘዞ ላይ ሠራዊተዎን ሁሉ አሰልፈው አዩ። ሰልፉ አምሮ ሠራዊቱ በዝቶ እንኳን ደርቡሽ ይቆምለት ላጤ ዮሐንስም ሠራዊት ቢሆን በግርማው ብቻ አለመድፍና አለነፍጥ የሚአንቀጠቅጥ ነበረ። አጤ ምኒልክ ያን ሁሉ ሰልፍ በፈረስ ሁነው ዳር እስከ ዳር እየቃኙ አዩ አዩና ከልበዎ በደረሰ ጊዜ ቀኝና ግራውን በዘንግ እያሳዩ በዚህም ቢመጣ በዚህም ቢመጣ ውሎህ እንዲህ ነው አሉና ለሠራዊተዎ ነገሩ። የዚያን ጊዜ ነገሩን አውጥተው ባይናገሩት ትግሬ ቢመጣ እንዲህ ሁነህ ተሰልፈህ በሰናድርና በመድፍ አቅልጠው በፈረስ አደባየው ማለተዎ ለሁሉ ገባው፣ የመከዳተዎ ነገር ታወቀ። ከዚያው ላይ አቅራሪ ተነሣና አይሆንም እንጂ ተሆነማ ተመጋዞ ይሻላል ጉልማ ብሎ አቅራራ።

አቅራሪ እንዲህ ማለቱ ከዚያ በፊት ጉልበት እየተሰማው የሸዋ ሰው እንዋጋ ለትግሬ መገበር አይገባነም ሲል አጤ ምኒልክ ጊዜዎን እየጠበቁ ዝም ብለው በጆሮዎ ይሸኙት ነበረና ስለዚህ ነው። የዚያን ጊዜ ግን ነገሩ መዘራዝር ገባ፣ ተቈረጠ። አጤ ዮሐንስ ዝም ማለታቸውን ትተው እንግዴህ ደርቡሽ ተሄደ በመጣህበት መንገድ ወዳገርህ ተመለስ ብለው ላጤ ምኒልክ ላኩ። አጤ ምኒልክ ግን ይልቁንም ተናደዱና በደንገል በር አድርገው ወደ ጎጃም ተሻገሩ። የጎጃም ሰውም እልልታውን እያቀለጠ ተቀበለዎ። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም በያገሩ በየመንገዱ ሁለንተናውን እያሰናዱ በደስታ ተቀበሉዎ። ከዚህ ወዲአ ሁለቱም ንጉሦች በትግሬ ሰው ተባበሩበት፣ ከዱ። ውላቸውም አጤ ዮሐንስ ወደ ጎጃም የሄዱ እንደሆነ፣ አጤ ምኒልክ በጌምድር ሂደው በስተጀርባ ሊታዘሉና ሊከቡ። አጤ ዮሐንስ ወደ ሸዋ የሄዱ እንደሆነ ግን ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በጌምድር ወርደው በስተጀርባ ሊከቡ ነበረ።

አጤ ዮሐንስ የሁለቱንም መከዳት ወሬ በሰሙ ጊዜ ከኢጣልያ ጦር ተፋጠው የነበሩት ተቤቴ አንበሳ ሲገባ ተውጭው ነብር ጋር ተፋጥጬ ለምን እቀመጣለሁ? ብለው ወደ ጎጃም ገሠገሱ። ወደ ሸዋ ትተው ወደ ጎጃም መሄዳቸው ግን ለብልሀት ነበረ። አጤ ምኒልክን ተዋግተው እንዳይዋጣላቸው

አውቀው ፊት የሚአስቸንፋትን ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ድል አደርገው አጤ ምኒልክ ደንግጠው ሳይዋጉ እንዲገቡላቸው ነበረ። ነገር ግን አባ ዳኛው አንድ ጊዜ ልቡ ቈርጦ ተነሥቷልና ለዚህ ላጤ ዮሐንስ መሰሪነት ልቡ ፍንክች አላለም። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም ጅበላ ሶስት ወር ሙሉ በትግሬ ጦር ተከበው ተቀመጡ። ጎጃምን የመሰለ ደግ አገርም ሶስት ወር ሙሉ በትግሬ አንበጣ ተመደመደ። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም አጤ ምኒልክ በውለዎ በጌምድር ወርደው እንዳላገዟቸው ባዩ ጊዜ ታርቀው ተጅበላ ወረዱ። ከዚህ በኋላ ግን አፄ ዮሐንስና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት አንድነት ሁነው አጤ ምኒልክን ለመውጋት ወደ ሸዋ ተቃኑና አባይን ለመሻገር በጋላ ቤት በኩል ቃጡ። አጤ ምኒልክ አስቀድመው ነገሩን አውቀውት ነበረና ወደ ግንደ በረት ደጃች መኰንንን ሰደዱ፤ በስላሴ በኩልም ራስ ዳርጌን፣ ወደ ወሎም ወሴ ብጡልን ሰደዱና እርሰዎ ራሰዎ አዲስ አበባ ተቀምጠው ከተማዎን ያሰሩ ጀመረ።

አጤ ዮሐንስና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት አባይ ደረሱና ታባይ ወዲአ አሻግረው ቢአዩ ደጃች መኰንን ያረርጌን ሁሉ ጦር አስከትተው ሂደው ግንደ በረት ላይ ያን ሁሉ ነጭ ድንኳኑን የጥቅምትን ኮከብ አስመስሎ ደቅድቆ አዩት። አጤ ዮሐንስ የሸዋ ሁሉ ጦር ከቶ ከባለቤቱ ጋራ መጥቶ መስሏቸው የግምጃ ድንኳን አላይም፤ የንጉሡ ድንኳን ወዴት ነው? ብለው ጠየቁ። ያወቀ ሰው ቶሎ ብሎ አጤ ምኒልክ ጥንቱንም ካዲስ አበባ አልተነቃነቁም፤ አርፈው ከተማቸውን ያሰራሉ፤ ይሄ ጦር ግን ያረርጌው ጌታ የደጃች መኰንን ብቻ ነው ብሎ ነገራቸው። በዚህ ጊዜ አፄ ዮሐንስ አንድ ደጃዝማች ብቻ ይሄን ያህል ጦር ካለው የሱ የራሱስ ምን ያህል ሥራዊት ይኖረው ብለው ተገረሙ። ተገረሙ ማለት አጠይሞ ለመናገር ያህል ነው እንጂ ፈሩ፣ ተንቀጠቀጡ ለማለት ነው። በዚያ በኩል መሄዳቸው ጥንቱንም ለማንገራገር ነበር እንጂ አባይንም መሻገር ሁኖላቸው ቢሆን እውነት የዚያን ጊዜ ጉረሮ የሚውጠውን እጅ ይመጥነዋል ነውና ካባ ዳኘው ጋራ ተዋግተው እንዳይዋጡት ያውቁ ነበረ። ስለዚህ ባባይ ምክኛት አድርገው እንዲአው ዳር ዳሩን ይሉ ጀመረ።

ያን ትተው አባይን በሰላሌ በኩል ለመሻገር ተጓዙ። ነገሩ ከልብ አልነበረም፤ ታፍ በላይ ነበረ። በሰላሌም በኩል ታባይ ማዶ አባ ግርሻ ዳርጌ ድንኳኑን ለጥልጦ ሰፍሮበት ነበረ። ነገሩ እያደረ ከበደ የሸዋ ፀሐይ ገና ተመስኮቷ ብቅ ብላ ስታበራና ስታጻድል የትግሬን ሰፈር የቀን ጨለማ ወርዶ አጠለቀው። ይሄ ሁሉ ሲሆን አጤ ዮሐንስ መቸነፋቸውን በልብ ተረድተውት ሳለ ባፋቸው ምንም አልተረቱ ነበረ። በዚህ መካከል ወግድ ምኒልክስ መቸም አምልጦ አያመልጠነና አሁንስ ቤተክሲያናችነን ያቃጠለውን፣ ታቦታችነን ያረከሰውን ደርቡሽን ሂደን እንውጋ፤ ደማችነን እንመልስ ብለው ወደመተማ ወረዱ።

ከዚአ ወዲአ ያጤ ዮሐንስ ነገር እጅግ ያሳዝናል፣ እጅግ ያስለቅሳል። የውነት ነው አጤ ዮሐንስ ለዘውድ ሳስተው ሠራዊት ለማብዛት ጦር ለማጠንከር ብለው የሚአበሉት እህል፣ የሚሰጡት ገንዘብ፣ የሚሸልሙት መሳርያ፣ የሚጋለብ ፈረስ፣ የሚጫን በቅሎ፣ ለሠራዊታቸው ቢአጡ፤ ደጎ በደሉ ተሰሪ አገቡ ልዥ አስሸለጉ አገር ዘረፉ አገር አጠፉ ደሀ አስለቀሱ፤ ተትግሬ በቀር ሠራዊታቸው ድፍን በጌምድርን መደመዱን አጠፉ ላስታን ድላንታን የጁን ወሎን አጠፉ፤ የትግሬ ወታደር በሐምሌ ዝረዝር አሳጨደ በበጌምድር ደሀ ግፍ ሰራበት፣ የትግሬ ወታደር በዚያ ጉረሮ በሚፍቅ ቋንቋው ኩሪ ኩሪ እያለ እርጉዝ አስወረዳት፣ እምጫት ጡቷ ደረቀባት፣ ቄሱ ተቤተክሲአን ገበሬው ተዱሩ ነጋዴው ተመደበሩ ተሸሽጎ በትግሬ ወታደር አለቀሰ፤ ተማለለ። የጐጃም ደሀ ሶስት ወር ሙሉ በትግሬ ሰው ሲአለቅስ ኑሮ፣ አጤ ዮሐንስ ከደርቡሽ ጋር ሊዋጉ መተማ ወረዱ በተባለ ጊዜ እንዲህ ብሎ የርግማን ቃል ተናገረ፣ ዘንድሮ ንጉሡ ደህና ቢመለሱ ምንኛ ጐልድፏል ጐጃሜ ምላሡ። ይሄን ሁሉ አፄ ዮሐንስ አወቁት፤ ያውቁት ነበር። ዛሬ እንዲህ እርሳቸው ተረሱ። ያደረጉት ነገር ግን እስተመቸውም አይረሳም። ነገር ግን የርሳቸው ነገር መጨረሻው አሳዘነ፣ ያሳዝናል። እንዲህ ሞት ላይቀር ከፉም በጁም ያን ያህል ሲፈሩ ሲከበሩ ለጥቂቱ ሲጠቅሙ ሁሉን ሲጐዱ ኑረው ካጤ ምኒልክ ጋር ተዋግቶ ድል ሁኖ በገዙበት ስፍራ እንዳይገዙ ባስገበሩበት ፈንታ እንዳይገብሩ በላይ ኑረው በታች እንዳይሆኑ ሞታቸውን መርጠው

ሞታቸውን ሲአውቁ ተጎጃም ገሥግሰው መተማ ወረዱ። ለመመለስ አይደለም፣ ተዚያው ለመቅረት። ከዚያው በመቅረታቸው ታልቈረጡ፣ አጤ ዮሐንስ ማዋጋታቸውን ትተው ሳይቸግራቸው ያን ያህል እንዳንደኛ እሸለምና እሾም ባይ ወታደር ተመሀል ገብተው ደረታቸውን ላረር ባልሰጡም ነበረ። ከዚያው መቅረታቸውን ወደውት ነበርና ባንድ ወገን ሥራዊታቸው ድል አድርጎ ሲማርክና ሲፈክር ሳለ እርሳቸው ባንድ ወገን ደረታቸውን ገልብጠው ለዚያ ቤተክሲአን አርካሽ ደርቡሽ እንካ ብለው ባልሰጡትም ነበረ። እንዲህ ዮሐንስን የመሰለ ንጉሥ ከዚያው ወድቆ ቀረ፤ የኢትዮጵያ ንጉሥ ያን ያህል ተገዛው አገር ለሶስት ክንድ መሬት ሳይበቃ ከደርቡሽ መሬት ወድቆ ቀረ። ያ የተቀደሰ ገላው ባረመኒ ጦር ተሰንጥቆ እረከሰ፣ ያን የመሰለ ንጹህ ገላው በደም ተነክሮ ባፈር ተለውሶ መተማ ላይ ወድቆ ቀረ። የዮሐንስ በደርቡሽ እጅ መሞት የኢትዮጵያ ቅስም መሰበር ነው። ምንም ደህ ቢበድሉ ላጤ ዮሐንስ ኢትዮጵያ ማዘን ይገባታል፤ የኢትዮጵያ ሰው ይቅር ስለ እግዚአብሔር ነፍስዎን ይማር ብሎ ላፄ ዮሐንስ ማዘን ይገባዋል። ያጤ ዮሐንስ ሞት ግን ባጤ ምኒልክ ብርታት ነው እንጂ በዚያ ደካማ ደርቡሽ ብርታት እንዳልሆነ ሁላችን እናውቃለን።

# በስደት ሲኖር ሲኖር ኑሮ የሰሎሞን ዘውድ በ፲፰፻፹፩ ዓመተ ምሕረት ከስፍራው ገባ።

ያጤ ዮሐንስ መተማ ላይ መሞት ወሬው ከመ ቅጽበተ ዓይን ላጤ ምኒልክ ደረሰ። አጤ ምኒልክ በብርቱ አዘኑ፤ አለቀሱ። ጠላት ከሆኑ ለምን አለቀሱ ይል ይሆናል ሞኝ ሰው። ምኒልክን ያህላል ልበ ወላላ ንጉሥ ምንም በተገባዎ ባያት በቅድመ አያተዎ አልጋ ቢጣሉ ዮሐንስን ያህል ንጉሥ በዚያ ቤተክርስቲያን አርካሽ ደርቡሽ እጅ መተማ ወድቆ ሲቀር የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የተቀደሰ ሬሳው በርኩስ እስላም እጅ ወድቆ መቃብር አጥቶ ሲቀር ምነው አለማዘነዎ? በዚህስ የውነቱን መናገር ነው የኢትዮጵያ ቅስም ተሰበረ።

የትግረ አንበሳ በደርቡሽ ጦር ተወግቶ ለሶስት ክንድ ላገሩ መሬት ሳይበቃ፣ ሞት አይቀርም በመጋቢት ባ፲፰የ፹፩ ዓመተ ምሕረት መተማ ላይ ቀረ። ነፍሱን ይማር ነፍሱን ይማረው።

ከዚህ በኋላ ያጤ ዮሐንስ የነበረ መኳንንት ሁሉ ከራስ መንገሻ ዮሐንስና ከራስ አሉላ በቀር ተመተማ እየገሠገሰ እየመጣ ላጤ ምኒልክ ገባ። የኢትዮጵያ ሠራዊት ተሁለት ተካፍሎ ይኖር የነበረ አንድነት ሆነ፣ ባንድ ቃል ማደር ጀመረ። የኢትዮጵያ ንግር ደረሰና የተመኘው የውነተኛው አውራው የውነተኛው የሰሎሞን ልዥ ዳግማዊ ምኒልክ ነገሡለት። ዳግማዊ ምኒልክ እንደ ብዙዎች ነገሥታት መድፍና ብረት ሠራዊትና ጉልበት ቢበዛም አይደለ መንገሡዎ። መንግሥተዎ የተገባ ነው። ብዙ ንጉሦች ከወታደርነት ወደ ወንበዴነት ከወንበዴነት ወደ ሽፍታነት እየተላለፉ ነጋዴ አስረው ባላገር ዘርፈው መንገደኛ ገፈው ባፈሩት ገንዘብ መሳሪአ ገዝተው ወታደር አባብለው ጦር አደራጅተው ዘውድ ከመጫን ይደርሳሉ። ያ የጫኑት ዘውድ ግና የወርቅና የብር አይደለም የደሀው እንባና የደሀው ደም እየረጋ የተሰራ ዘውድ ነው። በነዚያ ምክኛት በየዱሩ እስንት ደም ፈሰሰ፤ በየቤቱ እስንት ሰው አለቀሰ? በየመንገዱ እስንት ነጋዴ በያገሩ እስንት ጐናዴ የፊጥኝ ታሰረ ወረቱን ተቀማ የዚህን ነገር የሞተም ይረሳ ያለም ይገንዘበው። እኼ ሁሉም ሁኖ ወዲያው በነገሡ በማግሥት ካያት ተቅማታቸው ጀምረው ባለ ዘውድ ባለ አልጋ ሁነው ይገኛሉ። ነገሩ ግን ያንድ የእበላ ባይ ወሬ ነው፣ ከዚያም ወዲያ ያው ወሬ እውነት መስሎ ተለክኮ ይቀራል። ዳግማዊ ምኒልክ ግን ገና ተናቱ ማኅፀን ሲወጣ በጁ ሉል ጨብጦ በራሱ ዘውድ ደፍቶ ነው የተወለደ። ያው ዘውድ ግን እንደሌላዎቹ ሁሉ አንጠረኛ በሳት አቅልጦ በመዶሻ ቀጥቅጦ ያበጀው አዲስ አይደለም፤ ተባሕር ወዲአ ተጉዞ ከሰሎሞን የመጣ አሮጌ ያሮጌ አሮጌ ዘውድ ነው። ይሄን ዓለሙ ሁሉ ያውቀዋል። ይሄን አጭር ታሪክ የጣፈው አንድ እበላ ባይ አይደለም። ደግሞም እንዳይጠረጠር ይሄን የጣፈው የሸዋ ሰው አይደለ አንድ የዘጌ ልዥ እንጀራ ሳይንቅ እንጀራ የማይፈልግ ሰው ነው።

አጤ ምኒልክ ወዲያው አጤ ዮሐንስ እንደ ሞቱ ውጫሌ ላይ ሳሉ ከኢጣልያ መንግሥት ጋራ የፍቅር ውል ተዋዋሉ። የኢጣልያ መልክተኛ ኮንት አንቶኔሊ ይባል ነበረ። የውሉ ነገር ተ፳ ተከፍሎ ነበር። ከዚሁ ከ፳ው ክፍል የቀረው ሁሉ የፍቅሩን የንግዱን ነገር ሲናገር አሥራ ሰባተኛው ክፍል ባማረኛ የተጣፈው የኢትዮጵያ መንግሥት ወደሌሎች የኤውሮፓ ነገሥታት ጋር መላላክ የወደደ እንደሆነ በወዳጁ በኢጣልያ መንግሥት በኩል መላላክ ይሆንለታል ይል ነበረ። የዚህ ቃል ትርጉም ግን በፈረንሳዊ ቋንቋ ኢትዮጵያ ከኤውሮፓ ነገሥታት ጋር ለመላላክ የወደደች እንደሆነ በኢጣልያ መንግሥት በኩል ነገሯን ሁሉ ልትላላክ እሺ ብላ ተቀብላለች ይል ነበረ። እንደዚህ ትርጓሜ የሆነ እንደሆነ ኢትዮጵያ በኢጣልያ ጥግ እንድትኖር እንጂ አለኢጣልያ ፈቃድ ከማንም መንግሥት ለመላላክ ፈቃድ አልነበራትም። ለጊዜው የዚህ ትርጉም አልታወቀም ነበረ፤ ጥፋቱ ታስተርጓሚዎች ነው። አጤ ምኒልክ ግን ያማረኛውን ቃል እንጂ የፈረንጁን ትርጓሜ ሳያውቁ ደጃች መኰንንን፣ ከወዳጆቼ ኢጣልያ አገር ሂደህ ከብዙ ዘመን በኋላ ባያት በቅድመ አያቶቼ ሥፍራ መቆሜን የምስራች ብለህ የፍቅራችነንም ነገር አሳምረህ አስልተህ፣ አስታውቀህ ተመለስ ብለው ወደ ኢጣልያ ንጉሥ ላኩ። እርሰዎም ወደ እንጦጦ ተመለሱና የድፍን ኢትዮጵያን ካህናት አስጠርተው ከዳርቻ እስከዳርቻ ያለውን መኳንንት ጠርተው ጥንት የሁለትና የሶስት ንጉሦች የነበረውን ሠራዊት አንድነት አድርገው ጠጁ የረፋድ መንገድ በሚአህል ዳስ ሙሉውን ተጥሎ በጋን መሆኑ ተንቆ በገልዳና በሻንዳ እንደ ሐምሌ ጐርፍ እየጐረፈ፣ ፍሪዳው ድልቡ ሰንጋው ሽህሩ እንደካንቻ ተመቶ የንጉሠ ነገሥት ዘውድ ጫኑ። በበነጊአውም ወይዘሮ መባላቸው ቀረና እቴጌ ተብለው፣ እቴጌ ጣይቱ ዘውድ ጫኑ። የዚያን ቀን ዳር እስከዳር ኢትዮጵያ እልል አለች፣ ደስ አላት፤ ነገሠልነ፣ መጣልነ፣ እሰይ እሰይ የተመኘነው ደረሰልነ አለች።

ኢትዮጵያ የዚህን ደስታ ሳትጨርስ ገና ድፍን ኢትዮጵያ ታፏ እልልታዋን አንጠልጥላ በደስታ ሰክራ ሳለ የከብት እልቀት መጣና ድፍን አገሩ ባዶ እጇን ቀረ። ሽህ ላምና በሬ የነበረው ዘላን ካንድና ከሁለት የበለጠ አልተረፈውም።

ከዚህማ ወዲያ ኢትዮጵያ ደስታዋን ሳትጨርስ ባንድ ወገን ሀዘን ባንድ ወገን ደስታ ሆነና ማር በኮሶ እየለወሱ መዋጥ ሆነባት። የሞተው ላምና በሬ በየበረቱ በየመስኩ በየዱሩ በየገወቻው እየወደቀ በሄትም በሄት እየተዘለሰ እየቀረ አገር ምድሩ ጠነባ፤ ላሞራው ለቍራው ለጅቡ ለተኩላው አስቸነፈ። ይልቁንም የሚአስደንቀው ተከብቱ ጋራ ሰኰናው ስንጥቅ የሆነ ሁሉ የዱር አውሬ ምጥጥ ብሎ አለቀ። ጅብና ተኵላ በዱሩም በቤቱም ስራ በዛበት። አጤ ምኒልክ በዚህ አዝነው ተክዘው ቢጨንቀዎ ተንግዴህ የላም ሥጋ አትብሉ ብለው ባዋጁ ከለከሉ። ለሰው ከልክየ እኔ አልበላም ብለው ለራሰዎም የላም ሥጋ ተዉ። ከዚህ ቀጥሎ በድፍን ኢትዮጵያ ጭንቅ እራብ ገባና ሰውን ያሰጣው፣ ይፈጀው ጀመረ። የገጠር አራሽ ያገር ጐናዴ ሁሉ እስከ መቸውም ከብት አይተካ ብሎ ፈርቶ በገደልና በጎታ እህል ሞልቶት ሳለ ሸሸገ። ተገቢያው የህል መልክ ጠፋ። ፊት በብር ጫን ሁለት ጫን ይሸመት የነበረ፣ አንድ ቍልቢጥ የደፈረ አልገኝ አለ። ሰዉ ሁሉ በራብ እያለቀ በየመንገዱ፣ በየዱሩ፣ በየቤተክርስቲያኑ እድሞ በየመኳንንቱ ቅጥር ዙሪያ ይወድቅ፣ ይዘለስ ጀመረ። ጊዜው የጅብና ያሞራ ደስታ የሰው ሀዘን ሆነ። እንኳን አንዱ ላንዱ ይተዛዘን እንኳን ወዳጅ ለወዳጅ እግዜር ያጥናህ ሊባባል እናት ለልጇ፣ ልዥም ለናቱ ማልቀስ መላቀስ ቀረ። ለሞተም ሰው መቃብር ጌጥ ሆነበት። የዚያን ጊዜ መቃብር የሚቆፈርላቸው እንብዛ ለታደሉት ነበረ። ለቀረው ሁሉ ግን መቃብሩ ያሞራና የጅብ ሆድ ሆነ። ኢትዮጵያን የመሰለ አገር የዚያን ጊዜ ተመስኩ አንድ ላም ውል አይልበት፣ ተበረቱ እምቦሳ አይጮህባት፣ ተገጠሩ እርሻ አይታይባት አሻግሮ ላየው ልብ ያባባ ነበረ። ከብት ሳያልቅ በፊት በከብቱ ብዛት የተነሣ በጥርስ የሚቈነጥጥ እሳር ይጠፋበት በነበረው መስክ ሁሉ ፈረስ እስከ ፈረሰኛው የሚአጠልቅ ለምለም እሳር እያደገ በገዛጁ ይደርቅ ይወድቅ ያረጅ ይበሰብስ በላዩ ላይ ሌላው ይበቅልበት ጀመረ።

አጤ ምኒልክ በየቀኑ እየወጡ እልፍ ሁለት እልፍ የሚሆን ደሀ ከተቀመጠበት አደባባይ ተመካከሉ ገብተው በገዛ እጀዎ እንጀራን እያጠፉ እህሉን እየዛቁ ካልመጠወቱ በሌላ ሰው እጅ ማስመጥወቱ ከልበዎ

አይደርስም ሆነ። በዚያ ፀሐይ ሲመጠውቱ ወዘዎ ሲንጠፈጠፍ፣ በዚያ ዝናም ልብሰዎ ሲርስ ላየዎ ሰው ያስለቅሱ ነበረ። ነገር ግን አጤ ምኒልክ ይመጠውቱት የነበረ ደሀ ለዚያ ለጥቂቱ ተፊተዎ ተከተማዎ መድረስ ለሆነለት ደሀ ብቻ ነበረ። እራቡ ግን የሚአሳጣው በድፍን ኢትዮጵያ ነበረ ምን ይሆናል የዚያን ጊዜ ካንዳንድ ስፍራ ሰውን ሰው በላው። ተንሳሮ አገር አንዲት ባልቴት ሰባት ልጕች በልታ ተይዛ መጣች። አጤ ምኒልክ ተፊተዎ አስቀርበው እንጦጦ ከልፍኘዎ ደጃፍ ተቀምጠው፣ እውነት የሰው ሥጋ በላሽን ብለው ጠየቋት። እሷም፣ አዎ ጃንሆይ ቢርበኝ ሰባት ልጕች በላሁ አለች። ጃንሆይም መልሰው፣ ከወዴትስ እየያዝሽ እንዴትስ እያደረግሽ ገደልሽና በላሻቸው ብለው ቢጠይቋት፤ ከሚጫወቱበት እያነቅሁ አለች። ያችው እሴት ግን እንኳን ሰባት ልጕች የበላች ምንም አትመስል ነበረ። ያ እርቅናውን የወደቀ አንጀቷ ተጣጥፎ የድርቅ ላም ዳልጋ ይመስል ነበረ ዓይኗ አባብጦ፣ አመድ መስላ ካሁን አሁን የምትወድቅ ትመስል ነበረ። ደጉ ምኒልክ ባይነዎ እንባ እየተንቆረዘዘ እንዴት አገሬ ጠፋ ደጎዬ አለቀ ብለው አለቀሱ። ያችንም እሴት ዘመን ያመጣውን ምን ይደረጋል ብለው እንዳይበርዳት ልብሱን፣ እንዳይርባት ቀለቡን አዝዘው ላዛዡ አሳልፈው ሰጧት። አንድ ልዥ ነበራትና ልዧንም እንዲማር ወደ አቶ ሮባ አታክልት ሰደዱት።

አጤ ምኒልክ በምጧትም በርጥባንም በምንም ቢማስኑ ለድፍን ኢትዮጵያ ደጎ እንዳይበቃ አዩትና አንድ ብርቱ ነገር አስበው አገኙ። ነገሩም እንዲህ ነው። ቅድም እንደተናገርሁት የገጠር አራሽ ያገር ጕናዴ እህሉን በየገደሉና በየጎታው ሸሽጎ አንዳንድ ቁልቢጥ እሕል ባንዳንድ ብር እያቀና ብሩን ይጎደጕድና ያምቅ ጀመረ፤ ሰውም ለማለቅ አልቦዝን አለ። በዚህ ጊዜ ልበ ብርሃኑ ንጕሥ መኳንንቱን በያገሩ ሰደዱና የተሸሸገውን ሁሉ እሕል እያስያዙ ለባለ እህሉ ለቤተ ሰቡና ለራሱ ላንድ ዓመት የሚበቃ ቀለብ እያስተዉ የቀረውን ለተራበ ደሀ አስናኙት፣ አከፋፈሉት። ከዚህ በኋላ ይሄን ወሬ የሰማ ባለ እሕል ሁሉ ሹም ደርሶ የሸሸገውን እህል እንዳይዝበት እያወጣ ያቀናው ጀመረ። ገቢያም ከዚህ ወዲያ መጥገብ ጀመረ፤ ሰውም በርኅብ

መሞቱ ቀረ። ደጉ ንጉሥ በዚህም ብቻ ነገሩን አልተዉት እንደ ደጎ ባላገር መጥረቢአ አስለው መቆፈሪአ አዋደው ካንቻ መቍረጥ መሬት መቆፈር ጀመሩ። አንድ ቀን ከእንጦጦ ማርያም በታች ያለውን የኤካን ዱር በንጉሥ እጀዎ መጥረቢአ ይዘው ካንቻ ሲመቱ፣ እግረዎን ጋሬጣና እሾህ ደም አደረገዎ። አብረዎት የነበሩ መኳንንት በዚህ ደንግጠው በሻማ ደምዎን ለመጥረግ ተጐነበሱ። ደጉ ምኒልክ ግን ተቈጡና ተዉ አትንኩኝ! ይልቁንስ እኔ ለናንተ እንዳሳየሁ እናንተም ከበታቻችሁ ላለው ሰው አሳዩ አስተምሩ፣ ከዚህ ወዲያ ትርፍ ጥቅሙን ታዩታላችሁ አሉ። የዚህን ጊዜ ቃለዎን የሰማ ደመዎን ያየ መኳንንት ሁሉ ያልተንቀጠቀጠና ባይኑ እንባ ያልቋጠረ መኳንንት አልነበረም።

ድሮ ይሄ ትምህርት ለፍጥረቱ በቃውና ሁሉም ለየራሱ መቆፈሪአውን መጥረቢአውን ማጭዱን እየያዘ እንኳን ሌላው መኳንንቱ ካህናቱ ቄሱ ቈመሱም አልቀረ ሁሉም ወደ ዳሩ ተሰማራ። የሁሉ ጨዋታና አፍ መውጫው ድሮ የቁፋሮ ያረሞ የዘር የጕልጓሎ ብቻ ሆነ። ጥንት ቆፋሪ ማለት የስድብ የውርደት ስም ነበረ፣ ከዚህ በኋላ ግን እገሌ ቆፋሪ ሆነ፤ ቀኛዝማች እገሌ ፊታውራሪ እገሌ ቆፋሪ አራሽ ሆነ ማለት የክብር የምስጋና ስም ሆነ። ይሄ በሆነ ባመቱ እራብ በያገሩ ጠፋ። ደጉ ምኒልክ እንዲህ ደኅውን ለማክበር እርሱ ተዋርዶ ካንቻ ለመምታት መሬት ለመቆፈር ወደዱር ሄደ። ኢየሱስ ክርስቶስ ለማስተማር የሐዋርያትን እግር ተደፍቶ አጠበ። ዳግማዊ ምኒልክም ለደኅው ለማስተማር እጁን ላጣጥ እግሩን ለጋሬጣ ገብሮ ካንቻ መቍረጥ ጀመረ። ክርስቶስ ሞት ሳይገባው ለሰው ሲል ተሰቅሎ ሞተ። ዳግማዊ ምኒልክም ለደኅው ሲል ሉል በጨበጠበት እጁ ውርደት ሳይገባው መጥረቢአ ይዞ ዱር መነጠር፣ እግሩ በሾህ በጋሬጣ ደም አባላ ሆነ። የውነተኛ ንጉሥ እንዲህ ነው። ሞት አይቀርምና ምኒልክም ይሞታል፤ ይሄ ነው የኢትዮጵያ ጉዳት፣ ይሄ ነው ብርቱው መከራዋ። አጤ ዮሐንስ ደኅው ያለውን ሁሉ በተሰሪ ጨርሶ ለወታደር የሚአበላው ቢአጣ ከብቱንና ልዡን አስሸለጉት። ዳግማዊ ምኒልክ ግን ደኅው የሚበላው ቢአጣ የገዛ እህለዎን ናኙት፤ ከብት

አልቆ የሚአርስበት ቢአጣ ከሞት የተረፈውን የገዛ በሬዎን እረስበት ብለው በያገሩ ለደኅው አካፈሉት። ይሄ አባት ነው እንጂ ገዢ ንጉሥ ነው፡- ግሩም ነው ግሩም የግሩም ግሩም ። ምኒልክ ትበል እንዲህ እናት።

# አጤ ምኒልክና የኢጣልያ መንግሥት።

አጤ ምኒልክ ቅድም እንደተናገርሁት ውጫሌ ላይ ሳሉ በተዋዋሉት ነገር ደጃች መኰንንን ወደ ኢጣልያ ሰደዱ። ደጃች መኰንን አርባ ሰው አስከትለው ወደ ኢጣልያ አገር ተሻገሩና የኢጣልያ ንጉሥ በክብር ሮማ ላይ ተቀበላቸው። ያቀባበሉ ነገር በቃል ተናግሮ የሚጨርሱትና ጨርሶ በቃል የሚአስረዱት ነገር አይደለም፤ ግሩም እጹብ ድንቅ ነበረ። እስከ ረፉድ መንገድ ከሁለት እልፍ የበለጠ ጦር ተሰልፎ በጣልቂአ በጣልቂአው ባለ ሙዚካ ተሳክቶ ቁሞ መለኸቱ ነጋሪቱ እምቢልታው ሁሉ እየተነባበረ እየተመታ በመካከሉ ደጃች መኰንንን እስከ ሰዋቸው በባለ በባለ ብር ጉብጉብ ሰረገላ ተቀምጠው በፊት በኋላ በቀኝ በግራ ባለወርቅ ባለወርቅ ኩፍታ ባለብር ጥሩር ሽልሜ ሰቀላ ሰቀላ በሚአካክል ፈረስ ተቀምጦ ተቀምጦ ደንገላሳ እየጋለበ ከንጉሡ አዳራሽ ደረሰ። ያ ሁሉ የንጉሥ ሽልሜ ከናት ማኅፀን እንደ ሰው የወጣ አይመስልም ነበረ። ብቻ በተለየ ሁለት ሁለቱን መዘዞ አንድነት እየጨፈለቁ ያበጁት ይመስል ነበረ። በግራ ክንዱ ጎሽ በቀኝ ክንዱ ዘሆን ለግቶ አላግቶ የሚጥል ይመሳስል ነበረ። ይሄው ሽልሜ የንጉሡ ዘበኛ ከንጉሡ ዙሪአ የማይለይ ምርጥ ሎሌ ነው። ይሄው ምርጥ ዘበኛ ደረቱ በክንድ ቁመቱ በገመድ የሚሰፈር የመሳሰለ ሽልሜ ነበረ። ከንጉሡ አዳራሽ ሲደርስ ከደጃፉ ላይ ግራና ቀኝ የየጁን በርበሬ የመሰለ ጁህ ጁሁን ለብሶ ቅዱና ቅጡ ባበሻ ያልታወቀ ኩፍታ ኩፍታውን አድርጎ የብር የብር ጐመዱን ይዞ አጋፋሪ ቁሞ ነበረ። ደጃች መኰንን እስከ ሰዋቸው ተሰረገላ ወረዱና በዚያ ሁሉ ሰልፍ መካከል ወዳዳራሹ ገቡ። ካዳራሹ ጥልቅ ሲገባ ከበረዶ የነጣ የዕብነ በረድ ደረጃ ወለል ብሎ ይታይ ነበረ። በዚያ ወለላ ሰፊ ደረጃ ላይ በመካከሉ ተመልካም ከፈይ የለሰለሰ ወላንሳ ተነጥፎበት ነበረ። ከደረጃው መካከል ብቅ ሲባል የሰማይ ስባሪ የመሳሰለ መስተሀት ዙሪአ ዙሪአውን እንቍጣጣሽ በመሰለ ወርቅ ተጣፍጦ ላይን ያሰክር እራስ ያዞር ነበረ። የቀረውን ታገራችን ታይቶ የማይታወቀውን ሕብር የሌለውን ሁሉ ላይን እንደሳት የሚፋጀውን እንደ ጮራ የሚዋጋውን ደፍሮ ለማየት የሚቸግረውን በየገጹ በየሳንቃው

በየመስኮቱ በየወለሉ በየምኑም ሁሉ ያለውን ጌጥ ነገር ላየም ይግረመው ላላየም ይቀኈጨው ለሰማም ይጭነቀው እንጂ በስሙ ለማስረዳት ላገራችን አይታወቅም። በዚህ መሀል ለመሀል ደጃች መኰንን ሙሉ መሳሪያቸውን አድርገው ሰዎቻቸውም አጊጠው አምረው ሄዱ፤ ሄዱና የጉግሥ መጫወቻ ከሚአህል ወለል በደረሱ ጊዜ ሁለት ሶስት ጊዜ ለጥ ለጥ ብለው እጅ ነሱ። ከዚያ ካዳራሽ ወለል መሀል የኢጣልያ ንጉሥ በሽልሜው ታጥሮ በመኳንንቱ በሹማምንቱ ተከቦ የመንግሥት ልብሱን ለብሶ ከመንበረ መንግሥቱ ላይ ተቀምጦ ነበረና እንዴት ዋላችሁ እንኳን ደህና ገባችሁ! አሰኘ። ከዚህ ወዲያ ንጉሡ ከመንበረ መንግሥቱ እንደ ተቀመጠ የኢትዮጵያንና የኢጣልያን ፍቅር ነገር ቃሉን በወረቀት አድርጎ ይዞ ነበርና አንብቦ ለደጃች መኰንን አሰማ። ንጉሡ ወዲያው አፈፍ ተነሣና ለደጃዝማች መኰንን እጁን ሰጠ፤ ቀጥሎም ለፊታውራሪ ቢራቱ ሰጠ። ያ ግርማው የሚአንቀጠቅጥ ፍቅሩ የሚአሳስብ ደግ ንጉሥ ኡምበርቶ ቀዳማዊ ደስ ብሎት ደስ አሰኝቶ ያበሻን መልክተኛ ተቀበለ። ደጃች መኰንን ወዲአው ጃንሆይ የሰደዱትን ገጸ በረከት ሁሉ አቀረቡ። ንጉሡ እስከ መኳንንቱ ያን በረከት ከበው ደስ ብሏቸው አዩ። ተሁሉ ደስ ያሰኛቸውና እንደ ግሩም ያስደነቀ አንድስ አንድስ ያህል ታይቶ የማያውቅ ሁለት የዝሆን ጥርስ ነበረና ያ ነው።

ደጃች መኰንን ከኢጣልያ አገር እስከ ሰዎቻቸው እየተከበከቡ በደስታ ሮማ ላይ ተነሐሴ እኮሌታ እስከ ህዳር ድረስ ተቀመጡ። የኢጣልያን ዋና ዋናውን ሁሉ ከተማ እየዞሩ አዩ፣ ደስ ተሰኙ። ብዙ ምሽግም እየዞሩ ሲያዩ ታኲስም ኀውልት የሚበላልጥ መድፍ ሲተኮስና በዙሪአው ያለው ሰው መሬቱ እየተንቀጠቀጠ ሲወድቅ አዩ፤ ተገረሙ፣ ተደነቁ። አንዱ የመድፍ ጥይት ብቻ ቁመቱ ከፊታውራሪ ቢራቱ ዛሬም ደጃች ተብሏል ከሱ ቁመት ስንዝር ተጋት በለጠ። ወፍሩ ግን ሁለት ሰው ክንዱን ዘርግቶ በዙሪአው ቢጠመጠም ሳይደርስበት ቀረ። ይሄ የዚያን ጊዜ ነው ዛሬ ግን መድፍና የመድፍ ጥይት አራት እጥፍ እየበለጠ ሂዷል።

በዚህ ደስታ በዚህ ፍቅር መካከል ኢትዮጵያ በኢጣልያ መንግሥት ውስጥ ልትኖር ውል ተደረገ የሚል ወሬ በጋዜታ ላይ ተጣፈ። እቴጌና ጃንሆይ ጥበብ ተማር ብለው ኢጣሊአ አገር የሰደዱት አንድ አፈወርቅ የሚባል ትውልዱ የዘጌ የሆነ የኢትዮጵያ ልጅ ከዚአው ነበረና ይሄን ቃል ተጋዜታ ላይ አይቶ ለደጃች መኰንን በኢትዮጵያ ምነው እንዲህ ያለ ክፉ ነገር ተደረገባት፡ - ብሎ ነገረ። ደጃች መኰንን ቶሎ ብለው ይሄ ነገር ፍቅራችነን ያደፈርስብናልና ቶሎ ይሄ ወሬ ይታረም አይሆንም ብለው ለኮንት አንቶኔሊ ተናገሩ። ወዲአው ደጃች መኰንንና ኮንት አንቶኔሊ በዚህ ነገር ተጣሉ። ያም የኢትዮጵያ ልዥ አፈወርቅ የጋዜታውን ቃል አውጥቶ ላገሩ ተቈርቁሮ ለደጃች መኰንን በተናገረበት ነገር ሮማ ላይ ግፍ ተሰራበት ኮንት አንቶኔሊ ፊት በገንዘብ ዝም እንዲል አባበለው፤ የማይሆንለት በሆነ ጊዜ ግን አይቶ ባደባባይ ከፍና ዝቅ አድርጎ ሰደበው፣ አዋረደው።

የኢጣልያ መንግሥት ከራስ መኰንን ጋራ የሁሉንም ነገር ለመጨረስ ኮንቴ ሳልምቤኒ የሚባል ሰው ወደጃንሆይ ላከ። የዚያን ጊዜ ነራሲኒ የሚባል አንድ የወታደር ሀኪም ደጃች መኰንን ለመንግሥት ነግረው አስፈቅደው ወዳረርጌ እንዲወጣ ለማድረግ አፈወርቅን መከራ አሳይቶ ለደጃች መኰንን ንገርልኝ ብሎ ለመነ። ደጃች መኰንን ፊት እምቢ አሉ ኋላ ግን አፈወርቅ አጥብቆ ለመናቸውና እሺ ብለው ለመንግሥት አስፈቀዱለትና ይሄው ነራሲኒ አረርጌ ወጣ። ደጃች መኰንን ከኢጣልያ ተነሥተው ኢየሩሳሌምን ስመው ምጥዋ በታኅሣሥ ገቡ።

ዳግማዊ ምኒልክ በጥር ራስ መንገሻን ለማሳመን ትግሬ ገቡ። የትግሬ ጦር ሸሽቶ በየዱሩና በየዋሻው ተሰማራ። አጤ ምኒልክ ዋሻውን ሁሉ በመድፍ እያቀለጡ የትግሬን አመጠኛ በግድ አስገቡት። ገና አጤ ምኒልክ ትግሬ እንደገቡ ያጋሜው ባላባት ደጃች ስብሐት ከትግሮች ተነጥሎ ገባላቸው። ደጃች መኰንን ጦራቸው ሁሉ አረርጌ ቀርቶ ከነዚያ ኢጣሊአ አገር አብረዋቸው ከሄዱት ከጥቂቶች ሰዎቻቸው በቀር ሰው አልነበራቸውምና ደጃች ስብሐት አድቦ ከጃንሆይ ድረስ ወሰዳቸው።

ዳግማዊ ምኒልክ ትግሬን መልሰው ለራስ መንገሻ ሰጥተው፣ ደጃዝማች መሸሻ ወርቄን አኲስም ላይ እንደ ጥብቅ አድርገው ሹመው እንጦጦ በሰኔ ገቡ። ደጃች መኰንንም ራስ ተብለው ባረርጌ ላይ ድፍን ጨርጨር ተጨምሮላቸው አረርጌ ተመለሱ። የኢጣልያ መንግሥት መልከተኛ ኮንቴ ሳልምቤኒ ከዚህ ቀጥሎ እንጦጦ በሐምሌ ገባ። አጤ ምኒልክ በክብር አሳምረው ተቀበሉት። ከዚህ ወዲያ የውጫሌ ውል እንደ ገና ተነሣ። አጤ ምኒልክ ኢትዮጵያ እራሷን ቀጥ ለበጥ አድርጋ ችላ በመንግሥቷ አዝዛ ትኖራለች እንጂ በማንም በማን መንግሥት ጥግ ትኖር ዘንድ ከዛሬ በፊትም በታሪክ አልተገኘ፣ ለንግዴሁም እንዲህ ያለው ነገር አይታለም፣ አይወራ፤ የውጫሌ ውላችነም የፍቅራችነን የንግዳችነን እንዲህ እንዲህ ያለውን ነገር ይናገራል እንጂ ኢትዮጵያ በኢጣልያ ጥግ ትኖራለች የሚል ቃል ታማረኛው ጽሕፈት አይገኝበትም። አሁንም ፍቅራችን እንዳይበላሽ ባስራ ሰባተኛው ክፍል ያለውን ውላችን እናንተ አጥፍታችኋልና ወዲአ ተዉ። እኔ ያጠፋሁት ነገር የለኝም፤ ባስራ ሰባተኛው ክፍል ያለው ውላችን ኢትዮጵያ በኢጣልያ ጥግ ትኖራለች የሚል ነገር እንኳን በውኔ በህልሜም አላሰብሁት ብለው ተናገሩ። ወዲያውም ለኤውሮፓ ነገሥታት ሁሉ ኢትዮጵያ እራሷን ችላ ትኖራለች እንጂ በኢጣልያ ጥግ ልትኖር ምንም ውል አላደረግሁ፣ እወቁልኝ ብለው ላኩ። የጀርመን ንጉሥ ለኢጣልያ የመርዳት ነገር ላከ። እንግሊዝ ደግሞ ከፉም በጎም ሳይናገር መካከለኛ ቃል መለሰ ነገሩ ለኢጣልያ ለማድላት ነበረ። መስኮብና ፈረንሳዊ ለኢጣልያ ጠላት ነበሩና ላበሻ የረዱ መስለው ላኩ። መስኮብስ እስቲ ላበሻ ወዳጅ ስለሆነ ይሁን ፈረንሳዊ ግን ምንም ላበሻ ሰው ነገሩ ባይገባው በኢጣልያ መቅናትና ለሌላ ብልሀት ነበረ።

የኢጣልያ መንግሥት ባስራ ሰባተኛው ክፍል የነበረው ቃል እንደተመኘው ሳይሆን ሊቀርበት በሆነ ጊዜ ተናደደና ኮንት አንቶኔሊን እንጦጦ ሂደህ የዚህን ነገር አንተ እንደጀመርህ ተነጋግረህ ብልሃቱን አስታውቀነ ብሎ ላከው። ኮንት አንቶኔሊም በታዘዘው ገሥግሶ እንጦጦ ደረሰና ነገሩ ተጀመረ። አጤ ምኒልክ ግን አንድ ጊዜ በተናገሩት ቃል ኢትዮጵያ

ምንም ቢሆን በሌላ መንግሥት ጥግ አትኖርምና በፍቅር እንኑር ትሉ እንደሆነ የዚህን ነገር ልቀቁ መልቀቃችሁንም ለድፍን ኤውሮፓ ነገሥታት አስታውቁ ብለው አስጨንቀው ያዙ። ኮንት አንቶኔሊ ግን የተዋዋልነውም ውል ላምስት ዓመት ብቻ ነው፣ አሁን ያሄው ካምስቱ ዓመት ሁለቱ አለፈ፤ እንግዴህ ሶስት ዓመት ነው የቀረነና ከፋም በጀም ይሄው ውላችን እንዳለ ሶስቱን ዓመት ይለፍ አለ። አጤ ምኒልክ ግን ነገሩ ሳይጐላ እንዲህ ባጓጉል እንኳን ሶስት ዓመት ሶስት ቀንም ቢሆን አያድርና ይልቁንስ አሁኑ ቶሎ ነገሩ ይለቅ ብለው ሰቅዘው ያዙ።

በዚህ መካከል ያስመራ ገዥ ጀነራል ጋንዶልፊ ከራስ መንገሻና ከራስ አሉላ ጋር መመሳጠርና መተባበር ጀመሩ፣ ትግሬም ወዲአው መሸፈቱን አስታወቀ። የኢጣልያ ጦርም አጤ ምኒልክ በፍቅር ተሰጡት አገር ወዲያ ተሻግሮ በለሳ ሙና ድረስ ያዘ። ነገሩም እያደረ በዚህ ከበደ። አጤ ምኒልክ በዚህ ተናደዱና፣ እንዲአውም ባያችሁ ከኔ ጋር ጠብ ፈልጋችኋል፣ ስለምን ተሰጠኋችሁ አገር ወዲህ ወጥታችሁ አገር ያዛችሁ? አሁንም ወደኋላችሁ ተመለሱና ከሰጠኋችሁ አገር ሳትዛነፉ ተቀመጡ አሉ። ኮንት አንቶኔሊና ኮንቴ ሳልምቤኒ ነገሩን ያላወቁ መስለው እንጃ አናውቅም አሉ። አጤ ምኒልክ ወደ ኢጣልያ ነገሩን ላኩ። የኢጣልያ መንግሥት ፊት ወደርሰዎ የላክናቸውን የኮንት አንቶኔሊንና የኮንቴ ሳልምቤኒን ወሬ እንጠብቃለንና ነገሩ ከዚያ በኋላ ይሆናል ብሎ ምላሽ ሰጠ። ነገሩ ወዝ ለመስጠት እንጂ ለመልቀቅ እንዳልሆነ አጤ ምኒልክ አወቁት።

ኮንት አንቶኔሊ ከዚህም በኋላ ችክ ብሎ ይዞ ውሉን የተዋዋልነው ላምስት ዓመት ብቻ ነው፤ የዚሁም አምስት ዓመት ጊዜው ተዋግዷል፤ አሁንም ይሄን የቀረውን ጊዜ ያሥራ ሰባተኛውን ክፍል ነገር አናንሣው ይቅር ብሎ ለጃንሆይ ተናገረ። በዚህ ጊዜ መቸም ነገር ታስተርጓሚ ነውና፤ አስተርጓሚው ኮንት አንቶኔሊ እንዳለው አምስቱ ዓመት እስቲአልቅ ድረስ ያሥራ ሰባተኛው ክፍል ነገር ላሁኑ አይነሣ ይቅር ይላል ብሎ ማስተርጎሙን ትቶ እንዲአው ባጭሩ ያሥራ ሰባተኛው ክፍል ነገር ይቅር አይነሣ ይላል ብሎ

ለጃንሆይ ተናገረ። ጃንሆይ ይቅርን በሰሙ ጊዜ እኔስ እስከዛሬ የተናገርሁት ባሥራ ሰባተኛው ክፍል ያለው ቃል እንዲቀር አልነበረምን፡- አሁንም እሺ ወዲአ ይቅር ይሰረዝ አሉ። ይሄው ቃል በወረቀት ተጣፈ። ባማረኛ የተጣፈው ባሥራ ሰባተኛው ክፍል የነበረው ቃል ይቅር ተሰርዟል ይል ነበረ። ይሄው ቃል በሁለት ወረቀት ተቀድቶ አንዱ ለኮንት አንቶኔሊ ተሰጠ አንዱ ከቤት መንግሥት ተቀመጠ። ኮንት አንቶኔሊ እሱ እንደተመኘው ሁኖ የተጣፈ መስሎት ደስ ብሎት ተቀበለ። እሄ በሆነ በማግሥቱ ግን ኮንት አንቶኔሊ ያን ወረቀት ለሌላ አስተርጓሚ አስተውሎ አስተርጉሞ ባየ ጊዜ ባሥራ ሰባተኛው ክፍል የነበረው ቃል ተሰርዟል ማለት ለመቸውም ተፍቋል ለማለት መሆኑን አወቀው።

ኮንት አንቶኔሊ በዚህ ደንግጦ ተናዶ ቶሎ ወደጃንሆይ ሄደ። አዲስ አበባ እቴጌና ጃንሆይ ከተቀመጡበት ከልፍኝ ገብቶ ምነው ባሥራ ሰባተኛው ክፍል የነበረው ቃል ተሰርዟል ተብሎ ተጣፈ፡- አለ። ጃንሆይም ሁለታችን አንተናኔ ተነጋግረን አንተ ወደህ የተጣፈው ቃል ነው ሌላ አልታከለበት ስለምን ነው አሁን መጠየቅህ? ጠጠት አደረብህን፡- አሉት። ኮንት አንቶኔሊ፣ እኔ ለጊዜው አይነሣ ይቅር አልሁኝ እንጂ ለጭራሹ ይሰረዝ አላልሁኝም አለ። ጃንሆይ ግን፣ ካንተ ቃል ያገኘሁትን አልለወጥሁም ባስተርጓሚ የተናገርኸው ቃል እሄው እንደተጻፈው ነው አሉት። ኮንት አንቶኔሊ ወዳስተርጓሚው ዞሮ ይሄን ሁሉ የምታዘናኩር ቀጣፊ አንተ ነህ! ብሎ አስተርጓሚውን ግራዝማች ዮሴፍን ተሳደበ።

እቴጌ ጣይቱ ፊት ለፊት ገጥ ያለ ነገር መናገር እንጂ መቸም ሽቁምቁም ያለ ነገር አይወዱምና ስድቡን ሰምተው አጥፍቶስ ቢሆን አሽከራችነን በሚገባ እኛ እንቀጣለን እንጂ አንተ እንዲህ አላገባብ በኛ ፊት አሽከራችነን መሳደብ አይገባኸም አሉት። ኮንት አንቶኔሊ እንደማፈር አለና ጥቂት ቆይቶ፣ ፊት ውጫሌ ላይ የተዋዋልነው ያሥራ ሰባተኛው ክፍል ቃል ተለወጠብኝ አሁን ደግሞ ትላንት የተዋዋልንበት አምስቱ ዓመት እስቲአልቅ ድረስ ያሥራ ሰባተኛው ክፍል ነገር አይነሣ እንተወው ብል እሺ ታሉኝ በኋላ ያሥራ

ሰባተኛው ክፍል ነገር ተሰርዟል የሚል ቃል አስጥፈው አሳትመው ሰጡኝ ብሎ ተቆርቁሮ ተናገረ። በዚህ ጊዜ እቴጌ ጣይቱ በውጫሌ የተዋዋልንበት ወረቀትም ቢሆን ኢትዮጵያ በኢጣልያ ውስጥ ታድራለች የሚል ቃል ታማረኛው አይገኝበት፣ እንዲህ ያለ ቃል ተጽፎበታል የምትል እንደሆነ ተሆነልህ አሳየነ። በትላንትናውም ነገር የሆነ እንደሆነ አንተው ወደህ ያሥራ ሰባተኛው ክፍል ነገር ይቅር አይነሣ ብትል ይሄው ተጻፈ አሁን ለምን ነው መጠጠትህ፡- ከመጀመሪአው እስከ መጨረሻው ድረስ ጃንሆይ ከተናገሩት ሁሉ አንድም ቃል አልተዛባ አልተዛነፈ ብለው ተናገሩት።

ኮንት አንቶኔሊ አንሥቶ ውጫሌ የተዋዋልንበት ወረቀት በፈረንሳዊ ቋንቋ የተጻፈው ይታይ አለ። እቴጌ ጣይቱ ግን እኛ የምናውቀው ባማረኛ የተጣፈውን ነው እንጂ የፈረንጅ ቋንቋ አናውቅም፤ አንተ ግን የኛን ቋንቋ ታውቃለህና ባማረኛ የተጻፈውን እየው አሉት። ከዚህ ወዲያ ኮንት አንቶኔሊ ነገሩ ሁሉ እንዳልሆነለት አይቶ በንዴት ያን የታተመውን ደብዳቤ ብጭቅጭቅ አርጎ ቀዳዶ ጣለና እንግዴህ ፍቅራችን ፈረሰ ብሎ የጦርነቱን ነገር ገልጦ ተናግሮ ወጣ። እቴጌ ጣይቱ ከትከት ብለው ስቀው የዛሬም ሳምንት አድርገው፤ በዚህ የሚደነግጥልህ የለም ሂድ የፈከርህበትን አድርግ እኛም የመጣውን እናነሣዋለን፤ እግሩን ለጠጠር፣ ደረቱን ለጦር ሰጥቶ አገሩን የማያድን ሰው ከዚህ ያለ አይምሰልህ፤ የገዛ ደሙን ገብሮ ለገዛ አገሩ መሞት ጌጥ ነው እንጂ ሞት አይባልም፤ አሁንም ሂድ አይምሽብህ የፈከርህበትን በፈቀደህ ጊዜ አድርገው እኛም ከዚኸው እንቆይሀለን አሉት። ያው ፈረንጅ በንዴት እጅና እግሩ እየተንቀጠቀጠ ፊቱ እንዲአውም እንዲአ ነበረና ጭው ብሎ ላዳን እንዶድ የጨረሱበት ሸማ መስሎ እጅ ሳይነሣ ተወርውሮ ወጣ። ወዲያውም ከዚያ የነበሩትን ጥቂቶች ኢጣልያዎች ታባሻ ጋር ጦርነት ልንገጥም ነውና ተኔ ጋር ዛሬ ተነሡ ብሎ በግድ ሳይወዱ ይዞ ዕለቱን ተነሣ።

እቴጌ ጣይቱና ዳግማዊ ምኒልክ ግን ጠላትነቱን ታስታወቀ በኋላ ምንም እሱ ክፉ ተናግሮ ሰላምታ ነፍጎ እንደ ቡኸር ከንጉሦች ፊት ዘሎ ገና ተልፍኙ ቆቡን ተራሱ አድርጎ እንደ ዘላን ከበርቴ እያፎጫጨ ቢሄድ ለክፉ አድራጊ

በጎ መልስ ነውና ለመጓዣ ሲጋሩን ለመፍጠኛ ጮሌውን በመጣምር አንቈጥቍጠው እስከ ሰፈሩ ድረስ፤ ደህና ያድርስህ ብለው ሰደዱለት። ይሄም ብቻ አይደለ በተሻገረበትና በያደረበት ሁሉ ስፍራ ፍሪዳውና እንጀራው ጠላው ለተከታዩ ሙከቱ ዶሮው ማሩ ወተቱ ለሱ እንዳይጓደልበት አዘዙ። ኮንት አንቶኔሊ ግን ተናዶ በመንገድ ያየውንና እጅ የነሣውን ሁሉ እየተሳደበ ፊቱ ሎጥን መስሎ ጭው ብሎ ተጓዘ።

ዳግማዊ ምኒልክ እንግዴህ ከኢጣልያ ጋር በመዋጋታቸው ቊርጥ አደረጉና መሳሪአ እያሰናዱ ተቀምጠው ሳለ በበጌምድር የገዛ አሽከራቸው ራስ ዘውዴ ለምን አሳደጉኝ ለምን ከሻለቃነት ፊታውራሪነት፥ ከፊታውራሪነት ራስነት ሾሙኝ፥ በጌምድርን ሰጡኝ፥ ለምን ሎሌየ በዛ ጦሬ ገነገነ ብሎ ከዳ ከራስ ወሌ ጋራ ተፈካከረ አቅሙን ሳያውቀው አቅም አለኝ አለ፤ ጉልበቱን ሳያውቀው ጉልበት አለኝ አለ። ድሮ የተከተለው ጀግና የሚአስከትለው ጅም ነፍጥ የሚተኰሰው ጥይት የጌታው መሆኑን እረሳው። ወሌ ብጡል ማለት ጣይቱ ብጡል፤ ጣይቱ ብጡል ማለት የጁ አማራ ስሜን በጌምድር ማለት መሆኑ ጠፋው። በዚህ ሞኝነቱ ሲፈክር ሲፈክር ባጀና ለመዋጋት ዘቢጥ በታች ያን ሁሉ ጦር አስከትቶ ሰፈረ። ወሌ ብጡል ግን ምንም ቢሆን ደፍሮ ወደሱ ጦር የሚወረውር ቃታ የሚከፍት ሰው ከራስ ዘውዴው ተከታይ አንድም እንዳልነበረ ያውቅ ነበረና ዘቢጥ ላይ ከጥቂት ጦር ጋር ሰፈረ። ነገር ግን እራስ ዘውዴ ማለዳ ተንቅልፉ ቢነሣ በህልም ታይቶ ብንን ሲሉ እንደሚጠፋ ነገር ጦሩ አንድም ሳይቀር ብቻውን ጒልቶት ሂዶ አገኘው። ከዚህ በኋላ ደንግጦ ከነዚያ አብረውት ተቀሩት ጥቂት ሰዎች ጋር እየጋለበ በረሀውን ገባ። ወሌ ብጡልም እሳት ለብሶ እሳት ጒርሶ አያምልጥህ ብሎ ፈረሰኛ በኋላው ለቀቀበት። ነገር ግን ብዙ ጦር ሲሸሽ በግድ ይታያል፥ እራስ ዘውዴ ግን ሲል ሲል ታስር ታስራምስት የበለጠ ሰው አልቀረውም ነበረና በረሀውን መልሶ በስሜን ቆላ ጠፋና አልታይ አለ። ኋላ ግን አምልጦ አለማምለጡን ባወቀው ጊዜ ተላልኮ ከራስ ወሌ እጅ ገባ። ጥቂት አላቈዩት ራስ ወሌ በመንቈር አግብተው አዲስ አበባ ወሰዱት። ሰው ጥቂት ያዘነበትና የነቀፈበት ነገር እራስ

ወሌ በጃቸው ተወደቀ በኋላ የጥንት አማቻቸውን ዘውዴን ያህል ሰው በመንቆር አግብተው በማስጐተታቸው ነው። እቴጌ ጣይቱ ግን ምንም ከፉ የተናገራቸው ብዙ ያናደዳቸው ቢሆን፣ ገና ከፊታቸው በመንቆር ገብቶ ራስ ዘውዴ በደረሰ ጊዜ እጅግ አዘኑ፣ እጅግ ተጠጠቱና ቶሎ መንቆሩን አስወልቀው በሰንሰለት አስገቡት። ወይ ሞኝነት! ዘውዴን የመሰለ መልከ መልካም፣ ዘውዴን የመሰለ የታደለ ጌታ በድፍረቱና በሞኝነቱ አቅሙንም ባለማወቁ ጌታውን አሳዳጊውን በመከዳቱ ወቃቢ ሸሸውና እንዲህ ቀረ። ያ ሁሉ ጌትነቱ፣ ያ ሁሉ ሲሳዩ የሕልም ሲሳይ ሁኖ ቀረ። ነገር ግን እነደጃች ነጋሽን እነራስ ወልደ ሥላሴን በጉልበት አስጨንቆ ይዞ ለጌታው አገልግሎ ደስ አሰኝቶ ነበረ።

አጤ ምኒልክ የራስ ዘውዴ ነገር አለቀና በትግሮች ነገር ገና እንደተናደዱ ነበረ። ራስ አሉላንና ራስ መንገሻን ቶሎ ድረሱ እያሉ መላልሰው ቢልኩ መጣን ቀረን እያሉ ዝም አሉ። የራስ መንገሻ ከኢጣልያወች ጋራ የመዋዋሉ ነገር መቸም አስቀድሞ ታውቆ ነበረ። ና ብለው ደጋግመው ቢልኩበት እሺ ማለቱን ትቶ ይልቁንም እሱ ራሱ እራስ ሲባል መሾም የማይገባውን እራስ ብሎ ደጃች ስብሐትን ሾመ። አጤ ምኒልክ ከዚህ ወዲያ ለኢጣልያ መንግሥት ያመጠ ሎሌየን ለመቅጣት ትግሬ እወርዳለሁና ከመረብ ወዲህ ያለ ሰዋችሁን ወደ አስመራ እንዲከረከም አድርጉ። ይሄን ማለቴ የሸፈተ አሽከሬን ስቀጣ የናንተ ሰው ድንገት ተመካከል ተገኝቶ የሞተ እንደሆነ ባልሆነ ነገር ፍቅራችን እንዳይሻክር ብየ ነው ብለው ላኩ።

የኢጣልያ መንግሥት ግን ምንም ኮንት አንቶኔሊ አስቀድሞ የጦርነቱን ነገር ገልጦ ተናግሮ ቢሄድ እንደ ገና ከጥንት ፍቅራችን እንመለስ ብሎ ዶቶር ትራብርሲን ወደ ሸዋ ላከ። አጤ ምኒልክም ዶቶር ትራብርሲን በክብር ተቀበሉት። የመጣበትን ነገርም በሰሙ ጊዜ እሺ እንጂ ምን ከፉ፣ ጥንቱንም ነገሩ ከኔ አልቀረ፣ የተጋፋችሁኝ እናንተ ነበራችሁ፤ አሁንም ከጥንቱ ፍቅራችን እንግባ ታላችሁ እሺ። ነገር ግን ራስ መንገሻ እናንተን ተማምኖ አምጦኛልና አስቀድማችሁ የዚህን ነገር አስታውቁኝ አሉ። የዚህን ጊዜ ራስ መንገሻ ወደ

ኢጣልያ እንደምን ልሁን? ወይ በተዋዋልነው አይዞህ በሉኝ በቅጡ እርዱኝ ካጤ ምኒልክ ለመዋጋት የሚበቃ መሳሪአ ስጡኝና ልዋጋ አለዚያ ግን እኔ እንዴት ላድርግ? ቶሎ ግባ እያሉ አጤ ምኒልክ ይጠሩኛል ብሎ ቢልክ የኢጣልያ መንግሥት ሂድ ተጌታህ ተስማማ እኛ አናግዝኽም ብሎ ላከበት። ከዚህ ወዲያ እራስ መንገሻ በኢጣልያዎች አመላለስ ተናዶና አዝኖ ቂም ይዞ ሸዋ ገሥግሶ ሂዶ ደንጊያ ተሸከሞ ወድቆ ባ፲፰፻፹፯ ዓመተ ምሕረት በግንቦት ከዳግማዊ ምኒልክ ጋራ ታረቀ። ትግሬም እንደገና ተመረቀለትና ተመለሰ። ራስ አሉላ ግን ከራስ መንገሻ ጋራ አብረው ደንጊአ ተሸከመው ታርቀው ራስ መንገሻ ወደ ትግሬ ሲመለስ እርሳቸው ተንግዴህ ትግሬ አልመለስም ከዚሁ ካደባባይዎ ደጅ እጠናለሁ ብለው አዲስ አበባ ቀሩ።

ገና ራስ መንገሻ ይሄን እርቅ ሳይታረቅ በፊት ሀኪም ትራብርሲም ገና ተልኮ ታገሩ ሳይመጣ ጀምረው አጤ ምኒልክ ጭራሽም ሳይታረቁ, ጭራሽም ሳይጣሉ ዝም ብለው ነፍጡን ጥይቱን መድፉን ከኤውሮፓ እያስጓዙ ለመሰብሰብ አልቦዘኑም ነበረ። ለሀኪም ትራብርሲ ግን እናንተ ከኔ ጋር መፋቀሩን ከወደዳችሁ ለኔ ምን ከፋኝ ብለው ወደ ኢጣልያ ታገሩ መንግሥት ሊነጋገር መለሱት። ወዲያው ሀኪም አገሩን ሲሄድ ፍቅር ከወደዳችሁ አንድ አራት መሊዎን የሰናድር ጥይት ስደዱልኝ ብለው ላኩ። የኢጣልያ መንግሥት ግን ነገሩን አዙሮ ሳያይ እሺ ብሎ አራት መሊዎን የሰናድር ጥይት አሰብ ድረስ ሰደደ። ሁለቱ መሊዎን ጥይት ቶሎ በግመል ተጭኖ ባውሳ ወጣና አንኮበር ደረሰ። የቀረው ሁለቱ መሊዎን ግን ግመል አጥጦ አሰብ ላይ ተቀመጠ። በዚህ መካከል አጤ ምኒልክ ለፈረንሳዊዎች የአሰልን ጨው ለክራይ ሰጡ ተብሎ በጋዜታ ተጻፈ። በዚህ ነገር የኢጣልያ መንግሥት ተከፋ። ከዚህ ወዲአ የኢጣልያ መንግሥት ጭራሹን ታርቀው እንዳይታረቁ አየና አሰብ የቀረውን ሁለት መሊዎን ጥይት ወደ ሸዋ እንዳይሄድ ከለከለ፤ ሸዋ በገባውም ጥይት እጅግ ተቈረቈረ፤ አዘነ። ነገር ግን ምን ይሁን የሆነው ሆነ የማይመለስ ነገር ነበረ።

ሀኪም ትራብርሲ እንደገና አበሻ ተመለሰና የተሰበረውን ሁሉ ነገር ለማቅናት ይጥር ይማስን ጀመረ። ነገር ግን አንድ ጊዜ ኮንት አንቶኔሊ እንዳይጠገን አድርጎ ነገሩን ሰብሮት ነበረና ምስነቱ ከንቱ ሆነበት። ባንድ ወገንም የኢጣልያ ጦር ከሰጡት ተሻግሮ ያልሰጡትን አገር በለሳ ሙና ድረስ ያዘ። አጤ ምኒልክ እየደጋገሙ ልቀቁ ቢሉ እሺ እያለ ወዝ ብቻ እየሰጠ ተመልቀቁ ላይ ተቸገረ። አጤ ምኒልክ ግን ባንድ ወገን ፍቅር የፈለጉ እየመሰሉ ባንድ ወገን ጠብ ፈልገው ኢጣልያዎች በለሳ ሙናን ነክሰው አለቅ አሉ፡- ይሄ ስራት ተጒልበት መያዛቸው ነው እኛም ለዚህ መድኃኒት አለነ ብለው የልበዎን በልብ አድርገው መሳሪያ ይሰበስቡ ያበዙ ይጠነቀቁ ጀመሩ። የጦርነቱ ነገር የተቈረጠ ገና ቀድሞ ነበረ፤ ነገር ግን ኢጣልያዎች ወይ ያስራ ሰባተኛውን ክፍል ውል ነገር ጨርሰው ለቀው እስከ በለሳ ሙና ድረስ ተሻግረው የያዙትን አገር ለቀው አልታረቁ ወይ ኮንት አንቶኔሊ በፈከረው ወጥተው አልተዋጉ ዝም ብለው ተፍቅሩም ተጠቡም ሳይሆኑ አጉል ተቀመጡ። አጤ ምኒልክ በዚህ ሞኝነት እየሳቁ ነገራቸውን ሁሉ እያበጃጁ እያሰናዱ ተጋፍቶ ቢመጣም እንገጥመዋለን ተጋፍቶም ባይመጣ ተደራጅተን ስናበቃ አለፈቃዳችን የያዘውን አገር ግፋን ሂደን እናስለቅቃለን ይሉ ጀመር። በዚህ ቈርጠው ተቀምጠው ሳለ አንድ ቀን ከፈረንሳዊ የገዙት ሰላሳ ያህል የስመዎ ምልክት ‘ም’ የተጣፈበት መልካካም መድፍ ደርሶላቸው ደስ እያላቸው ሲአዩ ሲአዩ ቆዩና በሀኪም ትራብርሲ ፊት እንግዴህ የመጣው ይምጣ አይመጣም እንጂ ቢመጣማ በዚህ እናሳየዋለን አሉ። የዚያን ጊዜ ነገሩን ያወቀ አወቀው የኢጣልያን ስም ባይጠሩት ነው እንጂ አጤ ምኒልክ የተናገሩት ነገር ግልጥ ነበረ። ያም ሆነ ያም ሆነ ሀኪም ትራብርሲ ነገሩ እንዳልተቃናለት አይቶ ጭራሹን ወዳገሩ ተነሣ። የኢጣልያ መንግሥት ግን የነገሩን ጭራሽ ለማስረገጥ ኮሎኔሎ ፒአኖን ወዳበሻ ሰደደ። ነገሩ የሞኝነት ነበረ ለሀኪም ትራብርሲ ያልሆነለት ነገር ለሌላ ሰው እንዳይሆን የታወቀ ነበረ። ኮሎኔሎ ፒአኖም አዲስ አበባ ደርሶ ነገሩን አይቶ በመጣበት እግሩ ተመለሰ። ተዚህ በኋላ የኢጣልያና የኢትዮጵያ መንግሥት ባፍ ቀረና ንግግሩ በመድፍ ብቻ ሆነ።

# ያዱ ጦርነት።

የኢጣልያ መልክተኛ ኮሎኔሎ ፒአኖ ካዲስ አበባ ወዳገሩ እንደ ተመለሰ በጥር ባ፲፰፻፹፯ ዓመተ ምሕረት ያስመራ ገዢ ጀነራል ባራቴሪ እራስ መንገሻን ከዋቲት ላይ ተዋግቶ ድል አደረገ። እንደውነቱ ግን የራስ መንገሻ ጦር አሳምሮ ተዋጋ። ነገር ግን ድል በሚአደርግበት ጊዜ ጥይት አለቀበትና ሰነፍ እርቅ ለማድረግ ተላላከ። የኢጣልያ ጀነራል ግን ነገሩ በመላ ገባውና መታረቁን ትቶ አይዞህ በለው ተሸሮልህል አለና ጦሩን አዘዘ። በዚህ ጊዜ ራስ መንገሻ ከተረፈው ጦር ጋራ ሸሽቶ ሰናፌ ሰፈረ። ጀነራል ባራቴሪ ቀኑን ሁሉ እየገሠገሰ ሲከተል ውሎ ጀንበር እንደ መጥለቅ ስትል ደርሶ ከዚያም ከሰፈረበት ላይ መድፍ ተያያዘው። እራስ መንገሻም የገዛ ድንኳኑ እንደተተከለ ጥሎ ሸሸ። የዚያን ጊዜ ግብር ገብቶ ኑሮ ሞሰቡ እንደተከፈተ ወጡ እንደወጣ ጠጁ እንደተቀዳ ተገኘ። ድንኳኑም እንደተተከለ ቀርቶ ተያዘ። አጤ ምኒልክ አጋዥ ብለው ብዙ ጦር በቀኛዝማች ኃይለ ማርያም እግር ሰደዱ። ነገር ግን ይሄው ላጋዥነት የመጣውም ጦር ከራስ መንገሻ ጋራ አንድነት ሁኖ ደብረ ኃይላ ሰፍሮ ሳለ የኢጣልያ ጦር ደረሰና ድል መታው ቀኝ አዝማች ኃይለ ማርያምም ተያዘ እራስ መንገሻ ግን ሸሽቶ አመለጠ።

የኢጣልያ ጦር መቸም ብርቱው ጦሩ ባሸ ብዙቅ ነበረና ትግሬን ሁሉ እስከ አሸንጌ ድረስ ያዘ። መቀሌ ላይም ብርቱ ምሺግ ሰራና ብዙ ጦር አስቀመጠ። ይሄ ሁሉ ሲሆን አጤ ምኒልክ ቶሎ ወደ ትግሬ ለመምጣት አልተቻኰሉም ነበረ፤ ዝግ ብለው ብቻ የጦርነታቸውን ሁሉ ነገር ያሰናዱ ጀመረ። ይሄ ዝግታዎ ግን ከኤውሮፓ ሁሉ የፍርኀት መስሎ ታይቶ ነበረ። አባ ዳኘው ሁሉንም ካሰናዳና ታሳመረ በኋላ ባረርጌ በኩል እራስ ዳርጌን ባውሳ በኩል ራስ ወልደ ጊዮርጊስንና ራስ ተሰማን አዛዥ ወልደ ጻድቅን ትተው ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን አስከትለው ወደ ትግሬ ጫን አሉና ተጓዙ።

አጤ ምኒልክ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጋራ ወደኋላ እየተጓዙ ራስ መኰንንንና ፊታውራሪ ገበየሁን ወደፊት መንገድ ጠራጊ ሰደዱ። አምባላጂ

የዚያን ጊዜ የኢጣልያ ጦር ሁለት ሽህ ያህል ሁኖ ከጥቂት መድፍ ጋራ ማጅኦር ቶዜሊ በሚባል ሹም እግር ታዝዞ ተቀምጦ ነበረ። አሸንጌ ሲደርሱ እራስ መኰንን መጣሁብህ አትችለኝምና ሽሽ ከፊቴ አትቁም ብለው አምባላጂ ለነበረው ጦር አለቃ ለማጅኦር ቶዜሊ ላኩ። ይሄው ማጅኦር ቶዜሊ ግን አሻፈረኝ፣ ከዚህ ስፍራ አልነቃነቅም፤ እስቲ ከደፈርህ ንካኝ ብሎ ላከ። ወዲያው እራስ መኰንን ደረሱና ከበው ይዘው አንድ ሳይቀር በሰናድር እርግፍ አደረጉት። ጥቂትም ቢቀር እስከ ጠበንጃውና እስከ መድፉ በራስ መኰንን እጅ ወደቀ። የኢጣልያ ጦር አለቃ ማጅኦር ቶዜሊም ፊቱን ወደኋላ እጥፍ ሳያደርግ እንዳንበሳ ኮርቶ እንደጀግና መክቶ እየተዋጋ ጐራዴውን ክንዱ ዛል ሳይልበት ይዞ እየፈከረ ተቆመበት ላይ ወደቀ። ነገር ግን ሰውነቱ አምባላጅ ወድቆ ቢቀር ስሙ በኤውሮፓ ቁሞ ቀረ። ራስ መኰንን ያምባላጅን ጦር ድል ተመቱ በኋላ ወደ መቀሌ ገሥግሰው ምሽጉን በታኅሣሥ በስምንት ቀን ከበው ይዘው ይዋጉ ጀመረ። ይሄ በሆነ በወሩ አጤ ምኒልክ ዝግ ብለው በያገሩ እያደሩ እየዋሉ ፈረስ በቅሎ እንዳይከሳ ጦረኛው ጀግናው እንዳይጐዳ ሳይቸኵሉ በየሰፈሩ ውሎ እያደረጉ ነጋሪቱ ውጋ ውጋ እያለ ሲጐሰም፣ መለኸቱ ባንድ ወገን አይዞህ ግፋ ግፋ ቀኑ ያንተ ነው የሚል እየመለሰ ሲክላላ ሲንጠረጠር፤ ባንድ ወገን ደግሞ አቅራሪ ኧረ ጉዱ፣ ኧረ ጉዱ በዛ በጀልባ ተሻግሮ አበሻን ሊገዛ? እያለ እያቅራራ ተጓዙ ተጓዙና መቀሌ የታኅሣሥ አመ ፴ ዕለት ደረሱ። የመቀሌን ምሽግ በሩቁ ከበው መውጫ መተንፈሻ አሳጥተው ከምሽጉ ውስጥ የነበረውን ጦር አፍንጫውን ከምሽጉ ደጃፍ ብቅ እንዳያደርግ አደረጉ። ተቀን ቀን አንድ ቀን እያዘዙ ምሽጉን በመድፍ ያስቀልጡት ጀመረ። ነገር ግን ሰው በከንቱ እንዳያልቅ ብለው ጭራሹን ተዋግተው ምሽጉን ለመያዝ አልጣሩም ነበር፤ ብቻ በራብና በጥማት እንዲፈታ ለማረግ ነበር አሳበዎ። ወደኋላው ግን ቀኑ ሲበዛ ጊዜ አምርረው መዋጋት ጀመሩ። የሸዋ ሰው አይኑን እየጨፈነ እስተ ምሽጉ ድረስ ከደጃፉ እየገባ ያልቅም ይፈጅም ጀመረ። ነገር ግን የኢጣልያው ጦር ጠንክሮ ይዞ ምሺጉን አላስደፍር አለ። ካጤ ምኒልክ ሰውም ብዙ ሰው ብዙ ትልልቅ መኳንንት አለቀ። ከዚህ ወዲያ አጤ ምኒልክ ገና ዋናው ጦር ሳለብነ በከንቱ ከምሺግ ደንጊአ ጋር እየተዋጋ ሰዋችን አይለቅ

አሉና እንዲአው ከበው ይዘው ምንጩን ውሀውን ሌት ተቀን በዘበኛ ኢያስጠበቁ ተቀመጡ። የኢጣልያም ጦር ከውስጥ ሁኖ የጦሩ በጦር የቀረው በራብና በጥማት አለቀ ተጨነቀ የሞተውም መቀበሪአ አጣ። አንዳንዱ ባሽ ብዙቅ በውሀ ጥማት ሊሞት ሲሆን ጊዜ ከውሀ ጠባቂዎች እየለመነ አንድ ብርጭቆ ውሀ ባስር ጥይት እየገዛ በሽሽግ ከመጠጣት ደረሰ። አጤ ምኒልክ ይሄን ወሬ ጠዋትና ማታ ይሰሙት ነበረና አዝነው ለምሽጉ ጦር አለቃ ለማጆኦር ጋሊአኖ መላኩን ትተው ከበላዩ ላለው ለጦሩ ሁሉ አለቃ ለጀነራል ባራቴሪ ተመቀሌ ምሽግ ያለው ጦር በውሀ ጥምና በራብ አይለቅብኝ ትል እንደሆነ ልተውልህ ይውጣ፣ እንኳን ሌላ እስከ መድፉም እስከ ጠበመንጃውም እስከምኑም ሁሉ ይዞ ይሂድ አልነካብህም ብለው ላኩ። እሱም እሺ ብሎ ለምሽጉ አለቃ ለማጆኦር ጋሊአኖ ላከና የምሽጉ ጦር ከምሽጉ ወጣ። አጤ ምኒልክም ለመድፉና ለቃው ሁሉ መጫኛ ኢጋሰስ ቢቸግረው የሚበቃውን ያህል ፫፻ ኢጋሠስ እኩሉን በዋጋ እኩሉን በክርካር ሰጥተው እስከ አዳጋሙስ ድረስ አስሸኝተው ሰደዱት። አጤ ምኒልክ ከዚህ በኋላ ወደ አዱ ተዘነበሉ። አዱ ደረሱና ሰፈርዎ አዱን መሰረት አድርጎ በቀኝም በግራም በፊትም በኋላም ተሳፍቶ ባንድ ወገን መጀመሪአው ባንድ ወገን መጨረሻው አይታወቅም ነበረ። ካዱ ወደ አስመራ ለመውረድ ለዚያ ሁሉ ሠራዊት የሚበቃ ቀለብ ባለመገኘቱ ተመከረና አዱ ላይ ዝም ብለው ግፉን እስቲሄድላቸው ተቀመጡ።

ይሄ ሁሉ ሲሆን የኢጣልያ ጦር በመርከብ እየወጣ ጥቂት ጥቂት እያለ ይሰበሰብ ነበረ። ፊት አዳጋሙስ ላይ አንድ እልፍ ካንድ ሽህ ፈረንጅ አንድ እልፍ ካራት ሽህ ባሽ ብዙቅ ከሰላሳ አራት መድፍ ጋራ ሰፍሮ ነበረ። የዚያን ጊዜ የኢጣልያ ጦር አለቃ ጀነራል ባራቴሪ ያነን አዳጋሙስ የነበረውን ጦር ብቻ ይዞ የዳግማዊ ምኒልክን ሠራዊት ገጥሞ እርግጥ ድል አደርጋለሁ ብሎ ግፉን ሂዶ ለማጫር ተሰናዳ። በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያን ኃይልና ብርታት ያወቁ ሰዎቹ ይተዉ እርቅ ይሻላችኋል ላትችሉ በከንቱ የሰው ደም አይፍሰስ ብለው ቢመክሩ፣ ያበሻ ጦር በቁጥር ቢበዛ ከኛ ፊት አንድ ሰአትም አይቆም በዚህ

በተሳላ መድፍ እናረግፈዋለን ብሎ ፈከረ። ይሄ ሁሉ ሲሆን ለዚሁ ለኢጣልያ ጦር አለቃ ከራስ መኰንንም ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም ከራስ ሚካኤልም የምስጢር ደብዳቤ ይመጣለት ነበረ። ሁሉም እየራሳቸው ጦርነቱ ሲጀመር ለናንተ አግዛለሁ አጤ ምኒልክን እከዳለሁ እያሉ ሁሉም በምስጢር ላኩበት። ለሱ እውነት መስሎት ደስ አለው ነገሩን ላወቀው ሰው ግን ይሄ ሁሉ የምስጢር ደብዳቤ አንድ ካጤ ምኒልክ ያልታወቀ አልነበረበትም፤ ከነዚሁ ሁሉ ሰዎች ለኢጣልያዎች ለማገዝ እንኳን በውኑ በሕልሙም ያሰበ አልነበረም። በቀረውስ ምን ቸገረኝ ብሎ ባገሩ ይረዳባት ነበር፡- ተብልህ የሚገኝ ሞኝነት ተራራ ያህላል ነውና ከጀነራል ባራቴሪ የዚያን ጊዜ የነበረ ሞኝነት እጅግ የሚአስቅ፣ እጅግ የሚአስደንቅ ነበረ። አንድ ቀን ዝምታና ዳታ ሲበዛበት ጊዜ ለጀነራል ባራቴሪ ራስ መኰንን እንዲህ ብለው ላኩበት ለምን ዝም ብለው ተቀምጠዋል፡- አሁንም ቶሎ ይምጡና ጦርነቱን ይጀምሩ፤ እኔ እርሰዎን ነው የምጠብቅ፤ ወዲአው ጦርነቱን ሲጀምሩ እኔ ወደ እርሰዎ እዞርና አግዘዋለሁ፤ አሁንም ቶሎ ፈጥነው ይምጡና ይግጠሙ ብለው ላኩ። እንዲህ የሚለውን ደብዳቤ ባነበበ ጊዜ ጀነራል ባራቴሪ በደስታ ሰከረና ግፋን ለመነሣት አሰበ። ወይ ሞኝነት! ከዘውድ በቀር ሌላ ምንም የቀረው የሌለ እንደራስ መኰንን ያለ ጌታ ባልቸገረው ነገር የሚወደውን ጌታውን ምኒልክን ትቶ ኢትዮጵያን ከድቶ ለኛ ይረዳል ብሎ ጀነራል ባራቴሪ ማሰቡ እጅግ ያስገርማል ብዙ ያስቃል! የኢጣልያ መንግሥት ግን እሱን ጀነራል ባራቴሪን ያበሻን ጠባይ የኢትዮጵያን ሁሉ ነገር በጣም ያውቃልና እሱ ያደረገው ነገር ምንም ቢሆን አይበላሽም መስሎት ሰዶት ነበር፤ ነገር ግን ያው የኢትዮጵያን ጠባይ ማወቁ ታየለት። የኢጣልያን መንግሥት ነገሩን ያበላሸው ታበሻ ወጥተው የነበሩትን የጥቂቶች ሰዎች ቃል እውር ጭፍኑን አምኖ ነገሩን ሁሉ እነሱ ባሉት ማድረጉ ነው። እሄ ሁሉ ዝንኩርኩር ያለ ነገር የመጣበት ምክኛት ባንድ ወገን ነራሲኒ የሚሉት ሀኪም አረርጌ ሁኖ ራስ መኰንን ለኛ ምስጢረኛ ወዳጃችን ናቸው እንዲረዱኑ እርግጥ ነው አይጠረጠርም እያለ በውነት የራስ መኰንንን ልብ የያዘ መስሎት ላገሩ መንግሥት ይልክ ነበረ። ይሄ ሁሉ ያበሻን ነገር ባለማወቁ ነው እንጂ አውቆት ቢሆን እንደራስ መኰንን ያለ ሃይማኖቱ

ከጅማት የጠና ለጌታው የታመነ ለኢትዮጵያ የጣረ ሰው ሳይከፋው ሳይጠመው እውነት ላገሩ ትቶ ለኢጣልያ ያግዛል ብሎ ተስፋ ባላደረገም ነበረ። እሄው ሀኪም ነራሲኒ አንድ ጊዜ አርርጌ ሁኖ እራስ መኰንንን በምስጢር አድርጎ አባክዎን ያስራ ሰባተኛው ክፍል ነገር እንዲቃናልነ ያድርጉ ብሎ ለመነ። እራስ መኰንን ምንም ነገሩ ቢደንቃቸው እስቲ ወዳጅ መስየ ለኢትዮጵያ የሚጠቅም ምስጢር ባገኝ ብለው እሺ አዲስ አበባ ስሄድ ነገራችሁን አሳምርላችኋለሁ ብለውት ኑረዋል። ሀኪም ነራሲኒ እውነት መስሎት የምስራች ራስ መኰንን አዲስ አበባ ሲሄዱ ያስራ ሰባተኛውን ክፍል ነገራችነን ሊአሳምሩልኒ ሆነ ብሎ ላገሩ መንግሥት ላከ። የኢጣልያ መንግሥት ደግሞ ሀኪም ነራሲኒ የተናገረው ቃል እውነት መስሎት አዲስ አበባ ለነበረው መልክተኛው ለሀኪም ትራብርሲ፣ ራስ መኰንን አዲስ አበባ ሲመጡ ባስራ ሰባተኛው ክፍል ውላችን ነገር ሊአግዙነ ነውና ሲመጡ ቶሎ ሂደህ ተነጋገር ብሎ ላከ። ሀኪም ትራብርሲ ግን መቸም ሸንክ ነበረና ምንም ነገሩ እውነት ባይመስለው ወዲአው እራስ መኰንን አዲስ አበባ እንደገቡ ሂዶ ለነራሲኒ ባበሉለት ቃል እባከዎ ያሥራ ሰባተኛውን ክፍል ነገር ያሳምሩልነ ብሎ ተናገረ። ነገር ግን ወዲአው የማላገጥ መሆኑን አይቶ ወደስፍራው ተመለሰ። ራስ መኰንን በሀኪም ነራሲኒ ሞኝነት ሲደንቃቸው አድረው በማግሥቱ ከቤተ መንግሥት ተገናኘነና፣ ኧረ በል አፈወርቅ ይሄ ነራሲኒ የሚሉት ሀኪም እንዲህ ዞላ ኑሯልን፡- አንተ ግን እጅግ ብልህ ነው ስትለኝ ነበረ፤ እውነት እኔ የገዛ አገሬን ኢትዮጵያን በኢጣልያ ጥግ ትኑር ብየ ለሱ መንግሥት አግዝ መስሎት ነው ወደሮማ መላኩ፡- ብለው ነገሩኝ። ከዚአው የነበሩ ጥቂቶች ሰዎች እሄን ሰምተው፣ ኧረ በል አንተ የነበርህበት አገር እንዲህ ያለ የፈረንጅ ደላጎም ያበቅላልን ወይስ በእባካችሁ ኢትዮጵያን ለመግዛት አምሮታል፡- ብለው ጠየቁኝ። እኔ ግን የኢጣልያን ነገር አውቅ ነበረና ባንድና በሁለት ሰው ምክኛት እንደኢጣልያ ያለች አገር መነቀፍ አይገባትም አልሁኝ። እንዲህ ያለውን ትንንሹን ነገርስ ወዲያ እንተውና ወደ ዋናው ወደ ጦርነቱ ነገር እንመለስ።

ቅድም እንዳልሁት ሁሉ የኢትዮጵያ ጦር ወደ አዱ የተጓዘ ጊዜ ካዳጋሙስ ተነሥቶ ወደ አዱ ትይዩ ተጓዘ። የዚህን ጊዜ ከኢጣልያዎች ጋር የነበሩት ያጋሜ ገዢዎች እነራስ ስብሐት የኢትዮጵያ ሠራዊት እንደገነገነ የኢጣልያ ጦር እንደመነመነ ተጋፍቶ እንዳያጋፋ አዩትና ከድተው ብዙ የኢጣልያ ሰው ፈጅተው ላጤ ምኒልክ ገቡ። ከዚህ ወዲያ የኢጣልያ ጦር ቅስሙ መሰበር ጀመረ፣ ካንዱ ሰፍራ ወዳንዱ ስንቅ መቀባበል የማይሆንለት ሆነ። በየዙሪአው በየጀርባው በየ ዱሩ ሁሉ የራስ ስብሐትና የደጃች ሐጎስ ተፈሪ ጦር ስንቁንም ይቀማው፣ ሰውንም ይፈጀው፣ የስልኩንም ሽቦ ይበጥስበት፣ መከራን ያሳየው ገባ። የኢጣልያ ጀነራል ባራቴሪ ድሮ የሚአደርገው ጨነቀው። አብሮት የነበረውን ጦር በየሰፍራው እኩሉን የስልኩን ሽቦ ጠብቅ፣ እኩሉን ያዲግራትን ምሽግ ጠብቅ፣ እኩሉን ስንቅ አመላልስ፣ እኩሉን ሽፍታ አደጋ እንዳይጥልብነ ጠብቅ እያለ በየሰፍራው በታተነው፤ ሰፈሩም እያደረ እንደ መብዛት ሁሉ እያደረ አነሰበት። ነገሩ እያደረ በኢጣልያ ከበደበት ከጥቂት ጦር እንገላገላለን ያበሻ ጦር አይቆምልነም ሲል የነበረው ድሮ ጨነቀው፣ ጠበበው። ውሀ ተባሕር ወዲያ በመርከብ ተጭኖ መጥቶ እንዳረቂ በብርጭቆ ተለክቶ ተናኝቶ የበቅሎ የፈረስ ገለባና ገፈራ ተፈረንጅ አገር መጥቶ ጫማው ልብሱ ትምባሆው ሳይቀር ከባሕር ማዶ መጥቶ ካበሻ ጋራ ለመዋጋት እጅግ የጨነቀ ነገር ሆነበት። ያም ሆነ ያም ሆነ የኢጣልያ መንግሥት አንድ ጊዜ የሁለትና የሶስት ያበሻን ነገር እናዋቃለን የሚሉ ሰዎች ቃል ሰምቶ ነገሩን ሳያውቅ ጀምሮታልና የነገሩን መክበድ ባየው ጊዜ ብዙ ጦር ታገሩ አዘዘና የፊት የፊቱን እንደተሰናዳለት ይሰድ ጀመረ፤ አሳቡ ግን የበቃውን ያህል ጦር ለመስደድ ነበረ። በዚህ መካከል ገና ሶስት እልፍ ወታደር ከሙቶ መድፍ ጋራ ባልዲሴራ የሚባል አንድ ጀነራል ከሁሉ በላይ ሹሞ ሰደደ። እኩሉም ከመርከብ እየወጣ ወደ አዱ ሲጓዝ እኩሉም ገና በመርከብ ሲጓዝ ሳለ ጀነራል ባራቴሪ ተበላዩ የተሾመው ጀነራል ባልዲሴራ ሳይደርስ ተሻምቶ መዋጋት ፈለገ። ተዚአ ወዲአማ በከንቱ ነው የኢትዮጵያ አምላክ መቸም የኢጣልያን ሁሉ ነገር እንደ ጥቅመ ሡናዖር ጎንፃ እንደ ባቤል ቋንቋ አደረገው። ባንድ ወገን መንግሥት አበሻ ባለው ጀነራል በበላዩ ሌላ ሹሞ በሽሽጎት ሲሰድ፣ ባንድ

ወገን ደግሞ ያው መንግሥት አበሻ ለነበረው ጀነራል ካሁንን አሁን ድል የማድረግኸን ወሬ እንጠብቃለን እያለ ላከ። ጀነራል ባራቴሪ ግን ውስጥ ለውስጥ በበላዩ ተሹሞ ሌላ ጀነራል መሄዱን በምስጢር ደብዳቤ ከወዳጆቹ ደርሶለታል። በዚህ የተነሣ እስከ ዛሬ እንዲህ ማስኘ ክብር በማገኝበት ጊዜ እንዲህ ሌላ በላየ ተሹሞ እኔ በታች ልሆንና ድልም ብናደርግ ክብሩ ሞገሡ ለሱ ሊሆን? የዚያ የዚያስ ከዚህ ያለውን ጦር ይዤ እኔ እገጥማለሁ ብሎ ቅዳሜ ማታ በሚአዝያ በሀ ሁለት ቀን ወደ አዲ ሌሊቱን ሲገሠግስ አደረ። የዚያን ቀን መገሥገሱ በበነጊአው እሁድ ነበረና ሁሉ ወደቤተክርስቲያን ሲሄድ ባዳጋ ከሰፈር የቀረውን እፈጃለሁ፣ ድሉ እርግጥ የኔ ይሆናል ነበረ አሳቡ። ብልሀቱ ብልሀት ነበረ፣ ነገር ግን ከሰው ብልሀት የሥላሴ ፈቃድ ይበልጣልና ነገሩ ለብቻው ሆነ።

ቅዳሜውን ሲገሠግስ ጦሩን በሶስት ወገን እንዲጓዝ አደረገ ነገር ግን የሚደርሱበት ጊዜው የሶስቱም ወገን አንድ ጊዜ እንዲሆን ነበረ። ለሁሉም ነገር ወታደሩ ሌሊቱን ሁሉ በጀርባው ከባድ ኮረጆውን በጫንቃው ጠበንጃውን በቀኝ ጎኑ የጥይት ቀረጢቱን በግራ ጐኑ የውሀ ታኒካውን ተሸክሞ የገረረ ከባድ ጫማውን እስከ ጕልበቱ አጥልቆ ደልቀፍቀፍ እያለ በዚያ ጭንጫ፣ በዚያ ሙቀት፣ በዚያ አቀበትና ቍልቍለት ያ ሁሉ ፈረንጅ ያ ሁሉ ጐበዝ ያ ሁሉ ወጣት ልዥ ባገሩ እንዲአ ሲአምርበት በሰው አገር ላሊበላ ሳሚ መስሎ ኮርፈፍ ኮርፈፍ ሲል ታገሩ ወጥቶ ተናቱ ተላቅሶ ከወዳጆቹ ተሳስሞ ተጌትነቱ ከደስታው ታገሩ ተወንዞ ተነጥሎ ወዙን በግምባሩ እያንጠበጠበ በርሀብ ጐኑ ተጣግቶ በጥማት ልሳኑ ታስሮ ሲማስን ሲደክም ሲንደላቀፍ አድሮ ሳያርፍ ወዙን ሳያደርቅ ሲነጋጋ አባ ገሪማ ደረሰና መድፉን ጠመደ ገና ቃታው ከደረቱ ሲዘልበት የጠበንጃውን ቃታ ከፈተ ጦርነት ተጀመረ። ከዚያማ ወዲአ ምን ያነጋግራል አሞራው ሽዌ አዳጋ እንደተጣለበት ባየ ጊዜ የቸኮለ በሌጣው ያልቸኮለም በኮረቻው እየተሰካ እየፈከረ እየተንደቀደቀ ገባበት። ከሠራዊቱ አንዱ ወገን ወደ እሩቅ ስፍራ ለቀለብ ጭነት ሂዶ ነበረ አንዱ ወገንም ጀነራል ባራቴሪ እንዳለው ሁሉ ወደቤተክሲአን ሂዶ

ነበረ፣ የቀረው ግን ገና እንቅልፋን አላሳብ ተኝቶ ነበረ። የኢጣሊአ መድፍ ነው በማለዳ የቀሰቀሰው። ጥንቱንም ደፍሮ የኢጣልያ ጦር መጥቶ አዳጋ ይጥልብናል ብሎ ያሰበ አልነበረም። ነገር ግን አይጥ ለሞቷ የድመት አፍንጫ ታሸታለች ሁኖ ጀነራል ባራቴሪ አቅሙን ሳያውቅ ጦሩን ሳይቆጥር ያን ሁሉ ሰው አላበሳው ገፍቶ ካንበሳ አፍ ጣለው። እንደውነት ግን ፊት የደረሰው የኢጣልያ ጦር አሳምሮ ተዋጋ በወተድሊ እያንገበገበ አንዱን ወገን ሰበረና እየተከተለ ተመህል ገባ። ነገር ግን ከዚያው ታፍሮ ቀረ አልተመለሰም ጀነራል አሪሞንዲን የመሰለ ጀግና ከብዙ መኳንንት ጋራ ከዚያው ወድቆ ቀረ። አልበርቶኔን የመሰለ ብርቱ ጀነራል ከብዙ ጀግና ጋር ተመህል ታፍኖ ቀረና ተማረከ። የቀረውን ምርኮ ነገርማ ምን ያቈጣጥራል፡- እንዲአው አሞራው ሸዌ አፈሰና አስቀረው። በቀረውስ ምን ሊሆን ምንና ምን፡- የሸዋ ፈረሰኛ የጎጃም እግረኛ የትግሬ ነፍጠኛ ያማራ ስልተኛ ከቦ ያናፋው፣ ይቈላው፣ ያንደገድገው ጀመር። የኢጣልያው ጦር አለቃ ጀነራል ባራቴሪ ነገሩን ባየ ጊዜ፣ ነገሩ ገባውና ለካን እንዲህ ኑሯልና እንዲአ ቀላል ነገር ሲመስለኝ እያለ በፈረስ ተጋብቶ ወደኋላው ተሸመጠጠ። ያ ሁሉ አላበሳው የመጣ የኢጣልያ ጀግና አለ ስፍራው ገብቶ አለ ፈረስ አለ ምን በዚያ ጠጠር በዚአ ቁልቍለት በዚያ ጠባብ መንገድ እንዴት አድርጎ በከባድ መጫሚአ እሩጦ ያምልጥ፡- እንዲአው ብቻ ከንዝርት የቀለለ የጁየ ተነብር የፈጠነ በጌምድሬ ተቋንጣ የደረቀ ትግሬ እየደረሰ ፈጀው አሰጣው ዘለሰው። ዋናው ሹም ግና በጠገበ ፈረሱ ሁኖ የሶስቱን ቀን ጎዳና ባንድ ቀን አደረሰው አመለጠ። ይሄ ሁሉ ሲሆን የኢጣልያ ጦር መንገድ ጠቦት ገና ወደኋላ ቀርቶ የነበረ ሁሉ ነገሩን ሳያውቅ ወደ ጦርነቱ ሲጓዝ ነበረ። ነገር ግን የጀነራል ባራቴሪን መሸሽና የጦሩን መፈታት ባየ ጊዜ ያ ሁሉ ወደኋላ የነበረ መድፈኛ መጫኛውን በጐራዴ እየቆረጠ መድፉን እየጣለ በመድፉ ስፍራ እሱ እየተተካ በጋሥሱ እየጋለበ አስመራውን ገባ። ካንድ ላይ ብቻ አስራ ስምንት መድፍ አንድ ጊዜ ሳይተኮስ እስከ ጥይቱ እስከ መንኮራኩሩ ወድቆ ቀርቶ ተያዘ። እንደውነቱ ግን መንገዱ ጭንቅ ጠባብ አቀበት ቍልቁለት ባይሆንና ያባራሪውን ፈረሰኛ ባያስቸግረው ከኢጣልያ ጦር አንድ ለዘርም አያመልጥ ነበረ። ነገር ግን የኢጣልያ ጦር ምንም

አዳጋ ለመጣል ሌሊቱን ሙሉ ሲገሠግሥ አድሮ ቢደክም ቀጥሎም በጦርነት በደከመ ጉልበቱ በባዶ አንጀቱ ሲሮጥ ሲአባርር ሲገፋ ሲጋፋ ልሳኑ በውሀ ጥም ታስሮ አካላቱ ሁሉ በልዞ በደም ተለውሶ ሳለ ብዙ ሰው አምልጦ አስመራ ገባ። አጤ ምኒልክ ያን ሁሉ መድፍ ያን ሁሉ ነፍጥ ኢጋፈው ይዘው ያን ሁሉ ምርኮኛ በፊት እየነዱ ፊት ያዲግራትን ምሺግ ሰብረው ቀጥለው ወደ መረብ ለመቈልቈልና አስመራ ያለውን ጦር እስከ ባሕር ለማባረር አሰቡ። ኋላ ግን ሠራዊተዎ ሁሉ ሶስት ወር ሙሉ ትግሬ ላይ በርሀብ ተጐድቶ ነበረና ከርሞ ለመመለስ ወደሸዋ ተመለሱ።

ዳግማዊ ምኒልክ በዚአ ደግነተዎ በዚአ መሐሪነተዎ ላይ የራስ መንገሻ ዮሐንስን ምክር ሰምተው ካዷ ጦርነት በማግሥት አንድ ክፉ ሥራ ሠሩ ነገሩም እንዲህ ነው ጀነራል ባራቴሪና እራስ መንገሻ ከዋቲት ላይ የተዋጉ ጊዜ እራስ መንገሻ ድል መሆኑ በባሽ ብዙቅ ኃይል ነበረ። በዚህ የተነሣ ራስ መንገሻ በባሽ ብዙቅ ብርቱ ቂም ይዞ ተቀምጦ ሳለ ያዷ ጦርነት መጣና ካዷ ጦርነት ላይ ብዙ ባሽ ብዙቅ ለፈረንጆች ሎሌ ነበረና ሲዋጋ ከድሉ ላይ ተማረከ። እራስ መንገሻ በዚአ ቂሙ የተማረከው ባሽ ብዙቅ ሁሉ እጅና እግሩን ይቆረጥልኝ እሱ ነው ከዋቲት ላይ የተዋጋሁ ጊዜ ለነጮች እረድቶ ድል ከመሆን ያደረሰኝ ብሎ ለጃንሆይ ተናገረ። ዳግማዊ ምኒልክ ምንም እንዲህ ያለውን ያረመኒ ቅጣትና ጭካኔ ባይወዱት የራስ መንገሻ አነጋገር ለጊዜው አስገረመዎና እሺ ብለው ያን የተማረከውን ሁሉ ባሽ ብዙቅ እጅ እግሩን አስቆረጡት። የተቆረጠው ባሽ ብዙቅም ቁጥሩ ከ፬፻ ይበልጥ ነበረ። በዚህ ነገር ድፍን ኤውሮፓ ተደነቀና ነገሩን የሰማ ሁሉ እንዴት! እንዲህ ያለ ያረመኒ ስራ እስከ ዛሬ ድረስ ኢትዮጵያን በመሰለ የክርስቲያን አገር አለን፡- ብሎ እጅግ ነቀፈ። ነገሩ እውነት ነው ያስነቅፋል። እንዲህ ያለውን ያረመኒ ቅጣት ከዚህ በፊት የነበሩት ደንቆሮዎች ነገሥታት ቢአደርጉት አነሰና ዛሬ ብርሃን በወጣበት ብዙ ነገር በታወቀበት በዳግማዊ ምኒልክ ጊዜ መደረጉ ያሳዝናል። በቀረውም እስቲ ባሽ ብዙቅስ ላገሩ ትቶ ለባዕድ እረዳ ተብሎ በራስ መንገሻ ልሳን ተመከሰስ ተመወቀስ እጅ እግሩን ተማጣት ደረሰ በዚህማ ተሆነ እራስ መንገሻ

ይልቅ ሳይቸግረው ያስር ነጋሪት አገር አንድነት እየገዛ ባንድ ወገን ላጤ ምኒልክ የታመነ ሎሌ መስሎ ደጉ ምኒልክ እንዲአ ወዶ ሲአስወድደው አክብሮ ሲአስከብረው አገር ሰጥቶ ራስ ወርቅ አስሮ ሲአሞግሠው ሳለ ባንድ ወገን ለንግሊዝ መንግሥት እየላከ እባካችሁ እገዙኝ ያባቴን አልጋ ያባቴን ዘውድ የማይገባው ኃይለኛ ቀምቶኝ አይቀር ሲልና ዳግማዊ ምኒልክን ሲከስ አልነበረምን፡- ያውም አንድ ጊዜ ሁለት ጊዜ ብቻም አልነበረ ብዙ ጊዜ ነው። ያዱ ጦርነት ጊዜም ሳይቀር ባንድ ወገን ላጤ ምኒልክ የረዳ መስሎ ከኢጣልያዎች ጋር እየተዋጋ ባንድ ወገን ውስጥ ለውስጥ ለንግሊዞች እባካችሁ ኃይለኛ ያባቴን መንግሥት እንደቀማኝ አይቅር አባቴን በቴዎድሮስ ጊዜ እንዳገዛችሁ እኔንም እገዙኝ ብሎ ላከ ነገር ግን እንግሊዞች ሞኞች አይደሉምና መንግሥት ለማይገባው ለራስ መንገሻ አግዘው ከውነተኛው ባለ መንግሥት ከሰሎሞን ልዥ ከዳግማዊ ምኒልክ ለመጣላት ጥንቱንም አልሞከሩት አይሆንም ብለው ላኩበት። እንዲህ ባሽ ብዙቅ አይቀጡ ቅጣት ከተቀጣ ይሄን ሁሉ ላደረገው ለራስ መንገሻ እንዴት ያለ ቅጣት በተገባው ኑሯል፡- እንደ እውነት ሰው ሳይፈሩ የነፍስን የሚናገሩ ቢሆን ባሽ ብዙቅ አጤ ምኒልክን አልከዳም ውሸት ነው። ባሽ ብዙቅስ የተወለደበት አገሩ ምሽቱ ልዦቹ አሮጌዎች እናት አባቱ እርስቱ ንብረቱ ያለበቱ አገር ባጤ ምኒልክ ፈቃድ ከኢትዮጵያ መንግሥት ተሸርፎ በኢጣልያ መንግሥት እጅ ቢሆን ያን አገሩን ለሚገዛው ጌታ በውዱም በግዱም አገዘ ውሻ ጌታውን እንጂ የጌታውን ጌታ አያውቅምና አገሩን ለያዘው ቆርሶ ለሚአጕርሰው ቀዶ ለሚአለብሰው ላዲሱ ጌታው አገዘ፣ እሄ ከዳ ያሰኘዋል፡- አሁንም እንደውነት ቢሆን ባሽ ብዙቅ አላገባብ በግፍ በራስ መንገሻ ተከሶ ተቀጣ በማይገባ በግፍ እጅ እግሩን አጣ። እንደውነት መቀጣት ይገባው የነበረስ ከመረብ መለስ ታለው አገር የነበረው የትግሬ ሰው የገዛ የጌታውን የዳግማዊ ምኒልክን ሠራዊት በየዋሻው በየዱር በየገደሉ ተቀብሮ እየተኰሰ የፈጀው ትግሬ ነበረ። ያውም ቢሆን ቅጣት ማለት እጅና እግር እየቆረጡ፣ አካል እያጎደሉም አይደለ፤ እንዲህ ያለው ቅጣት ያረመኒ ቅጣት ነው እንጂ በልበ ብርሃኑ በዳግማዊ ምኒልክ ጊዜ የተገባም አይደለ። ቅጣትም ቢሆን እንዲአው አፍ እንዳመጣው ዕለቱን

ወዲአው በተናደዱበት ጊዜ ይቀጣ ብሎ መፍረድ አይገባም ሥላሴ የፈጠሩት ሰው እንዲህ በዋዛ መቀጣት አይገባውም። ሥላሴ አሳምረው የፈጠሩትን አካል አለሥፍራው እንደበቀለ እንጨት መቁረጥና ማበላሸት አይገባም፤ የሰው አካል ተመልሶ እንደዛፍ አያፈጠፍጥም። ቅጣቶም የሚገባው ቢሆን ነገሩን አይቶ አስተውሎ፣ አውጥቶ አውርዶ፣ መርምሮ ተጨንቆ አውሎ አሳድሮ፣ ፈርዶ አስፈርዶ ከዚአ በኋላ እውነት ለቅጣት የተገባ ሰው ከሆነ የሚታሠረውን ማሠር፣ የሚሞተውንም ወዲአ እስታሥራ ሁለት አካላቱ ጻእረ ሞት እንዳይበዛበት አድርጎ ዓይኑ እንዳያይ አድርጎ ሸፍኖ መግደል ነው። እንዲህ ያለውን ምክር ለኔ ተገብቶኝ አልመከርም፣ አይገባኝም፤ ነገር ግን አንድ ጊዜ አንዱ ደፍሮ ታልተናገረ ነገር አይታወቅም፣ ክፉ ልማድ መልካም መስሎ ይኖራል። ይሄን ሁሉ ነገር ብዙ ጉዳይ ያለበት ንጉሥ አስተውሎ ብቻውን ማስተካከል አይሆንለትም መኳንንቱ ግን ለንጉሡ እድሜ የሚሆነውን ላገር የሚጠቅመውን ነገር ለንጉሡ መምከር ይገባቸዋል እንጂ ዝም ብሎ ፈርቶ መቀመጥ አይገባም። ደግ ነገር መምከር መደገፍ ነው እንጂ መድፈር አይባልም። አሁን እሄን ያየ ከዛሬ በፊት እንደነቀፈኝ ሁሉ ደንቆሮ የሆነ ያገሬ ሰው እንዴት ደፍሮ ጣፈው ብሎ እንዲሰድበኝ አውቃለሁ፤ ብልህ የሆነ ሰው ግን እንኳን ይነቅፈኝ እሱም ጭምር በተቻለው የሚጠቅም ነገር ለንጉሡ ይመክራል። እኔም ዓለሙ ሁሉ የሚለውን ኢትዮጵያን የሚአስነቅፈውን ነገር ታላየሁ አልተናገርሁት። በቀረውም የኤውሮፓን ሥራት ማየት ማስተዋል ማድነቅ መምሰል ነው። ጥንት በኤውሮፓም እንዳበሻ ያለ የሞኝነት ሥራ ይሰራ ነበረ ነገር ግን እያደረ እውነት ብልህት ተበዛ ዘንድ ያ ሁሉ ክፉ ልማድ ቀረ። እንዲህ መሆኑ የሞኝነት ነው ወይስ የብልህነት፡- የኤውሮፓን ሥራት የሞኝነት ነው የሚል የለም፤ የሞኝነት እንደሆነ እንደ ኤውሮፓ ሞኝ መሆን ይሻላል። አሁንስ ወደኋላ ልመለስና ያዷን ጦርነት ነገር ልጨርስ።

የኢጣልያ መንግሥት በዚህ ድል እጅግ አዘነ ለድፍን ኤውሮፓም ብዙ ገረመው። የኢጣልያ ወዳጅ የሆነ በብርቱ አዘነ የኢጣልያም ጠላት የሆነ ላበሻ

አግዞ አይደለም እንዲአው ከነሱ በፊት አበሻ ሂዶ አገር ለመያዝ በመጣሩ ተመቅኝቶ ነበረና ደስ አለው።

የኢጣልያ መንግሥት በዚህ የተነሣ ምንም ቢሆን ቂማችነን ሳንወጣ አንቀር ብሎ እልቅ የሌለው ጦር ከኢጣልያ ለመስደድ ተሰናዳ። ነገር ግን ሕዝቡ አንድነት ጮኸና ጥንቱንም ካበሻ ጋር መጣላታችነን አልወደድነ ነበር፤ አበሾች ምን አሉ ተገዛ ቤታቸው አርፈው በተቀመጡ፡- አሁንም ተንግዴህ ሰዋችነን በማይገባ ከሰው አገር እየሰደድነ አናስጨርስም ገንዘባችነንም በከንቱ አናበላሽ ብሎ ለመንግሥት አስቸገረ። ጥንቱንም ከኤውሮፓ ሁሉ እንደ ኢጣልያ ሰው ያለ ፍቅር ወዳጅ ሰው መጋፋት የማይወድ አይገኝም ፍርድ አዋቂ ነው። በፍቅር እንኑር እንንገድ ተሰው ቤት በፍቅር እንጂ በጠብ በተንኮል አንሂድ ነው የሚል። የዚያን ጊዜ ጦርነት የፈለጉት የደንቆሮ ነገር ሰምተው ጥቂቶች ሹሞች ነበሩ እንጂ አገሩ አልነበረም። እነዚያም ወዲአው ተሻሩ ዛሬም ሞቱና ሌላ ፍቅር ፈላጊ ተተካባቸው። ለሁሉም ነገር መቸም የኤውሮፓ መንግሥት ምንም ቢሆን ደሀ ያልወደደውን ስራ ማድረግ አይሆንለትምና ጦር መስደዱን ተወ። ነገር ግን ኋላ ለተሾመው የጦር አለቃ ጀነራል ባልዲሴራ ከዚያው ያለውን ሁሉ ጦር ሰብስበህ መከት ያዲግራትንም ከምሽጉ ተቋርጦ የቀረ ጦር አድን ብሎ ወዳስመራ ላከ። ይሄው ሹም ከጦርነቱ በኋላ የደረሰውን ሁሉ አንድ ሶስት እልፍ ያህል ጦር ሰብስቦ ወደ አዲግራት ተጓዘና ማይ መሬት ሰፈረ። አጤ ምኒልክ ግን ሠራዊተዎ ተርቦ ነበረና ከርመን እንመለሳለን እንሂድ ብለው እራስ መኰንንን አዳጋሙስ ላይ ትተው ተጓዙ።

በዚህ መካከል የኢጣልያ መንግሥት እስሮቻችነን ይመልሱልነ ብሎ እርቅ ተደራደሩ። የሮማ ሊቀጳጳስም አባከዎን የታሰሩትን ያገሬን ሰዎች ይፍቱልኝ ብሎ አንድ አቡን ወደ አዲስ አበባ ላከ ነገር ግን አልሆነለትም። አጤ ምኒልክም ለኢጣልያ መንግሥት ምን ከፋ እርቅ ተወደዳችሁ ከጥንት የተጣላንበትንም ነገር ባስራ ሰባተኛው ክፍል የነበረውን ቃል ትታችሁ የኢትዮጵያ መንግሥት እራሷን ቀጥ ለበጥ አድርጋ ችላ መኖሯን በማንም በማን መንግሥት ጥግ አለመኖሯን ለድፍን ኤውሮፓ አስታውቁ፤

አለፈቃዴም ተሻግራችሁ የያዛችሁትን መሬት ቶሎ ልቀቁ እኔም እስሮቻችሁን እስከ ዛሬ የቀለብሁበትን ገንዘብ መልሱልኝና እለቅላችኋለሁ። ጥንት በፈቃዴ የሰጠኋችሁን አገር ግን መረብ በመለስ ለናንተ እተውላችኋለሁ፤ የሌላ የሌላውን ደንበር ግን ዝግ ብለን በፍቅር እናስተካክላለን አሉ። የኢጣልያም መንግሥት እሺ ብሎ በዚህ ታረቁ እስሮችም ተመለሱ።

ካዱ ጦርነት ወዲህ የኢትዮጵያ ስም ፀሐይ ባየው ሁሉ አገር ታወቀ። ከዚያ በፊት ኢትዮጵያ ምንም ከጥንት ከመሰረት ጀምራ ራሷን ችላ ብትኖር ከቶውንም በነፈርዖን ጊዜ ተባሕር ወዲያ እስከ ምስር ባንድ ወገንም እስከ አደን ካረብ አገር ተሻግራ ብትገዛ በኤውሮፓ ስሟ ያህዛብ አገር ናት ትባል ነበረ። በዳግማዊ ምኒልክ ኃይል፣ በዳግማዊ ምኒልክ እውቀት ዛሬ ግን ኢትዮጵያ የውነተኛ ስሟ ተገለጠ ከውነተኛ መዓርጓ ገባች። የኢትዮጵያ ዓለም ካዱ ጦርነት ወዲህ ተጀመረ። እቴጌ ጣይቱ ትንቢት ይቀድሞ ለነገር ነውና እንደ ምንቸት ውሀ ፍል ውሀ ይባል ለነበረው የርጉፋን የቆማጣ መከማቻ ለነበረው ገጠር አዲስ አበባ ብለው ስሙን ቀደሱት። እውነትም ከዚያ ወዲህ ኢትዮጵያ አበበች። የዚህን አበባ ፍሬውን የኢትዮጵያ ሰው በደስታ ለመብላት ያብቃው ተካዮችንም ዳግማዊ ምኒልክንና ጣይቱ ብጡልን የኢትዮጵያ አምላክ ከድሜ ላይ እድሜ ይቀጥልላቸው። ሞት አይቀርምና ለኋላውም በዚህ አላፊ መንግሥት የማያልፈውን መንግሥት ይተካላቸው። አሁን ደግሞ አዲስ ዓለም ብለው ስም አወጡ፤ ይሄውም ስም ለኢትዮጵያ ትንቢት ሁኖ የውነተኛ አዲስ ዓለም ያምጣላት። ዳግማዊ ምኒልክንና እቴጌ ጣይቱን አሰንብቶ በነዚህ ኃይል ድንቁርና ጠፍቶ በሰዉ ጥበብ ባገሩ ብርሃን እንዲገባበት እንዲሞላበት እንደ ኤውሮፓ አገር ሁለንተናው እንዲሰራበት ታይቶ የማይታወቀው ባበሻ ሰው እጅ ተሰርቶ እንዲታይበት ያድርግ። አዲስ ዓለም ማለት ትርጉሙ ይሄ ነው።

# ለኢትዮጵያ ሣህል ወምሕረት።

## አፈወርቅ ዘብሔረ ዘጌ።

አሁን እሂችን ትንሽ ታሪክ ጽፌ ስጨርስ ዳግማዊ ምኒልክ አዲስ አበባ ጃን ሜዳ ላይ ሊቃውንት እስከ መኳንንት አስከትተው ጉባኤ ሁኖ በደብዳቤ አድርገው የሰጡትን የምክር አዋጅ ቅጅውን ታገሬ አንድ ጃንሆይንና ኢትዮጵያን የወደደ ወዳጅ ጽፎ ሰደደልኝ። እኔም እንዲህ ያለ ብርቱ ቃል ለኢትዮጵያ የሚጠቅም ነገር የተጻፈበት የምክር አዋጅ ሳይታተም አይቀር ብየ እሄው ከዚች ትንሽ ታሪክ ጋራ እንዲታተምና የኢትዮጵያ ሁሉ ሰው እንዳይረሳው እንዲአነበው ብየ አሰብሁ። እንዲህ ከታተመ ዘንድ ለዘላለሙ እንዲታወቅ ማንም እንዲአነበው ምክሩ በልቡ ተሰርጾ እንዲቀር ይሆናል። ካልታተመ ግን ከቤተ መንግሥት ብቻ ከመድበል ተጽፎ ይቀርና ሕዝቡ በቶሎ ረስቶት የኋላም ልዥ ሳያውቀው ይቀራል ብየ ነው። እንዲህ ያለው ቃል ልብ ላለው ያሳዝናል። ኢትዮጵያን የወደደ የኢትዮጵያን መልማት የኢትዮጵያን ደስታ የኢትጵያን ትልቅነት የወደደ ሰው ይሄን የጃንሆይን ቃል አዝኖ ተክዞ መቀበል ይገባዋል። አዝኖ ተክዞ ማለቴ እንዲህ ያለ እናት ንጉሥ የሞቱን ነገር አስቦ ለኢትዮጵያ የሚበጀውን አውቆ እንዲህ ያለ የተገባ የጣፈጠ ከልብ ጠልቆ የሚገባ ምክር ለሕዝቡ መስጠቱ ተሞቱም በኋላ ለኢትዮጵያ የሚሆነውን ላገር የሚጠቅመውን ለሕዝቡ የሚአከብረውን ነገር ማሰቡና መምከሩ እጅግ ያሳዝናል ማለቴ ነው፡

እርግማነዎ ግን በከንቱ ነው እርሰዎም ባይረግሙት ለተገባው ለባለመንግሥቱ ትቶ ላልተገባው ሰው ላልተገባቸው መኳንንት የተከተለና ለነሱ ደሙን ያፈሰሰ ደም ያፈሰሰ ሥጋ የቈረሰ ወታደር የኢትዮጵያን ጤና የኢትዮጵያን ስፋት የጠላ ነውና በሥላሴ ዘንድ የተረገመ እሱ እርጉም የልጅ ልጁ እርጉም እንደሆነ የታወቀ ነው። መርገምስ አለ አገባብ መንግሥት ግዛት አገር ደንበር መጋፋት የሚወዱትን መኳንንት ብቻም አይደል ለነዚሁ የሚአግዘውን ወታደር ይልቅ በብርቱ መርገም ነው። በቀረውስ በኢትዮጵያ

ምን ባለጉልት ምን ባላባት ባለ ግዛት አለ፡- የኢትዮጵያ ጌታ ከላይም እግዚአበረሄር ከታችም የውነተኛው ንጉሥ ነው ይሄውም ንጉሥ የሰሎሞን ዘር እንደ ዳግምዊ ምኒልክ ያለ ነው። የሱም ዘር በኢትዮጵያ ይተካል የሱ ሀረግ እየተሳበ እየለመለመ ሳይበጠስ ይኖራል መበጠሻ አይኑረው። ከዛሬ በቀደም ኢትዮጵያ ተጐድታ መኖሯ በሕዝቡ መደንቆርና ባላባት ባላልጋ እኔ ነኝ ባዩ ስለበዛ የውነተኛው ባለመንግሥት ባለመታወቁ ነበረ አሁን ግን ይሄ ሁሉ ታውቋል ተገልጧል የኢትዮጵያን ትልቅነት፣ የኢትዮጵያን ስፋት፣ የኢትዮጵያን አንድነት የወደደ አንድ የውነተኛው ባለመንግሥት የሰሎሞን ዘር ብቻ መሆኑን ይወቀው። ይሄን ግን ያላወቀ ሰው የገዛ ደስታውንም ሳያውቀው አጓጉል ይሞታል።

ይሄን ያህል መናገሬ የልቤን ለማስታወቅና የመሰለኝን ነገር ሸሽጌ እንዳላስቀረው ነው እንጂ እግዚአብሔር ያላወቀዎ የመረጠዎ የገለጻልዎ ጃንሆይ የተናገሩት ቃል ብቻ ይበቃል። በቀረውም እሄው ከዚህ ቀጥላችሁ ታዩታላችሁ።

## የጃንሆይ የዳግማዊ ምኒልክ ቃል።

በ፲፱፻፩ ዓመተ ምሕረት ግንቦት ፲ ቀን አዲስ አበባ ጃን ሜዳ ከሚባል ሥፍራ ጉባዔ ተደርጎ ዳግማዊ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ያዘዙት ቃል ይህ ነው።

ያገሬ የኢትዮጵያ ሰዎች፣ ልጆቸ፣ ወዳጆቸ፤ እግዚአብሔር የገለጻልኝን ምክር ልምከራችሁ። ምክሬንም እግዚአብሔር በልባችሁ እንዲአሳድርባችሁ ተስፋ አደርጋለሁ።

አጼ ቴዎድሮስ የሞቱ ጊዜ ከሳቸው ጋራ የነበረው ሰው ሁሉ ያንዱን አገር አንዱ እደርባለኍ፤ አንዱን ገድዬ እኔ ጌታ እሆናለሁ፤ እያለ ሁሉም ላይረባ ተላልቆ ቀረ።

ከዚህም በኋላ ያጼ ዮሐንስ ሰው የኊነውን የምታውቁት ነው ባገር በሽታ ሳይገባበት ሌላ የባዕድ ጦር ሳይነሣበት በምቀኝነት እርስ በርሱ እንደተላለቀ አይታችኊታል።

አሁንም ልጆቼ ወዳጆቼ አንዱ ባንዱ ምቀኝነት ይቅር፤ ያንዱን አገር አንዱ እኔ እደርባለሁ እንዳትባባሉ። እኔ እስካሁን በፍቅር እንዳኖርኋችሁ እናንተም ተስማምታችሁ በፍቅር እንድትኖሩ እለምናችኋለሁ።

እናንተ አንድ ልብ ከሆናችሁ በምቀኝነት እርስ በርሳችሁ ተዋግታችሁ ካላለቃችሁ በቀር አገራችንን ኢትዮጵያን ለሌላ ለባዕድ አትሰጧትም፤ ክፉም ነገር አገራችነን አያገኛትም፤ ነፋስ እንዳይገባባችሁ፣ አገራችሁን በያላችሁበት በርትታችሁ ጠብቁ፤ ወንድሜ ወንድሜ እየተባባላችሁ ተደጋገፉ፣ የኢትዮጵያን ጠላት ተጋግዛችሁ ተደንበር መልሱ። የኢትዮጵያ ጠላት ባንዱ ወገን ትቶ ባንድ ወገን ቢሄድና ደምበር ቢጋፋ በኔ ወገን ታልመጣ ምን ቸገረኝ ብላችሁ ዝም አትበሉ፤ ያ ጠላት በመጣበት በኩል ኊላችሁም ሂዳችሁ አንድነት ተጋግችዛሁ ጠላታችሁን መልሱ እስከ እየቤታችሁ እስቲመጣ ዝም ብላችሁ አትቆዩ።

ይህነን ምክር ለናንተ መስጠቴ እኔማ በእግዚአብሔር ቸርነት ይህነን ያህል ዘመን ገዝቼ የለምን። ነገር ግን ሰው ነኝና እንግዴህ እስንት ያህል ዘመን እቆያለሁ ስል ነው። አሁንም እኔ እንደተመኘሁት እግዚአብሔር የተጨመረበትና ፈቃዱ ሁኖ ልጄን ቢአቆምላችሁ ከልጀ ጋራ ሁናችኊ አገራችሁን ጠብቁ አደራ ብያችኋለሁ። አደራ የሚአኖሩበት ሰው የታመነ ስለሆነ ነው፤ አሁንም እኔ እናንተን አምኘ ልጀን አደራ ብየ እሰጣችኋለሁና አሳድጉት፣ በብልሀት ምከሩት፣ በጉልበት እገዙት፣ በምክር ደግፉት። ልጀን አደራ መስጠቴ ከልጀ ጋር ኢትዮጵያን አደራ ጠብቁ ማለቴ ነው። እኔም እሄው በገዢዎቹ አለማወቅ በሕዝቡ አለመስማማት የተነሳ ተብዙ ዘመን ጀምሮ ተከፋፍላ የነበረችውን አገራችነን ኢትዮጵያን ማስኘ ተጣጥሬ ይሄው አስፍቻታለሁ። እናንተም ከልጀ ጋራ ሁናችሁ ተሰማምታችሁ የኢትዮጵያ

ደንበር እንዲሰፋ እንጂ አንድም ጋት መሬት እንዳይጠብ አድርጉ ጠብቁ አልሙ። የደጊቱ አገራችን የኢትዮጵያ አምላክ ይገዛችሁ ይጠብቃችሁ።

ከዚህ ቃል የወጣ በሰማይም ነፍሱ በምድርም ሥጋው ልጅ እስከ ልጅ ልጁ የተረገመ ይሁን፣ የኢትዮጵያ ወቃቢ ያጥፋው፣ እኔም ሳለሁ ከፈቃዴ የወጣውን እረግሚአለኍ።

# INDICE DEI NOMI

(d. = ደጃዝማች f. = figlio; fit. = ፊታውራሪ r. = ራስ w. = ወይዘሮ v.= vedi)


ጎሩት(w) page. 17
ሀብቱ(ato) 12
ሀብተ ማርያም 11.
ህንድ(ባሕር) 29.
ኃይሌ(märĬd-azm) 13 14 20 27.
ኃይለ መለኮት(re)10 11 12 14 15.
ኃይለ ማሪያም(d) 17.
ኃይለ ማሪያም(qänäzm) 87.
ሐጎስ ተፈሪ(d) 96.
ላስታ 54.
ሌቃ 32.
ልቻ 28.
ሎጥ 79.
መሀመድ አሊ 27 (v. ሚካኤል)
መሀመድ አንፋሪ 23.
መረብ 82 104 109.
ማርየ(r) 17.
ምስር 23 24 109.
መስተሀት(w.) 37
መስኮብ 73.
መሸሻ ሰይፉ 27 38.
መሸሻ (f. di Teodoro) 15.
መሸሻ ወርቄ 72.
መቀሌ 87 89 90.
መቅደላ 13 24.
መተማ 55 56 57.
ሙና 74 84 85.
መንዝ 28.
ምንጃር 12.
መንገሻ(r.) 57 71 72 74 81 a 83 86 87 102 a 104.
መኮንን (d., r.) 44 52 53 59 66 a 72 88 89 92 a 95 108.
ሚካኤል(r.)27 38 92(v.መሀመድ አሊ.)
ሚካኤል(ስሑል) 25
ማይ መሬት 108
መድኃኔ ዓለም (chiesa) 39.
መገዘዝ 12.
ምጥዋ 48 71.
ሮማ 66 69 95 108.
ሮባ(ato) 63.
ሰላሌ 52 53.
ስሉልታ 26.
ሳልምቤኒ 71 72 74 75
ሰሎሞን 1 39 47 56 a 58 104 112 113.
ስልጢ 41.
ስሑል ሚካኤል 25.
ስሐጢ 48.
ስሜን 17 80 81
ስራህ ብዙ(ato) 14.
ስብሐት (d., r) 71 72 82 96.
ሰናዖር 97.
ስናፌ 87.
ስዩም (fit., d.) 36.
ሰይፉ(ato) 14.
ሱዳን 30.
ሸለንቆት 43.
ሻንቅላ 41 47.

ሸዋ 10 a 15 a 17 a 20 a 22 a 33 a 36 a 41 a 43 a 48 50 a 53 58 83 84 90 99 100 102.
ቀወት 17 26
ባሕር ዳር 26.
በለሳ 74 84 85.
ባልዲሴራ 97 108.
ብሩ(aläqä) 23.
ቢራቱ (fit., d.) 69 70.
ባራቴሪ 86 87 90 a 93 96 97 99 a 102.
በረኸት 12 42.
ቦሰና 42.
በሻህ አቦየ 28.
በሽሎ 29.
ባቤል 97.
ቤተሪአ(lago) 30.
በዛብህ(ato) 11 13 14 15 17 18 20.
በድሉ(ato) 11.
በዳኔ(ato) 27.
በጌምድር 15 20 26 31 37 51 52 54 79 80 100.
ባፈና(w.) 26 27 40
ታሞ 27.
ተራ መስከ 11.
ትራበርሲ 82 a 86 94.
ቱርክ 23 25.
ተሰማ(r.) 88.
ተክለ ሃይማኖት(re) 32 33 35 a 38 49 51 52 88 92.
ተክለ ጊዮርጊስ(atiė) 1 20 a 22.
ቴዎድሮስ(atiė) 1 a 4 10 a 21 24 39 104 113.
ቶዘሊ 88.
ታየ(alqa) 7 8.
ተጎሪ 48.
ትግሬ 21 a 23 25 a 28 30 31 37 47 48 50 a 54 57 71 72 74 81 a 83 87 88 100 102 105.
ነራሲኒ 71 93 a 95.
ነጋሽ(d.) 81.
ነጭ አባይ 30.
አሊ (r.) 10.
አሉላ (r., f. di Gugsa) 17.
አሉላ (r, generale di Giovanni IV) 38 57 74 81 83.
አልበርቶኔ 100.
አማራ 11 41 46 80 100.
አምባላጂ 88 89.
ኡምበርቶ(re) 69.
እምባቦ 32 33 36 a 38.
አሪሞንዲ 100.
አረርቱ 12.
አረርጌ 41 a 47 52 53 71 72 88 93 94.
አሩሲ 44 47.
እርቁ 14.
አረብ 109.
ኤርትራ (ባሕር) 30.
አራያ ሥላሴ(r.) 38 39
አሰል 84
አሥመራ 48 74 82 86 91 101 108.
አሰብ 84.
አሸንጌ 87 88.
አበሻ 6 20 22 23 25 26 69 73 86 89 92 94 a 94 96 97 107.
አባይ 26 27 52 53(v.ነጭ).

አብድላሂ 43.
አባ ዳቂ 32 (ጉበና).
አባ ዳኘው 29 31 35 40 a 42 47 51 53 88.
አባ ገሪማ 99.
አባ ግርሻ 53 (v.ዳርጌ).
ኢትዮጵያ 1 2 6 8 16 19 20 22 a 24 28 40 41 46 a 48 56 57 59 a 63 66 69 70 72 73 77 86 91 93 a 97 103 104 106 108 a 115.
እንሳሮ 63.
አንቶሌኒ 59 70 73 a 79 82 84 85.
አንኮበር 11 14 39 84.
እንደርታ 21.
እንግሊዝ 19 a 21 24 73 103
እንግዳ(r.) 12
እንጦጦ 41 43 a 45 60 63 72 73.
እንጦጦ ማርያም(chiesa) 64.
አኩስም 69 72.
ኤካ 64.
ኤውሮፓ 41 46 59 73 74 83 88 89 102 106 a 110.
አውሳ 23 29 48 84 88.
አዋሽ 42.
አዘዞ 50.
ኢየሩሳሌም 71.
አይሻል 10.
ኢዮአስ(atiĕ) 25.
አዳል 47.
አዲስ አበባ 43 46 52 53 76 81 83 86 94 108 109 111 113.
አዲስ ዓለም 110.
አደን 19 109.
አድዋ 22 86 91 95 97 98 102 103 109.
አዳጋሙስ 91 95 108.
አዲግራት 96 101 108.
አጋሜ 71 96.
እጅግ አየሁ(w.) 18.
አገው ምድር 38.
ኢጣልያ 48 51 59 60 66 68 a 74 77 a 79 82 a 88 90 a 97 99 a 101 103 104 106 a 109.
አፈወርቅ 70 71 95 110.
ከረዩ(ጋላ) 42.
ካሳ(d) 21 22 (v. ዮሐንስ).
ከስም 12.
ከንፈሮ 26.
ከዋቲት 86 102.
ከፋ 29 41 42 47.
ወሎ 10 11 13 20 a 22 26 a 29 37 38 41 47 49 52 54.
ወላሞ 42.
ወሌ ብጡል(r.) 37 40 52 80 81
ወልደ ሥላሴ (r,) 81.
ወልደ አባ ሥዩም 28.
ወልደ ገብርኤል 42.
ወልደ ጊዮርጊስ(r.) 88.
ወልደ ጊዮርጊስ (ababa, asiĕgiĕ) 36.
ወልደ ጻድቅ(azzăż) 27 44 88.
ወለጋ 29 32 41 47
ወርቂቱ(w.) 17 19
ወራቢሌ 43.
ወረይሉ 27.

ዋቄ ደቦ 10.
ውቤ(r.) 13.
ወጋደን 42.
ውጫሌ 59 66 72 77 78.
ዘቢጥ 21 80.
ዘውዴ(r.) 79 a 81.
ዘውዲቱ(w.) 39
ዘጌ 58 70 110.
ዮሐንስ(asiĕ) 1 2 4 5 22 a 31 37 a 39 44 48 a 57 59 66 114 (v. ካሳ).
ዮሴፍ(grāzm.) 76.
የጁ 16 54 80 100.
ይፍራታ 11.
ድላንታ 54.
ደራ(r.)10.
ዶሪ(r.)17
ደረሶ(r.) 32 36 (v. ጠቦ).
ደርቡሽ 48 a 50 54 a 57.
ዳርጌ (ato, r.) 13 14 23 27 44 52 88 (v. አባ ግርሻ).
ደብረ ኃይላ 87.
ደብረ መይ 26.
ደብረ ብረሃን 11 20 39 41.
ደብረ በግዕ 12.
ደብረ ታቦር 37
ደንገል በር 51.
ዳዊት 1.
ደጀን 27.
ጅማ 29.
ጃራ(ato) 14.
ጅሩ 41.
ጀርመን 73.
ጃርሶ (ጋላ) 13.
ጅበላ 52.
ጃን ሜዳ 111 113.
ጋላ 20 29 32 41 42 46 47 52 (v. ከረዩ ጃርሶ).
ጋሊአኖ 90 91.
ጉራ 24 25.
ገርማሜ(d.) 23 27 28.
ጉር ሥላሴ 11.
ጉራጌ 41.
ግሸ 11.
ግቤ 32.
ጉበና (ato, r) 21 23 32 33 41 (v. አባ ዳቂ).
ገበየሁ(fit.) 88.
ጋንዶልፊ 74.
ጎንደረ 26 29 47 49.
ጉንደሬ(truppa) 42 44.
ግንደ በረት 52.
ግድም ጊዮርጊስ(chiesa) 18.
ጎዳጉዲ 23 25 26.
ጎጃም 26 27 32 33 36 38 51 52 54 55 100.
ጉግሳ(r.) 16.
ጠራ 12 20 33 41.
ጠቦ ደረሶ(r.) 32 (v. ደረሶ).
ጣይቱ ብጡል (w., itēgiĕ) 16 17 26 39 40 43 a 46 60 76 a 81 109 110.
ጠጣው(cavallo) 34.
ጨርጨር 29 41 42 72.
ፒአኖ 86.
ፍል ውሃ 46 109.
ፈረንሳዊ 73 84 85.
ፍርኩታ 11.

ፈርዖን 109.
ፈሾዳ 42.
ፍቅሬ ግምብ 18.
ፍንፍኒ46

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY



## ስለደራሲው በጥቂቱ

አፈወርቅ ገ/ኢየሱስ በ1860 ዓ.ም ጎንደር ዘጌ በተሰኘችው ስፍራ ተወለዱ፡፡ የእቴጌ ጣይቱ ብጡል የሥጋ ዝምድና እንዳላቸው የሚነገርላቸው አፈወርቅ በልጅነት ዕድሜያቸው አዲስ አበባ መጥተው አደጉ።

ለዘመናዊት ኢትዮጵያ ሥልጣኔ መስራች የሆኑት ዳግማዊ አጤ ምኒሊክ ያውሮፓን ሥልጣኔ ቀስመው እንዲመጡ ወደውጭ ሀገር ከላኳቸው ብልህ ወጣቶች መካከል አንዱ አፈወርቅ ገ/ኢየሱስ ናቸው።

አፈወርቅ የ20 ዓመት ብላቴና ሳሉ በአጤ ምኒልክ በጎ ፈቃድ ከሁለት ወጣቶች ልጅ ጉግሳ ዳርጌ እና ልጅ ቅጣው ዛማኑኤል ጋር በ1880 ዓ.ም ወደ ስዊዘርላንድ ተላኩ። ከዚያ ከደረሱ በኋላ በገዛ ፈቃዳቸውና ባልታወቀ ምክንያት ወደ ጣሊያን ቱሪን ሄደው በኮሌጅ ኢንተርናሲዮናል ደ.ቤሊ አርቲ ከፍተኛ የሥነ ጽሑፍ ትምህርት ተከታተሉ። ከአድዋ ጦርነት በ1986 በፊት ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው በ1882 በቤተመንግስት ባለሟልነትና በሠዓሊነት ሙያ ያገለገሉት አፈወርቅ፥ በተለይ ከእቴጌ ጣይቱ ጋር በመቃየየማቸው በ1888 ዓ.ም. በስደት መንፈስ ወደ ኢጣሊያ ተመለሱ። በናፖሊ የምስራቅ ጥናት ኢንስቲቲዩት የአማርኛ ቋንቋ በማስተማር የፕሮፌሰርነት ማእረግ አግኝተዋል።

አፈወርቅ በኢጣሊያ ሳሉ ለኢትዮጵያ ዘመናዊ ሥነ ጽሁፍ ዕድገት የበኩር ልጅ ሊያሰኙዋቸው የቻሉትን የአማርኛ መጻሕፍት የጻፉ ሲሆን እንደገና ወደሀገራቸው በ1922 ዓ.ም. እስከተመለሱ ድረስ፥ በግእዝ፥ በአማርኛ፥ በኢጣሊያንኛ እና በፈረንሳይኛ ቋንቋዎች የመማሪያ መጻሕፍት፥ የታሪክ እና የፈጠራ ልቦለድ መጻሕፍትን አሳትመዋል።

አፈወርቅ በ1902 ዓ.ም. ሮማ ባሳተሙት ዳግማዊ ምኒሊክ በሚለው የታሪክ መጽሐፋቸው ከግዕዝ ጽሑፍ ባህል ወደ ዘመናዊ አማርኛ ኪናዊ ሥነጽሑፍ ለተደረገው ሽግግር በተለይ በ1908 ዓ.ም. በሮም ባሳተሟት ጦቢያ-ልቦለድ ታሪክ የፈጠራ ሥራቸው- በኢትዮጵያ የአማርኛ ዘመናዊ ሥነጽሑፍ መሥራች ካሰኛቸው ማእረግ ባሻገር በአፍሪካ ቋንቋዎችም ታሪክ- በሀገርኛ ቋንቋ በመጻፍ የመጀመሪያው ጥቁር አፍሪካዊ የሚል ምስክርነት አግኝተዋል።

ቀደም ሲል ለሀገራቸው በአስተርጓሚነት፥ በጉምሩክ ሥራ ኃላፊነት ነጋድራስነት እና በአምባሳደርነት ሮም ያገለገሉት አፈወርቅ በኢትዮጵያና ኢጣሊያን ጦርነት ወቅት 1924 - 1933 ኢጣሊያን ወገን ሆነው በ የቄሣር መንግስት መልእክተኛነት በሀገራቸው ልዩ በደል ፈጽመዋል በሚል ከነፃነት በኋላ በ1933 የዕድሜ ልክ እሥራት ተፈርዶባቸው በጅማ ጅሬን እሥር ቤት ለ6 ዓመታት በግዞት ቆይተው፥ በእርጅና እና በጤና ማጣት መስከረም 15 ቀን 1939 ዓ.ም በ79 ዓመታቸው አረፉ።

## <u>የደራሲው ሥራዎች</u>

1. ጦቢያ (**ልብወለድ**)
2. ዳግማዊ አጤ ምኒልክ (**ታሪክ**)

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY